አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ
ADDIS MEDIA NETWORK

# አዲስ ልሳን

ቅጽ 32 ቁጥር 3525 | ቅዳሜ ሰኔ 14 ቀን 2017 ዓ.ም | ዋጋው 10.00 ብር




# “ኢትዮጵያን መገንባት ላይ የማንለያይ መሆን አለብን”

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር)

3


ፎቶ- ከገፀ ድር
የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ከተፎካካሪ ፖለቲካ ፓርቲ ተወካዮች ጋር በተወያዩበት ወቅት

## ለተተከሉ ችግኞች ምን ያህል እንክብካቤ እየተደረገላቸው ነው?


6
ፎቶ ከፋይል
የፋይናንስ ቢሮ ሰራተኞች ለተከሏቸው ችግኞች እንክብካቤ ሲያደርጉ

## የበጎነት ፍሬ


8
ፎቶ በመባጽዮን ሀ/ገብርኤል
በበጎ ፈቃድ ቤት የተገነባላቸው ወይዘሮ ሻሼ ሽኖ

## ማዕከላቱ ከዓላማቸው አንጻር ሲመዘኑ፤


9
ፎቶ ከፋይል
በወጣት ማዕከላት ከሚሰጡ አገልግሎቶች መካከል አንዱ የሆነው ቤተ መጻሕፍት

# ለህጻናት መፃእይ ዕድል ትኩረት የሰጠች ከተማ


ፎቶ- ከገፀ ድር
የአዲስ አበባ ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አቤቤ የአፍሪካ የህፃናት ክብካቤ እና ጥበቃን በተመለከተ በአፍሪካ ህብረት አዳራሽ በተካሄደው ጉባኤ ላይ ንግግር ባደረጉበት ወቅት

**በይግለጡ ጓዴ**

አዲስ አበባ ከተማ በቀዳማይ ልጅነት ልማት ፕሮግራም ውጤታማ ስራ እየሰራች ትገኛለች፡፡ በተለይም የልጆች አካላዊ እና አእምሯዊ ዕድገት የሚጀምረው ገና ከፅንስ እና ከጨቅላ ህፃንነታቸው ጀምሮ መሆኑን በመገንዘብ ለነፍሰ ጡር፣ አጥቢ እናቶች እና ሕፃናት የቀጥታ አልሚ ምግብ ድጋፍ እንዲያገኙ ዕድል የተፈጠረላቸው ሲሆን ህፃናት ደግሞ የቀን ማቆያ አገልግሎት ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል።

አዲስ አበባ የህፃናት መዋያዎችን በመኖሪያ ቤቶች አካባቢ በግልና በመንግስት ተቋማት ውስጥ ገንብታ ለአገልግሎት አብቅታለች። በመዲናዋ የሚገኙ የጤና ጣቢያዎች ለእናቶች እና ለሕፃናት ምቹ እንዲሆኑ ስለማድረጓም መረጃዎች ያመለክታሉ፡፡

ህፃናት በትምህርትና በጤና ሁለንተናዊ ዕድገት እንዲጎናጸፉ ለማስቻል የቅድመ አንደኛ ደረጃ መምህራኖች እና የቤተሰብ ምክር

ወደ ገጽ 5 ዞሯል

# “ቴክኖሎጂን በመጠቀም በሚሰጡ አገልግሎቶች በርካታ ውጤቶች እየተገኙ ነው”

በአዲስ አበባ ከተማ የፐብሊክ ሰርቪስ እና ሰው ሀብት ልማት ቢሮ በቢሮ ኃላፊ ደረጃ የአገልግሎት አሰጣጥና አውትሶርሲንግ ዘርፍ ኃላፊ አቶ በቀለ ተመስገን

**በስንታየሁ ምትኩ**

አዲስ አበባን በስሟና ሚናዋ ልክ ውብ፣ በዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪና ለኑሮ ምቹ ለማድረግ በተለያዩ ዘርፎች ትኩረት ተሰጥቶ እየተሰራ ይገኛል። ከተማዋ የነዋሪዎችን ህይወት ለማሻሻል የሚያስችሉ መሰረተ-ልማቶችን በመገንባትና ተገቢውን ቴክኖሎጂ በመጠቀም ስማርት ሲቲ ለመሆን እየተጋች ትገኛለች፡፡

አዲስ አበባ “ስማርት ሲቲ” ለመሆን በምታደርገው ጥረት አንዱ እየሰራችበት ያለው ነዋሪው ወይም

ወደ ገጽ 7 ዞሯል




**አድራሻ** +251 111 112 218 +251 111 267 266 www.amn.gov.et 5 kilo infront of St. Mary Church Addis Ababa Ethiopia

## ርዕሰ አንቀፅ



# የአረንጓዴ ዐሻራ ስኬትን ለማስቀጠል ሁሉም የድርሻውን ይወጣ!

የአየር ንብረት ለውጥ የዓለማችን ፈተና መሆን ከጀመረ ሰነባብቷል፡፡ የዚህ ዳፋ የተረፋቸው ሀገራት ዜጎቻቸው ለህልፈት፣ ንብረቶቻቸው ለውድመት ተዳርገዋል፡፡ ሀገራት ማጣፊያው ሳያጥራቸው ለጉዳዩ አፋጣኝ መፍትሔ ማበጀት ይጠበቅባቸዋል የዘርፉ ምሁራን የሰርክ ውትወታ ነው፡፡ የደን ሽፋንን መጨመር ከቀዳሚ መፍትሔዎች መካከል እንደሚጠቀስ ልብ ይሏል፡፡ ተጨባጭ ውጤት ለማምጣት ደግሞ የሀገራት የተግባር እርምጃ በእጅጉ ያስፈልጋል፡፡

ከግብርና፣ ከማገዶ፣ ከከሰል ማክሰል፣ ከልቅ ግጦሽ፣ ከግንባታና ከእንጨት ስራ ጋር በተያያዘ የኢትዮጵያን የደን ሽፋን ከነበረበት 40 በመቶ ወደ 3 በመቶ አሽቆልቁሎ መቆየቱን የኢትዮጵያ ደን ልማት መረጃ ያመላክታል፡፡ ይህ ደግሞ እየደጋገመ የጎበኛትን ድርቅ ጨምሮ ለዘርፈ ብዙ ችግሮች ዳርጓታል፡፡

እንደ ሀገር ይህን ታሳቢ ያደረጉ ስራዎች በተለያዩ ጊዜያት በመሰራታቸው ውጤት ማስመዝገብ ተችሏል፡፡ የደን ሽፋኑን ከነበረበት 3 በመቶ በ2011 ዓ.ም 17 ነጥብ 2 በመቶ ማድረስ ተችሏል፡፡ በተጠቀሰው ዓመት ምህረት በተጀመረው አረንጓዴ አሻራ መርሃ ግብር እስከ አሁን ባሉት ዓመታት ደግሞ 40 ቢሊዮን ችግኞችን መትከል ተችሏል፡፡ ይህም የነበረውን ሽፋን ወደ 23 ነጥብ 6 በመቶ ከፍ እንዳደረገው ባለፈው ዓመት የተካሄደው ጥናት ሁነኛ አስረጅ ነው፡፡ ጉዳዩን ሀገራዊ አጀንዳ አድርጎ በማንቀሳቀስ ረገድ መንግስት የወሰደው የመሪነት ሚና ይበል የሚያሰኝ እና ተጠናክሮ ሊቀጥል የሚገባው ነው፡፡ ህብረተሰቡም ፋይዳውን በልኩ በመረዳት ከሊቅ እስከ ደቂቅ ብርድና ዝናቡ ሳይበግረው በነቂስ በመውጣት ያሳረፈው አሻራ ለውጤታማነቱ ትልቅ አጋዥ መሆኑን በውል መረዳት ያስፈልጋል፡፡

ዘንድሮም ይኸው መርሃ ግብር ቀጥሎ ከ7 ነጥብ 5 ቢሊዮን በላይ ችግኞችን የመትከል ውጥን መያዙን የግብርና ሚኒስቴር መረጃዎች ያመላክታሉ፡፡ ያለፉት ዓመታት ስራዎቻችን ውጤት ያገኘንበት ብቻም ሳይሆን በቀጣይ ከዚህም በላይ መፈጸም እንድንችል ልምድ የቸሩን ስለሆነ ይኼንኑ ማስፋት ይገባል፡፡ በተለይ አሁን የምንገኝበት የዝግጅት ወቅት ችግኝን ዛፍ የማድረግ አቅሙ ትልቅ ነውና ትኩረት ሰጥቶ መስራት ይገባል፡፡

መዲናችን አዲስ አበባም በአረንጓዴ አሻራው ላይ በንቃት እየተሳተፈች ትገኛለች፡፡ በዘንድሮው መርኃ ግብርም 916 ሄክታር መሬት የሚሸፍን ለተከላ በተለዩ 1577 ቦታዎች ላይ ለበርካታ ጉዳዮች ጥቅም ላይ ሊውሉ የሚችሉ አራት ሚሊዮን ችግኞች እንደሚተከሉ የከተማ ውበትና አረንጓዴ ልማት ቢሮ መረጃ ያመላክታል፡፡ ይህም በአረንጓዴ ሽፋኗ ላይ የራሱን አይተኬ ሚና ይጫወታል፡፡

የተፈጥሮን መልካም ምላሽ ለማግኘት የመንከባከብ ስራው ላይ መበርታት ያስፈልጋል፡፡ በዚህ የሁለትዮሽ መስተጋብር ነው የተሻለ ሀገር ለቀጣዩ ትውልድ ማስረከብ የሚቻለው፡፡ የችግኝ ተከላውንና እንክብካቤውንም የዘወትር ተግባራችን ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ ለዚህ ስኬታማነት ደግሞ ሁሉም የድርሻውን ይወጣ!

## የእኔ እይታ

# ሰሞነኛ እንዳይሆን!

**በሰናይ ምግባሩ**

የቅዳሜ እና እሁድ ገበያዎች የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የኑሮ ውድነት ጫናን ይቀንሱልኛል በሚል በትኩረት እየሰራባቸው ካሉት ተግባራት መካከል ናቸው፡፡ ነዋሪዎችም ከዋጋ አንጻር ከመደበኛ ሱቆች የተሻሉ እንደሆኑ፣ በአቅራቢያቸው መገኘታቸው ደግሞ ድካምና እንግልት እንደቀነሱላቸው በተለያየ መንገድ ሲናገሩ ይደመጣል። እኔም የዚህ ተጠቃሚ ስለሆንኩ ይኼንኑ በድፍረት መመስከር እችላለሁ፡፡

ይህ ማለት ግን ግብይቶቹ "እንከን የለሽ" ናቸው ማለት አይደለም። የሚሻሻሉና የመንግስት አካላትን ትኩረት የሚፈልጉ ጉዳዮችም እንዳሉ የማይካድ ሀቅ ነው፡፡ ከዚህ በፊት በዚህች ገጽ ላይ ሀሳቤን ለማጋራት እንደሞከርኩት፣ የፍጆታ ግብዓቶች የመሸጫ ዋጋ ትልቅ ስራን ይጠይቃል። ንግድ ቢሮ በየድንኳኖቹ ላይ የዋጋ ዝርዝር በሚታይ ቦታ ላይ ይለጥፋል፤ እነሱ ግን ከዚያ በላይ እየጠየቁ ይሸጣሉ፡፡ ከዚህ ቀደም ለግብይት በሄድኩበት ወቅት ፍራፍሬ ገዝቼ የተቀመጠውን ዋጋ ልከፍል ስል የበሰለና ያልበሰለ የሚሉትን ጨምሮ ውሃ የማይቆጥር ምክንያት በማስቀመጥ ዋጋ ጨምሬ እንድከፍል ጠይቆኝ ይህን እንደማላደርግ ነግሬው ትቼለት ሄጃለሁ፡፡ ሌሎች ተገልጋዮችም መሰል ችግር እንደሚያጋጥማቸው ሀሳባቸውን አጋርተውኛል፡፡ ከጎንዮሽ የሀሳብ ልውውጥ ባለፈም ከመንግስት አካላት ጋር በሚደረጉ ውይይቶች ላይ ይህ ጉዳይ ተደጋግሞ ተነስቷል፡፡

ከሰሞኑ ለግብይት በሄድኩበት ጊዜ እነዚህ ነጋዴዎች ንግድ ቢሮ ባስቀመጠው ዋጋ ሲሸጡ ተመለከትኩ፤ እኔም ሸመትኩ፡፡ ይህ እንዲሆን ያደረገው መንግስት የቅርብ ክትትል ማድረጉ መሆኑን መገመት ለስህተት አይዳርግም፡፡ ሆኖም "ይህ አይነቱ እርምጃ ቀጣይነት ይኖረው ይሆን?" የሚል ጥያቄ ግን አለኝ። ነጋዴዎቹ ዛሬ በተቀመጠላቸው ዋጋ ሸጡ ማለት ነገም በዚያው አግባብ ይቀጥላሉ ብሎ ለመናገር አያስደፍርም፡፡ ስለዚህ ንግድ ቢሮ ተከታታይ የሆነ ቁጥጥርና ክትትል ማድረግ ይጠበቅበታል። የተመደቡ የቢሮው ባለሙያዎች የፍጆታ ግብዓቶችን ዝርዝር ዋጋ ከመለጠፍ ባሻገር መሬት ላይ ያለው ግብዓት ምን እንደሚመስል ድንገተኛ ምልከታ ማድረግ፣ የሸማቹንም ስሜት መጋራት ይጠበቅባቸዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም መረጃ መስጫ ተብለው በተቀመጡ የስልክ መስመሮች የሚደወሉ ስልኮችን ማንሳት፣ መረጃውን በአግባቡ አደራጅቶ የመፍትሔው አካል ማድረግ ይገባል ብዬ አስባለሁ። ይህ ከሆነ ከሰሞኑ የታዘብናቸው በጎ ጅምሮች ዘላቂ ሆነው እንዲቀጥሉ ማድረግ ይቻላል፡፡

በመንግስት አካል ክትትልና ቁጥጥር ብቻ የሚፈለገው መፍትሔ ይመጣል ብሎ መጠበቅ ግን የዋህነት ነው። በመጀመሪያ ደረጃ የዋጋ ዝርዝር ተለጥፎ "ዋጋው ስንት ነው?" ብሎ ከመጠየቅ ልምዳችን እንውጣ። ሲቀጥል ደግሞ ከተቀመጠው ዋጋ በላይ ሲጠይቁ "እንደዚህ መሸጥ አትችልም" ብለን እንንገር፣ ሲያስፈልግም በተቀመጠው የስልክ ቁጥር ደውለን ጥቁምታችንን እንስጥ። ይህ ሲሆን እነዚህ ገበያዎች በሚፈለገው ልክ የታለመላቸውን ዓላማ መምታት ይችላሉ የሚል እምነት አለኝ፡፡ እናንተስ?

ADDIS MEDIA NETWORK
አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር
አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ እየተዘጋጀች

ዘወትር ቅዳሜ ወደ አንባቢያን
የምትደርሰው ይህች ጋዜጣ

ግንቦት 1985 ዓ.ም
ተመሰረተች

**አድራሻ**
አምስት ኪሎ ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን ፊት ለፊት በሚገኘው ማህበረ ቅዱሳን ህንፃ ጎን
ስልክ ቁጥር 0111-574923
ፖ.ሣ.ቁ 27080 code 1000
ፋክስ - 559368
addislisan1985@gmail.com

**የገበያ አገልግሎት እና የማስታወቂያ ዝግጅት ዳይሬክቶሬት**
ስልክ 0111 - 112218

**አታሚ**
ሜልባ ፕሪንቲንግ ፐብሊሺንግ ኤንድ ፓኬጂንግ ሼር ካምፓኒ

**ግራፊክስ ዲዛይን**
ዳንኤል ተስፋይ

**ሌይአውትና ዲዛይን**
ፍልሰታ አየለ

**የእርምት ባለሙያ**
ቸርነት ዋለልኝ
ገነት መላኩ

**የዕለቱ አዘጋጆች**
ሄለን ጥላሁን
ፋንታነሽ ተፈራ
ለይላ መሀመድ
ይግለጡ ጓዴ

**ዋና አዘጋጅ**
ምህረቱ ፈቃደ
Mehretu@gmail.com
አድራሻ ለሚ ኩራ ክ/ከተማ
ወረዳ 3 የቤት ቁጥር 34/55

**ም/ዋና አዘጋጅ**
ሰውነት ኃ/ጊዮርጊስ
መለስ ተሰጋ

**ከፍተኛ አርታኢያን**
ደረጀ ታደሰ
ጊዜው አማረ
ስንታየሁ ምትኩ
ሳህሉ ብርሃኑ

# “ኢትዮጵያን መገንባት ላይ የማንለያይ መሆን አለብን”

**ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር)**

**በሳህሉ ብርሃኑ**

ኢትዮጵያን በመገንባት ሂደት ላይ የማንለያይ መሆን አለብን ሲሉ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ተናገሩ።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ (ዶ/ር) ይህን ያሉት ከመላው ኢትዮጵያ ከተውጣጡ ተፎካካሪ የፖለቲካ ፓርቲ ተወካዮች ጋር ውይይት ባካሄዱት ወቅት ነው፡፡ የኢትዮጵያ ፖለቲካ ፓርቲዎች በአዲስ አበባ ከተማ የተሰሩ የልማት ስራዎችን ከጎበኙ በኋላ ከጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ (ዶ/ር) ጋር ውይይት አካሂደዋል፡፡ በውይይቱም ወቅት ስለ ቀጠናዊ ሁኔታ፣ የፖለቲካ ምዕዳርና ስለ ሀገሪቱ ሰላም ጉዳይ፣ የትግራይ ክልልን የተመለከቱ ጉዳዮች እንደዚሁም የመልካም አስተዳደርና በልማት ስራዎች ዙሪያ ጥያቄና አስተያየቶችን አንስተዋል፡፡

ፓርቲዎቹ መንግስት ከተፎካካሪ ፖለቲካ ፓርቲዎች ጋር በየጊዜው ውይይት እያደረገ መሆኑን እውቅና ሰጥተው በሚሰሩ የልማት ስራዎች ላይ ታሪክን መጠበቅ፣ ለስራ ዕድል ፈጠራና ለቴክኖሎጂ ጉዳዮች እንደዚሁም ለኑሮና ለስራ ምቹ ሁኔታዎችን ለመፍጠር ስለተሰራው የኮሪደር ልማት ስራ ምስጋናቸውን አቅርበዋል፡፡

የሀገሪቱን የጸጥታ ችግሮች በዘላቂነት ለመፍታት፣ የሀገራችን ብሔራዊ ጥቅም በሚፃረር ጉዳዮች ላይ የሚሰሩ አካላት፣ በሀገራዊ ምክር ሂደት ላይ እየተሳተፉ ያልሆኑ አካላትን፣ የፖለቲካ ምዕዳሩ ሁኔታና የመንግስት የሚዲያ ተቋማትን የተመለከቱ ጉዳዮች ዙሪያ ጥያቄዎች ተነስተዋል፡፡ እንደዚሁም ዋጋ ንረት፣ ደሞዝ ጭማሪና መሰል ጉዳዮችን በተመለከተ ማብራሪያ እንዲሰጣቸው ጠይቀዋል፡፡ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይም (ዶ/ር) በተነሱ ጉዳዮች ዙሪያ ሰፋ ያለ ማብራሪያ ሰጥተዋል፡፡

የፖለቲካ ፓርቲዎች ጋር ለመገናኘት የተፈጠረው መድረክ የሚፎካከሩ ፓርቲዎች አስፈላጊ በሆኑ ጉዳዮች ላይ የሚተባበሩ መሆናቸው ማሳያ መሆኑን ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ(ዶ/ር) ጠቅሰው የተፈጠረው መድረክ በራሱ ምህዳሩ እየሰፋ መሆኑን ማሳያ እንደሆነ ገልጸዋል፡፡ ከዚህ ቀደም የኢትዮጵያ ጠቅላይ ሚኒስትር በዓመት ሁለቴ ሶስቴ ፓርቲዎችን ሰብስቦ አያናግርም ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፣ መንግሥታቸው ይህን የሚያደርገው በውስጡ ያለውን ክፍተት ለማየት ከፓርቲዎች የሚያገኘው ሀሳብ ጠቃሚ በመሆኑ እንደሆነ ጠቅሰዋል፡፡

የብልፅግና ዕሳቤ በፉክክርና ትብብር መካከል ሚዛን መጠበቅ መሆኑን ያስረዱት ጠቅላይ ሚኒስትሩ ፉክክር ብቻውን ውጤታማ እንደማያደርግም ነው ያስረዱት፡፡ አክለውም ፍጹም የሆነ የፖለቲክ ምህዳር መጠበቅ ማለት ፖለቲካን አለመረዳት መሆኑን አውስተው፣ በመንግሥት በኩል የፖለቲካ ምህዳሩን ለማስፋት ጥረት እየተደረገ ነው ብለዋል፡፡ ጤናማ የሆነ ፉክክር እና ትብብር ሲኖር ደግሞ የፖለቲካ ምህዳሩ እንደሚሰፋ ገልጸዋል፡፡

አሁን ባለው ሁኔታ 273 የተፎካካሪ ፓርቲ ሰዎች በመንግሥት አስተዳደር ውስጥ ተወክለው እየሠሩ እንደሆነ የጠቆሙት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፣ ከነዚህም ውስጥ አራት ሚኒስትሮች፣ አራት ሚኒስትር ዴኤታዎች እና በርካታ የቢሮ ኃላፊዎች እስከ ዞን ድረስ እንዳሉ ተናግረዋል፡፡ “እነዚህን ሁሉ የፖለቲካ ፓርቲ ተወካዮች በአስተዳደሩ ውስጥ አሳትፋለሁ ያለ መንግሥት ለትብብር ያለው ቦታ ትልቅ እንደሆነ ማሳያ ነው” ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፣ ይህም በቂ ነው ብለው እንደማያምኑ እና ትብብሩን ወደ ላቀ ደረጃ በማሳደግ በጋራ ለሀገር የሚጠቅም ሥራ መሥራት አስፈላጊ እንደሆነ እምነታቸውን ገልጸዋል፡፡

በኢትዮጵያ ፖለቲካ ውስጥ የትጥቅ እና ሰላማዊ ትግልን ቀላቅሎ መንቀሳቀስ እንደሚስተዋል የጠቀሱት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር)፣ ፓርቲዎች ብቸኛው ኃይልን የመጠቀም ሥልጣን የመንግሥት መሆኑን ተቀብለው መንቀሳቀስ እንዳለባቸው አሳስበዋል፡፡ “ከሥጋው እያማለሁ ከመረቁ አድርጉልኝ” የሚል አባባልን የጠቀሱት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር)፣ ሰው ከጾመ ከሥጋውም ከመረቁም እንደሆነ ሁሉ የፖለቲካ ፓርቲዎችም የሰላም እና የትጥቅ አካሄድን አጃምለው መንቀሳቀስ የለባቸውም ብለዋል፡፡

“የፖሊሲ ልዩነት ቢኖረንም በኢትዮጵያዊነት እና ኢትዮጵያን በመገንባት እምብዛም የማንለያይ መሆን አለብን” ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፣ በኃይል ፍላጎታችንን እናስፈጽማለን ማለት ግን ይህን አካሄድ ያበላሻል ሲሉ ተናግረዋል፡፡ በቀጣይ ምርጫ የተሻለ አካታችነት ይፈጠራል የሚል እምነት እንዳላቸው የጠቀሱት ጠቅላይ ሚኒትር ዐቢይ፣ የተሻለ ነገር እንዲመጣ ተፎካካሪ ፓርቲዎች ሰብሰብ ብለው ኃይላቸውን ማጠናከር አለባቸው ብለዋል፡፡ ብልፅግና በምርጫው ማሸነፍን ዓላማ አድርጎ ይሠራል ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ (ዶ/ር)፣ ነገር ግን ጠቅላይነት እንደማያዋጣ እና አካታች የፖለቲካ መድረክ በኢትዮጵያ ውስጥ እውን መሆን አለበት ብሎ እንደሚያምኑም አውስተዋል፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ (ዶ/ር) የትግራይ ክልልን በተመለከተ ለተነሱላቸው ጥያቄዎች በሰጡት ማብራሪያ በክልሉ ሊመጣ የሚገባው ልማት፣ ሊሰራ የሚገባው ስራ በበቂ ተሰርቷል ብለን አናምንም ያሉ ሲሆን የተፈናቀሉ ሰዎችን መመለስን በሚመለከት መቶ በመቶ ዝግጁ ነበርን፣ አሁንም ነን ብለዋል። ከዚህ በፊት ራያ ላይ የተፈናቀሉ ሰዎችን የመመለስ ስራ መሰራቱን እና በወልቃይትም በተመሳሳይ ከጊዜያዊ መንግስቱ ጋር ምክክር እየተደረገ መሆኑን በመግለጽ፣ ዜጎች ለፖለቲካ ፍጆታ መጠቀሚያ ሳይሆኑ ቦታቸው ቢመለሱ ከማንም በላይ ኢትዮጵያ ታተርፋለች ሲሉ ተናግረዋል።

ከሕገ መንግሥት ጋር ተያይዞ ለተነሳላቸው ጥያቄ በሰጡት ምላሽ “ሕገ መንግሥት ካልተቀየረ ምኑን የለውጥ መንግሥት ይባላል የሚል እሳቤ ሕፀፅ ያለበት ነው” ያሉ ሲሆን ጥያቄው ተመልሶ ቢፈተሽ የተሻለ እንደሆነ ጠቅሰዋል። ለውጥ ሕጎችን፣ ፖሊሲዎችን፣ ስትራቴጂዎችን፣ መመሪያዎችን ሊይዝ ይቻላል ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፣ ሕገ መንግሥትን መቀየር ብቻ ለውጥ ተደርጎ መወሰድ እንደሌለበትም አስገንዝበዋል፡፡

ሕገ መንግሥቱ መታረም ያለበት ቦታ ላይ በጋራ በመሆን ማረም እንደሚያስፈልግም ገልጸው ለዚህ የሚሆን መድረክ መፈጠሩን የጠቀሱት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች ግን አሁንም በመድረኩ ለመጠቀም ዳተኛ መሆናቸውን ጠቁመዋል፡፡ በሀገራዊ ምክክር ሂደቱ የማይነሳ ጉዳይ እንደሌለ ጠቅሰው፣ የፖለቲካ ፓርቲዎችም ዳተኛ ከመሆን ይልቅ ቀረ የሚሉትን ሀሳብ መስጠት እንዳለባቸው ጥሪ አቅርበዋል፡፡

በአንዳንድ አካባቢዎች ለሚስተዋለው የሰላም ችግር መፍትሄው ምንድነው? ለሚሉ ጉዳዮች በሰጡት ምላሽ መንሥኤው ፍላጎትን በኃይል የማስፈፀም ኋላቀር እሳቤ ነው ብለዋል፡፡ በዚሁ ወቅትም ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ በሀገሪቱ ፖለቲካዊ ወይም ኢኮኖሚያዊ ፍላጎትን በጉልበት ለማስፈፀም የሚደረገው ጥረትና ሙከራ እንደ ሀገር ብዙ ዋጋ እያስከፈለ መሆኑን ገልፀዋል። የተለየ ሀሳብ ያለው ሁሉ የግድ ወደ ውጊያ ከመግባት ሀሳቡን በዴሞክራሲያዊ መንገድ ማራመድ የሚችልበት ምህዳር በመኖሩ መጠቀም ይችላል፤ ጉልበት የመጠቀም እሳቤን በጋራ ማስቆም ያስፈልጋል ብለዋል።

አንዳንዶች ለብዙ ሀገራት ተቀጣሪ ባንዳ በመሆን የሀገር ብሔራዊ ጥቅም በሚጋፋ መልኩ የመሪው አልጋው አልፀናም በመነቅነቅ እናባርረው በሚል ከጠላት ጋር እየሰሩ ናቸው ሲሉም ተናግረዋል ጠቅላይ ሚኒስትሩ። የህዝቦችን መብት እንደሸፋን በመጠቀም የፖለቲካ ንግድ የሚሰሩ፤ እንታገልለታለን የሚሉትን ህብረተሰብ ክፍል የሚያግቱ፣ የሚዘርፉ፣ የሚገሉ መኖራቸውንም ጠቅሰዋል። ለአብነትም ለኦሮሞ ህዝብ ነፃነት እየታገልን ነው እያሉ ህዝቡን እያገቱ እያሰቃዩ በህብረተሰብ ስም የፖለቲካ ንግድ የሚሰሩ መኖራቸውን አንስተዋል።

እርስ በእርሳቸው የማይስማሙ ሃይሎች በታጋይ ስም ተደራጅው ዘረፋ ይፈፅማሉ፤ በህዝበኝነት ስም የተገነቡ ትምህርት ቤቶችን ያፈርሳሉ፣ አስተማሪዎችን ያግታሉ፣ የአፈር ማዳበሪያ ለአርሶ አደር እንዳይደርስ መንገድ ይዘጋሉ ብለዋል። ይህም በኢትዮጵያ ህዝበኝነትና ህዝባዊነት ድንበራቸውን ስተው መቀላቀላቸውን ማሳያ ነው ሲሉ ተናግረዋል ጠቅላይ ሚኒስትሩ። በኢትዮጵያ ውስጥ ፍላጎትን በጉልበት ለመፈፀም ያለውን የተሳሳተ እሳቤ ለመግራት መንግስትም ራሱን ይፈትሻል እናንተም ውስጣችሁን ፈትሹ ሲሉ ለፖለቲካ ፓርቲዎቹ ኃላፊነት ሰጥተዋል።

የባህር በርን አስመልክቶ በሰጡት ማብራሪያ ጉዳዩ ለኢትዮጵያ የፖለቲካ አጀንዳ ሳይሆን የህልውናዋ ጉዳይ ነው ሲሉ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ(ዶ/ር) ተናግረዋል። የኢትዮጵያ የሁልጊዜም



ፎቶ ከገፀ ድር

የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ከተፎካካሪ ፖለቲካ ፓርቲ ተወካዮች ጋር በተወያዩበት ወቅት

ወደ ገጽ 19 ዞሯል

# አረንጓዴ ሸማን የለበሱ ሀገራት

**በመለሰ ተሰጋ**

በፀሐይዋ ግለት ሁሉም እያረረ፣

ደገኛ፣ ቆለኛ፣ መባባሉ ቀረ፡፡

ያስብላል አንዳንዴ! ክረምትን በቲሸርት፣ ግንቦትን በጃኬት ሲሆን ነገሩ፡፡ የሰው ልጅ ስነ ምህዳሩን እያዛባ፣ የሕልውናውን መሰረት እያራቆተ በአረንጓዴ ፀጋ የተሸለመችው ምድር ክብሯ እየረገፈ፣ ወዟ እየነጠፈ በመምጣቱ የአረንጓዴ አሻራን ችላ ባሉ ሀገራት ላይ ገራገር ጠባይዋ እየተቀየረ ነው፡፡

ምድር አረንጓዴ ልብሷ ሲገፈፍ ገላዋ በፀሐይ ወላፈን ሰርክ እየተለበለበ ነው። መረጃዎች እንደሚጠቁሙት ውቅያኖሱ እየሞላ፣ በረዶው እየቀለጠ፣ በልቅ የጋዝ ልቀት የፀሐይ አደገኛ ጨረርን የሚጋርደው የደመናው ሸማ እየሳሳ ምድራዊ ወበቁ ለፍጡራን ሕልውና ስጋት እየሆነ መምጣቱ ምስክር አያሻም፡፡

ምድራችን ሚዛኗ ሲዛባ ደግሞ ጤናማ ኢኮኖሚ እየራቀ፣ ድህነት እየመጠቀ፣ የግብርና ምርታማነት እያሽቆለቆለ፣ ስደት እያሻቀበ፤ ማህበራዊ ፍትህ እየጎደለ፣ የእርስ በርስ ግጭት እየጨመረ መጥቷል የሚሉም ብዙዎች ናቸው። በዚህም ድርቅ፣ በርሃማነት መስፋፋት፣ መሬት መሸርሸር፣ ጎርፍ፣ ርሀብ፣ እርዛት፣ የመሬት መንሸራተት... እና ቁጥር አልባ ጠንቆች ለዓለም ህዝብ መከራን እየጋበዙ ነው።

በዓለም አቀፍ እኩልነት እና በሥነ-ምህዳር ሽግግር ስራዎቹ እውቅናን ያተረፈው የዓለም ኢ-ፍትሐዊነት ላብራቶሪ ዳይሬክተር ሉካስ ቻንስል (ተባባሪ ፕሮፌሰር) እ.ኤ.አ 2020 Unsustainable Inequalities የተሰኘ ጥናታዊ መፅሐፍ አሳትመዋል፡፡ በዚህ ጥናታዊ ስራቸውም በማህበራዊ እኩልነት እና በአካባቢ መራቆት መካከል ያለውን ውስብስብ ግንኙነት መርምረዋል፡፡ መፍትሔዎቹንም አመላክተዋል፡፡

በዚህ መፅሐፍ ላይ በግልፅ እንደሰፈረው የባህር በረዶ ከአርክቲክ ዙሪያ ጠረፍ እየሸሸነው፡፡ በአልፕስ፣ በአላስካ እና በግሪንላንድ እንዲሁም በዓለም ዙሪያ በሚገኙ ዝቅተኛ ላቲትዩዶች የተራራ ሰንሰለቶች የሚገኘው የበረዶ ግግርም በፍጥነት እየቀለጠ ነው፡፡

ይህም ከፍተኛ የአየር ንብረት ለውጥ በምድሪቱ ላይ እያስከተለ ይገኛል፡፡ የአየር ንብረት ለውጥ የሙቀት መጠን እንዲጨምር፣ የባህር ጠለል ከፍ እንዲል፣ የአየር ጠባይ እንዲለዋወጥ፣ እንዲሁም ለመተንበይ አዳጋች የሆኑ ሌሎች ከባድ የአየር ጠባይ የመለዋወጥ ሁኔታዎች እንዲከሰቱ ያደርጋል። በሌላ በኩልም የዝናብ ስርጭት ለውጦች፣ የጎርፍ ክስተቶች፣ የድርቅ ወቅቶች፣ ተደጋጋሚ የሰደድ እሳት አደጋዎች፣ የውሃ አቅርቦት መመናመን እና ሌሎች ችግሮችንም ያስከትላል፡፡

የእነዚህ የአየር ንብረት ለውጥ ውጤትም የሰዎች ለችግር ተጋላጭነትን መጨመር፣ የግብርና ምርቶች መቀነስ፣ የምግብ ዋስትና አለመኖር፣ የውሃ አቅርቦት ችግር መባባስ፣ የስነ ምህዳር መጎዳት፣ እና የጤና ችግር መስፋፋትን እንደሚያመጣ ሉካስ ቻንስል (ተባባሪ ፕሮፌሰር) በጥናታቸው አመላክተዋል፡፡

በመሆኑም ይላሉ ዓለማችን የምታስተናግዳቸውን ተፈጥሯዊ አደጋዎች በዘላቂነት ለመቋቋም ከሚሰጡት ምክረ ሃሳብ ትልቁ አካባቢ መራቆትን መጠበቅ፣ የተራቆቱ የምድራችን ገጾችንም በአረንጓዴ ገጽታ መመለስ እና የደን ሽፋንን ማሳደግ አስፈላጊ ነው።

የዓለም ሙቀት መጨመርን አስመልክቶ የሃርቫርድ ዩኒቨርሲቲ "በሃርቫርድ ጋዜጣ" ላይ በ2022 ይፋ ባደረገው መረጃ መሰረት፡- ምድር ለሰው ትሰጠው የነበረው የሕይወት እስትንፋስ እንደ ሲኦል ወላፈን እየተጋረፈ ብዙ ነፍሳቶችንም እየቀጠፈ ነው፡፡ አስር ዓመታትን ባስቆጠረው በዚህ ጥናት ሰው ከተፈጥሮ ጋር የማይጠቅመው እልህና ጦርነት ውስጥ ስለመግባቱም ብዙ የተፈጥሮ ሀብት ውድመቶችን በመጠቃቀስ የችግሩን አሳሳቢነት በማስረገጥ የዩኒቨርሲቲው ጥናት አመላክቷል፡፡

ጠቢባን ከተፈጥሮ ጋር መስማማት ከራስ ጋር ከመዋደድ ይበልጣል ይላሉ፡፡ እውነትም የሰው ከተፈጥሮ ጋር ሳይስማማ እንኳን ከሌላው ይቅርና ከራሱ ጋር ሊግባባ አይችልም። የሰው ልጅ በምቾትና በሕይወት እንዲኖር ከምትረዳው ተፈጥሮ ጋር መስማማት አቅቶት በተለያዩ የተፈጥሮ እና ሰው ሰራሽ አደጋዎች የመከራ ጅራፍ ያለእረፍት መገረፍ ከጀመረ እልፍ ዓመታት ተቆጥረዋል። ከስህተት የተማሩ ከተፈጥሮ ጋር ያበሩ ህዝቦች ግን አብዝቶ ተጠቃሚ ሆነዋል፡፡

በምድራችን፤ ላይቤሪያ፣ ማይናማር፣ አፍጋኒስታን፣ ሴራሊዮን እና አይቬሪኮስትን የመሳሰሉ ሀገራት አረንጓዴ ልብሳቸውን ከተገፈፉ የዓለማችን ሀገራት መካከል የሚመደቡ መሆናቸውን ከ (world population review.com) ያገኘነው መረጃ ያመለክታል፡፡

በዚሁ መረጃ መሰረትም ሲዊዘርላንድ ከዓለማችን አረንጓዴ ፀጋን የለበሰች ቀዳሚ ሀገር ናት። ሲዊዘርላንድ የምድራችን አረንጓዴዋ ምድር የሚለውን ስያሜ እንዲህ በቀላል አላገኘችውም፡፡ በአጭር ጊዜም ሆነ በረዥም ጊዜ የሀገሪቷ ዕቅድ ውስጥ የአረንጓዴ አሻራ ጉዳይ በዋናነት ይቀመጣል፡፡ በልዩ ትኩረትም ይሰራል። ዜጎቿ ስለ አረንጓዴ አሻራ ያላቸው ግንዛቤ ከፍ እንዲልም ብዙ ሰርታለች። ይህን በማድረጓም ያለማንም ወትዋችና ጎትጓች የአረንጓዴ አሻራ ጉዳይ የሲዊዘርላንዳውያን ብሔር ብሔረሰቦች የጋራ መገለጫ ኩራታቸው ነው። ችግኝ መትከል፣ ተንከባክቦ ማሳደግና ተፈጥሮን መጠበቅ ደግሞ የዚች ሀገር ዜጎች የጋራ ቋንቋ ነው።

ሲዊዘርላንድ ከዚህ ባሻገርም ተፈጥሮን ከሚበክሉ የሀይል ማመንጫዎች በመራቅ የፀሐይ፣ የንፋስ፣ የውሃ፣ የእንፋሎትና መሰል ንፁህ የሀይል ምንጮችን ትጠቀማለች፡፡ ይህንንም በማድረጓ የተረጋጋ እድገት የሚመዘገብባት፣ ጤናማና ረዥም ዕድሜ ያላቸው ዜጎች የሚኖሩባት አረንጓዴዋ የምድራችን ቀዳሚ ሀገር ሆናለች፡፡



ፎቶ- ከገፀ ድር

ሀገራት የአረንጓዴ አሻራ መርሃ ግብርን ዋና አጀንዳቸው በማድረግ ሁለንተናዊ ከፍታቸውን ማስቀጠል ችለዋል

እንደ መረጃው ከሆነ ከሲዊዘርላንድ በመቀጠል ፈረንሳይ፣ ዴንማርክ፣ ማልታ፣ ሲዊድን፣ ዩናይትድ ኪንግደም፣ ሉዘንበርግ፣ አየርላንድ እና ፊኒላንድ እጅግ ጤናማ የተፈጥሮ ሀብት ያላቸው አረንጓዴ ለበስ ሀገራት ናቸው፡፡

ሀገራቱ ለዚህ የበቁበት ትልቁ ምስጢር ስለ አረንጓዴ አሻራ ጥቅም የዜጎቻቸውን አመለካከት ከፍ በማድረጋቸው፣ ዘላቂነት ባለው መልኩ በአጭርና ረዥም ጊዜ ሀገራዊ ዕቅዶቻቸው የአረንጓዴ አሻራን ጉዳይ አካተውና ዜጎቻቸውን በነቂስ በማሳተፍ ጠንክረው በመስራታቸው፣ ታዳሽ የሀይል ምንጮችን በመጠቀማቸው፣ መተኪያ የሌላቸውን የተፈጥሮ ሀብቶቻቸውን ተንከባክበው በመያዛቸውና የአካባቢ ልማት ስራዎቻቸው ትውልድ አስከባሪ ዘመን ተሻጋሪ እንዲሆኑ አስበው በመስራታቸው እንደሆነም መረጃው ያመለክታል፡፡

በጥንታዊው ታሪኳ ከሰው ልጆች ጦር ለመከላከል ታላቁን ግንብ በነጫጭ ድንጋዮች ገንብታ ድንበሯን በማጠር ዓለምን ያስደመመችው ቻይና፣ አሁን ደግሞ በአረንጓዴ ግንብ ከተፈጥሮ ጋር ለመወዳጀት የሚያስችላትን አዲስ ገድል እየፃፈች ነው፡፡ እ.ኤ.አ. ከ1978 ጀምሮ እየገነባች ያለችውን ግዙፍ የደን አጥር( አረንጓዴ ግንብ)፣ በሰሜናዊ ደረቃማ እና ከፊል ደረቃማ ዞኖች፣ የውስጥ ሞንጎሊያ፣ ጋንሱ፣ ኒንግዢያ እና ዢንጂያንግን የሚያካልል ነው። ይህ ፕሮጀክት የቻይና ህልውና ስጋት የሆነውን የጎቢ በረሃ መስፋፋትን እንደሚገታውም ይነገርለታል።

ቻይና የአረንጓዴ ግንብ መርሐ ግብር እ.ኤ.አ. በ 2024 ከ30 ሚሊዮን ሄክታር በላይ ችግኞችን በመትከል የሀገሪቱን የደን ሽፋን በ1949 ከነበረበት 10 በመቶ ወደ 25 በመቶ ማሳደግ ችላለች።

የኪንግ አብዱላህ የአረንጓዴ አሻራ ተነሳሽነት ደግሞ ሳውዲን አረንጓዴ እያለበሰ ያለ ስልጡን መላ ነው፡፡ እ.ኤ.አ በ2021 የተጀመረው ይህ ንቅናቄ የሀገሪቱ ህልውና ማስጠበቂያ የማዕዘን ድንጋይ ነው። ፕሮጀክቱ በደን ልማት፣ በብዝሀ ሕይወት ጥበቃ እና በልቀቶች ቅነሳ ላይ በማተኮር ሳውዲን በአካባቢያዊ ዘላቂ ልማት ላይ ዓለም አቀፋዊ መሪ ለማድረግ ያለመ ነው።

ከዋና ዋና ዓላማዎቹ መካከልም የደን ልማት፣ በረሃማነትን ለመከላከል እና አረንጓዴ ሽፋንን ለማሳደግ 10 ቢሊዮን ችግኞችን በሳውዲ ምድር በመትከል፣ በ2030 የካርቦን ልቀትን በ278 ሚሊዮን ቶን መቀነስን የመሳሰሉ ወሳኝ ዓላማዎችን ያነገበ ነው፡፡

በሳውዲ አረቢያ አረንጓዴ አሻራ ንቅናቄ እ.ኤ.አ ከ2021 እስከ 2024 ባሉት ዓመታት ብቻ ከ100 ሚሊዮን በላይ ችግኞች ተተክለዋል። ከ118 ሺህ ሄክታር በላይ የተራቆተ መሬት ወደነበረበት ተመልሷል። ከዚህ ባሻገርም ታዳሽ ሀይልን የመጠቀም፣ ብዝሃ ህይወትን የመጠበቅ አቅም ከፍ እያለ እንደመጣም የሳውዲ መንግስት ከሰሞኑ ይፋ ያደረገው መረጃ ያመለክታል፡፡

ወደ ኢትዮጵያ ስንመለስ በጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) መሪነት ከ2010 ዓመተ ምህረት ጀምሮ በስፋት እየተተገበረ ያለው የአረንጓዴ ልማት አሻራ መርሐ ግብር ተስፋ ሰጭ ለውጦች እያመጣ መሆኑን በርካቶች በመመስከር ላይ ናቸው፡፡ በዚህና በተያያዥ ስራዎች እነ ሀሮማያን የመሳሰሉ ሀይቆች ዳግም ተወልደዋል፡፡ አቢያታና ሻላ ካንዣበበባቸው አደጋ ወጥተዋል፡፡ ተመናምነው የነበሩ ደናማ ስፍራዎችም ወደነበሩበት እየተመለሱ እንደሆነም የግብርና ሚኒስትር በተከታታይ የሚያወጣቸው ተጨባጭ መረጃዎች ያመለክታሉ፡፡

የኢትዮጵያ መንግስትም በአስር ዓመቱ ስትራቴጂክ የልማት ዕቅዱ ካሰፈራቸው ስድስት አበይት ነጥቦች መካከል ከተፈጥሮ የተስማማ አረንጓዴ ኢኮኖሚ መገንባት የሚለው አንዱ ጉዳይ መሆኑ ይታወቃል፡፡

# ለህጻናት ... ከገጽ 1 የዞረ

ሰጪ የጤና ባለሙያዎችን በማሰልጠን "አዲስ አበባን ህፃናትን ለማሳደግ ምርጧ አፍሪካዊት ከተማ" ለማድረግ እየተሰራ ይገኛል፡፡

ባሳለፍነው ሀሙስ "በአፍሪካ ጥራት ያለውና አካታች የሆነ የህጻናት እድገትን ለማረጋገጥ የጋራ ትብብርን ማጠናከር" በሚል መሪ ቃል የአፍሪካ የህፃናት ክብካቤ እና ጥበቃን የተመለከተ ኮንፍረንስ በአፍሪካ ህብረት አዳራሽ መካሔዱ ይታወሳል፡፡

በእለቱ ከንቲባ አዳነች አቤቤ እንደገለጹት ኮንፍረንሱ አዲስ አበባ እንዲካሄድ የተመረጠዉ ከተማዋ የአፍሪካ ህብረት መቀመጫ ስለሆነች ብቻ ሳይሆን አዲስ አበባ ህጻናት በአዕምሮ፣ በአካል እና በስነልቦና የተሟላ ዕድገት እንዲጎናጸፉ ለማስቻል የሰራችዉ የተቀናጀ እና አካታች የቀዳማይ ልጅነት ልማት ፕሮግራም አፍሪካውያን ትምህርት የሚወስዱበት ውጤታማ ስራ በመሆኑ ጭምር ነው ብለዋል።

ከንቲባ አዳነች አፍሪካዊያን እጅ ለእጅ በመያያዝ ለተሻለ ነገ ከልብ እንዲሰሩ ጥሪ ያቀረቡ ሲሆን እስካሁን በከተማዋ የተሰሩ ስራዎችን ልምድ አካፍለዋል፡፡



ፎቶ- ከገፀ ድር
አዲስ አበባ በቀዳማይ ልጅነት ፕሮግራም ያስመዘገበችውን ስኬት ለጉባኤው ታዳሚዎች አካፍላለች

ባለፈው ዓመት ግንቦት ወር ላይ የተለያዩ የአፍሪካ ሀገራት መሪዎች እና ዓለም አቀፍ ተቋማት ተወካዮች የሕፃናት መዋያዎችን፣ ጤና ጣቢያዎችን፣ ቤት ለቤት ለህፃናትና ለእናቶች የሚደረገውን ድጋፍና ክትትል ምን እንደሚመስል ጉብኝት አድርገዋል፡፡

ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አቤቤ የከተማዋን የትውልድ ግንባታ ስራዎች ለመሪዎቹ ባስጎበኙበት ወቅት እንደገለፁት አዲስ አበባን፣ ህፃናትን ለማሳደግ ምርጧ አፍሪካዊት ከተማ የማድረግ ስራችን እውቅና አግኝቶ ለሌሎች ልምድ በማካፈላችን ደስታ ይሰማናል ማለታቸው የሚታወስ ነው፡፡ በህፃናት ማቆያ ማዕከላት ልጆች የተመጣጠነ ምግብ፣ የሞግዚት አገልግሎት፣ የጤና ክትትል፣ ትምህርት በጨዋታና በእናቶች ምክር አገልግሎት እያገኙ የተሟላ ዕድገት እንዲኖራቸው ልዩ ክትትል እንደሚደረግላቸውም ገልፀዋል፡፡ በቀጣይም የሕፃናት ማቆያዎችን፤ የመጫዎቻ ቦታዎችን ለማስፋፋት በትኩረት እንደሚሰራ መግለጻቸው ይታወቃል፡፡

አዲስ አበባ ለትውልድ ግንባታ የሰጠችው ትኩረት አስደናቂ መሆኑን በእለቱ በጉብኝቱ ላይ የታደሙ የተለያዩ ሀገራት መሪዎችና የዓለም አቀፍ ተቋማት ተወካዮች መናገራቸው ይታወሳል፡፡

የኤልማ ግብረ ሰናይ ድርጅት ፕሮግራም ዳሬክተር ትሬሳ ጆንሰን፣ የቀዳማይ ልጅነት ልማት በጤና ማዕከላት ያለውን አስደሳች አፈፃፀም፣ በቦሌ ክፍለ ከተማ አስተዳደር ግቢ ውስጥ ያለውን የህፃናት ማቆያ ተመልክተናል፡፡ በዚህ ስፍራ እናቶች ልጆቻቸውን በምቹ ቦታ አስቀምጠው ስራቸውን ያለስጋት ሲከውኑ ማየት እጅግ ያስደስታልም ማለታቸው ይታወሳል፡፡

የታንዛኒያ ፕሬዝዳንት ጽሕፈት ቤት ምክትል ሚኒስትር ፌስቶ ጆኒ ዱጋንጌ (ዶ/ር) አዲስ አበባ ለልጆቿ የተሻለ ነገን ለመፍጠር ቁርጠኛ መሆኗን ተመልክተናል፡፡ ያየነውም እንቅስቃሴ ይህንን የሚመሰክር ነው፡፡ በህፃናት ማቆያዎች፣ በጤና ጣቢያዎች እና በተለያዩ ስፍራዎች ሕፃናት ታሳቢ ተደርገው የተገነቡ ልማቶች በጣም ማራኪ ናቸው፡፡ ለነፍሰጡር እናቶች የሚደረገው ጥረትና መሰል ክብካቤም እንደ ታንዛኒያ ትልቅ ትምህርት የምንወስድበት ነውም ሲሉ ሀሳባቸውን ሰጥተዋል፡፡

የዛንዚባር የትምህርትና ሙያ ስልጠና ሚኒስትር ለኢላ ሙሃመድ በበኩላቸው ከንቲባዋ እየተሰሩ ስላሉ ልማቶች ገለፃ ሲያደርጉ "ይህ እንዴት ይቻላል ብዬ ነበር፡፡ ይሁን እንጂ በጉብኝቱ ወቅት እንዳረጋገጥኩት ሁሉም ነገር እንደሚቻል ነው፡፡" ሲሉ መስክረዋል፡፡

ባሳለፍነው ሐሙስ "በአፍሪካ ጥራት ያለውና አካታች የሆነ የህጻናት እድገትን ለማረጋገጥ የጋራ ትብብርን ማጠናከር" በሚል መሪ ቃል የአፍሪካ የህፃናት ክብካቤ እና ጥበቃን የተመለከተ ኮንፍረንስ በአፍሪካ ህብረት አዳራሽ ተካሂዷል። በዚሁ ወቅት ንግግር ያደረጉት የአዲስ አበባ ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አቤቤ በአፍሪካ ጠንካራ ማህበረሰብ ለመገንባት አፍሪካዊያን በህጻናት መፃኢይ ዕድል ላይ ትርጉም ያለው ተግባራዊ ውሳኔ ለማሳለፍ በትብብር የምንቆምበት ወቅት ላይ እንገኛለን ብለዋል፡፡

ከንቲባዋ አክለውም "ዛሬ ኮንፍረንሱ አዲስ አበባ እንዲካሄድ የተመረጠዉ ከተማዋ የአፍሪካ ህብረት መቀመጫ ስለሆነች ብቻ ሳይሆን አዲስ አበባ ህጻናት በአዕምሮ፣ በአካል እና በስነ ልቦና የተሟላ ዕድገት እንዲጎናጸፉ ለማስቻል የሰራችዉ የተቀናጀ እና አካታች የቀዳማይ ልጅነት ልማት ፕሮግራም አፍሪካውያን ትምህርት የሚወሰዱበት ውጤታማ ስራ በመሆኑ ጭምር ነው።" በማለት አብራርተዋል፡፡

> **ለትውልድ ማሰብ እና በዚያው ልክ መስራት ሀገርን በፅኑ መሰረት ላይ የመገንባት አንዱ እና ዋናው ጉዳይ ነው**

መድረኩን ያዘጋጀው የአፍሪካ ህብረት የጤና፣ የሰብዓዊ ጉዳዮችና ማህበራዊ ልማት ኮሚሽን ሲሆን በኮንፈረንሱ የተለያዩ የአፍሪካ ሀገራት ሚንስትሮች፣ የዓለም አቀፍ ተቋማት መሪዎች፣ የዘርፉ ባለሞያዎች እና ተመራማሪዎች ታድመዋል፡፡

"በአፍሪካ ጥራት ያለውና አካታች የሆነ የህጻናት እድገትን ለማረጋገጥ የጋራ ትብብርን ማጠናከር" በሚል መሪ ቃል የአፍሪካ የህፃናት ክብካቤ እና ጥበቃን የተመለከተ ኮንፍረንስ በአዲስ አበባ መካሄዱና የአፍሪካ ሀገራት በከተማዋ እየተከናወኑ ካሉ የትውልድ ግንባታ ስራዎች ልምድ መቅሰማቸው የመዲናዋን ተመራጭነት ከፍ የሚያደርግ መሆኑን በዋቸሞ ዩኒቨርሲቲ የፖለቲካል ሳይንስና ዓለም አቀፍ ግንኙነት መምህር ሳሙኤል ሺበሺ ተናግረዋል፡፡

ባሳለፍነው ዓመት ግንቦት ወር ከተለያዩ የአፍሪካ ሀገራት ልምድ ለመቅሰም ወደ መዲናዋ መምጣታቸው ይታወሳል። በዚሁ ወቅት የከተማ አስተዳደሩ ይፋ ባደረገው መረጃ መሰረት በከተማዋ 597 የህጻናት መዋያዎችን በመኖሪያ ቤቶች አካባቢ፣ በግል እና በመንግስት ተቋማት ውስጥ ተገንብተዋል፡፡ በነዚህ ማቆያዎች ለህጻናቱ የተመጣጠነ ምግብ፣ የሞግዚት አገልግሎት፣ የጤና ክትትል፣ ትምህርት በጨዋታ መስጠት፣ የእናቶች ምክር አገልግሎት እንዲሁም የተሟላ እድገት እንዲኖራቸው ልዩ ክትትል ይደረግላቸዋል፡፡

በዚሁ ወቅት ከንቲባ አዳነች አቤቤ አዲስ አበባ ህጻናትን ለማሳደግ ምርጧ አፍሪካዊት ከተማ የማድረግ ስራችን እውቅናን አግኝቶ ለሌሎች ልምድ የሚያካፍል ደረጃ ላይ በመድረሱ ደስታ የሚሰማን ሲሆን በቀጣይ የህጻናት መዋያዎችን 1000፣ የመጫወቻ ቦታዎችን ደግሞ 12 ሺህ ለማድረስ በርትተን እንስራ ብለዋል፡፡

የፖለቲካል ሳይንስና ዓለም አቀፍ ግንኙነት መምህሩ ሳሙኤል ሺበሺ በበኩላቸው አዲስ አበባ በዚህ ደረጃ ተመራጭ መሆኗ አሁንም ኢትዮጵያ፣ ለአፍሪካውያን ሁለንተናዊ ለውጥ ተምሳሌት መሆኗን የሚያሳይ ነው። በሌላ በኩልም አዲስ አበባ፣ የአፍሪካ መዲና እንደመሆኗ መጠን በሁሉም መስክ ይህንን ሊመጥን የሚችል ስራ እያከናዎነች መሆኑን የሚመሰክር ስለመሆኑም ተናግረዋል፡፡

የፖለቲካል ሳይንስና ዓለም አቀፍ ግንኙነት መምህሩ አክለውም ይህ ተግባር ከዛሬ አልፎ ለነገ ማሰብን፣ ለትውልድ መጨነቅን የሚያሳይ በመሆኑ ለአፍሪካዊያንም ሆነ ለዓለም ትልቅ ትምህርትን የሚሰጥ ነው፡፡ በርግጥም አፍሪካዊያን በእርስ በርስ ግጭት እና በተለያየ አሉታዊ ነገሮች ከመታወቅ ወጥተን በልማት መተሳሰርን አንዱ ከሌላው መልካም ነገርን መማር እንደምንችልም ትምህርት የሚሰጥ ነው ብለዋል፡፡

አክለውም ለትውልድ ማሰብ እና በዚያው ልክ መስራት ሀገርን በፅኑ መሰረት ላይ የመገንባት አንዱ እና ዋናው ጉዳይ ነው፡፡ በመሆኑም እንደ አዲስ አበባ በትውልድ ግንባታ ላይ እየተሰሩ ያሉ ተግባራት የበለጠ በሀገር ደረጃ እንዲሰፉ ቢደረግ በአጭር ጊዜ ውስጥ ለብዙ ችግሮቻችን መልስ ማግኘት ያስችላል። ዓለም አቀፍ ተደማጭነታችንንም ከፍ ያደርጋል፡፡ አዲስ አበባ ከፍ አለች ማለት ጥቅሙ ለኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን አህጉራዊ መሆኑን አሁን ከተደረገው ኮንፈረንስ ባሻገር የተለያዩ የአፍሪካ ሀገራት መሪዎች እና አለም አቀፍ ተቋማት የተወከሉ ጎብኚዎች ባሳለፍነው ግንቦት ወር ያደረጉት ጉብኝት አንዱ ማሳያ እንደሆነም አስታውሰዋል፡፡

# የተተከሉ ችግኞች ምን ያህል እንክብካቤ እየተደረገላቸው ነው?

- ቢሮው በጥናት ባረጋገጠው መሰረት በከተማዋ ከተተከሉ ችግኞች መካከል 88 ነጥብ 3 በመቶ መጽደቃቸው ታውቋል።

**በይግለጡ ጓዴ**

በየዓመቱ በሀገር አቀፍ ደረጃ የአረንጓዴ ልማት የችግኝ ተከላ መርሃ ግብር እየተካሄደ እንደሚገኝ ይታወቃል። አዲስ አበባ ከተማም ይህን የአረንጓዴ ልማት መርሃ ግብር እየተገበረች ትገኛለች። ይሁንና ችግኝ መትከል ብቻ በራሱ ግብ አይደለምና የተተከሉ ችግኞች የት ደረሱ ብሎ መንከባከብ እና ለጽድቀት ማድረስ ይገባል፡፡

በከተማዋ በርካታ ግለሰቦች እና ተቋማት ባለፉት የክረምት ወራት ችግኞች መትከላቸው ይታወሳል፡፡ የዝግጅት ክፍላችንም እነዚህ ግለሰቦች እና ተቋማት የተከሏቸው ችግኞች እንዲጸድቁ ከማድረግ አኳያ እንዴት እየተንከባከቡ እንደሚገኙ ቅኝት አድርገናል፡፡

በአዲስ አበባ ፋይናንስ ቢሮ ጽ/ቤት ኃላፊ አቶ ሽመልስ ዘመዴ ባለፈው የክረምት ወራት በፋይናንስ ቢሮ እና በስሩ ያሉ ሰራተኞችን በማስተባበር 50 ሺህ ችግኞችን ተክለው በመንከባከብ አብዛኞቹ መጽደቃቸውን ገልጸዋል። ችግኝ የተከሉበትን አካባቢ ከእንስሳት ንክኪ ነጻ በማድረግ ታጥሮ የተጠበቀ በመሆኑ የተተከሉ ችግኞች መጽደቃቸውን ተናግረዋል፡፡

እንደ አቶ ሽመልስ ገለጻ ውሃ በቦቲ መኪና በማቅረብ፣ መኮትኮቻና ውሃ ማጠጫ ቁሳቁስ በመግዛት የመኮትኮት፣ አረም የማረምና ውሃ የማጠጣት ስራ መስራታቸውን ገልጸው የችግኝ እንክብካቤ ስራውን በጋውን ሙሉ በየወሩ እየሄዱ እየተንከባከቡ እንደነበር ተናግረዋል፡፡

አቶ ሽመልስ ችግኝ መትከል ብቻ ሳይሆን መንከባከብ እንደሚገባ ገልጸው ማንኛውም ሰው የተከለውን ችግኝ መኮትኮት፣ በውሃ ማጠጣት ተንከባክቦ ማሳደግ ይጠበቅበታል ብለዋል። በክረምት የተከልናቸውን ችግኞች በጋ ላይ እንዳይደርቁ መኮትኮት፣ ውሃ ማጠጣት፣ ተንከባቦ ማሳደግ ከእኛ ይጠበቃል የሚሉት አቶ ሽመልስ ካልሆነ ግን ውጤታማ መሆን እንደማይቻል ይገልጻሉ፡፡

የአለርት ኮምፕሬሄሲቭ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል ማዕከል የህዝብ ግንኙነት ኮሙኒኬሽን ዳይሬክተር አቶ አለምሰገድ ጫኔ በሆስፒታሉ ግቢ የፍራፍሬና ልዩ ልዩ ሀገር በቀል ችግኞችን በመትከል እንክብካቤ እያደረጉ እንደሚገኙ ገልጸዋል፡፡ በሆስፒታሉ ለችግኝ እንክብካቤ የቀን ሰራተኞችን በመቅጠር እንክብካቤ እያደረጉ መሆኑን አቶ አለምሰገድ ገልጸዋል፡፡ በዚህም የተተከሉ ችግኞች መጽደቃቸውን ተናግረዋል፡፡ አቮካዶ ፣ ቡናና ለምግብነት የሚያገለግሉ ሌሎች የፍራፍሬ ዛፎችን በመትከል እንክብካቤ በማድረግ አጽድቀዋል፡፡

እንደ አቶ አለምሰገድ ገለጻ ችግኞችን መንከባከብ ልጆችን እንደመንከባከብ የሚቆጠር መሆኑን ገልጸው ሁሉም ሰው የተከለውን ችግኝ ለውጤት እንዲበቃ እንክብካቤ ማድረግ ይገባዋል ብለዋል፡፡

በአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ የከተማ ውበትና አረንጓዴ ልማት ጽ/ቤት ኃላፊ አቶ ቢኒያም ተስፋዬ በክፍለ ከተማው ባለፈው የክረምት ወቅት በሁለተኛው ምዕራፍ የአረንጓዴ አሻራ መርሃ ግብር 950 ሺህ ችግኞችን ለመትከል አቅደው የተለያየ ዝርያ ያላቸው 1 ሚሊየን 437 ሺህ ችግኞችን መትከላቸውን ገልጸዋል። በክፍለ ከተማው በሚገኙ የተለያዩ ቦታዎች ላይ ችግኝ የተከሉ መሆናቸውን ገልጸው በተከላው የተለያዩ የማህበረሰብ ክፍሎች ተሳትፎ ማድረጋቸውን ጠቁመዋል፡፡

ነባር አረንጓዴ ቦታዎችን እና ባለፈው ዓመት የተተከሉ ችግኞችን በበጎ ፈቃደኞች፣ በባለሃብቶች፣ በመንግስት ተቋማት፣ በሐይማኖት ተቋማት፣ በፍሊፖስ ዘላቂ ማረፊያ ቦታ እና በሌሎችም ቦታዎች መተከላቸውን ገልጸዋል፡፡ ማህበረሰቡን በማሳተፍ የእንክብካቤ ስራ ተሰርቷል፡፡ በሁለተኛ ዙር የአረንጓዴ አሻራ በክፍለ ከተማው በሚገኙ 12 ወረዳዎች የተተከሉ ችግኞችን የዳሰሳ ጥናት በማድረግ 91 ነጥብ 5 በመቶ መጽደቃቸውን ገልጸዋል፡፡

እንደ አቶ ቢኒያም ገለጻ በችግኝ ተከላ የተሳተፉ ሁሉ ችግኞችን እንክብካቤ እያደረጉ ሲሆን በመደበኛነት ደግሞ በየወረዳው የሚገኙ ባለሙያዎች፣ አትክልተኞች ችግኞችን እየተንከባከቡ እንደሚገኙ ተናግረዋል፡፡ ለዚሁ ተግባር ሁለት የውሐ ማጠጫ ቦታዎችን አዘጋጅተው ችግኞችን በመዟዟር ውሃ እያጠጡ እንደነበር ኃላፊው ጠቁመዋል። ለችግኝ እንክብካቤ የሚውል አፈር፣ ኮምፖስት፣ መኮትኮቻ መግዣ በጀት በመያዝ ግዥ በመፈጸም እንክብካቤ በማድረግ ላይ መሆናቸውን ገልጸዋል፡፡

ግብዓቶችን በማሟላት በንቅናቄ ፕሮግራም ችግኝ እንክብካቤ ስራ እየተሰራ ሲሆን እሁድ፣ ቅዳሜና በስራ ሰዓት የእንክብካቤ ፕሮግራም እየተደረገ መሆኑን አቶ ቢኒያም ተናግረዋል። የጥበቃ ባለሙያ በመቅጠር፣ አጥር በማጠር ችግኞችን ከጉዳት እየታደጉ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

በክፍለ ከተማው ችግኝ የተከሉ ተቋማትና ነዋሪዎች መትከል ብቻ ሳይሆን መንከባከብ እንደሚገባቸው ውል በማዋዋል እንዲንከባከቡ እየተደረገ ሲሆን በውላቸው መሰረት ለችግኞች እንክብካቤ ማድረጋቸውን ክትትል እንደሚያደርጉ ተናግረዋል፡፡

> **የተተከለውን ችግኝ የቅርብ ክትትል በማድረግ ውሃ ማጠጣት፣ መኮትኮት እና ዙሪያውን በሳር በመሸፈን እንክብካቤ ማድረግ ይገባል**



ፎቶ- ከፋይል

የፋይናንስ ቢሮ ሰራተኞች ለተከሏቸው ችግኞች እንክብካቤ ሲያደርጉ

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የከተማ ውበትና አረንጓዴ ልማት ቢሮ የተፋሰስና አረንጓዴ ልማት ዳይሬክተር ተወካይ ወ/ሮ ስንታየሁ መንግስቱ ባለፈው ዓመት በክረምት የአረንጓዴ አሻራ የችግኝ ተከላ መርሃ ግብር በከተማዋ ከተተከሉ 88 ነጥብ 3 በመቶ መጽደቃቸውን ገልጸዋል።

እንደ ወ/ሮ ስንታየሁ ገለጻ ችግኞች ባሉት ክፍት አረንጓዴ ቦታዎች፣ ጥብቅ ደን፣ የጋራ መኖሪያ ቤቶች፣ ትምህርት ቤቶች፣ ሆስፒታሎች፣ የሃይማኖት ተቋማት፣ መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማት ላይ ሰፊ የንቅናቄ ስራ በመስራት ችግኞችን በመትከል መንከባከብ መቻላቸውን ገልጸዋል፡፡

ሀገር በቀል እጽዋቶችን፣ የፍራፍሬና የውበት ችግኞችን በብዛት በመትከል ቦታውን መሸፈን ተችሏል ብለዋል። በስራውም የከተማዋ ነዋሪዎች የባለቤትነት ስሜት ተሰምቷቸው ዝናብና ብርድ ሳይገድባቸው በመትከል ለጽድቀት ማብቃት መቻላቸውን አስታውሰዋል፡፡

የተተከሉ ችግኞች ከፍተኛ እንክብካቤና የቅርብ ክትትል የሚጠይቁ መሆኑን ወ/ሮ ስንታየሁ ገልጸው እንዲጸድቁና ቀጣይነታቸውን ከማረጋገጥ ጎን ለጎን እየተሰሩ ያሉ ስራዎች መኖራቸውን ተናግረዋል፡፡

በችግኝ ተከላው 142 ተቋማት ተሳትፎ ማድረጋቸውን ጠቁመው ችግኝ ተከላ ላይ የተሳተፉ የፌዴራልና የአዲስ አበባ የመንግስት ተቋማት ችግኝ የተከሉበት ቦታ እና የተከሉትን የችግኝ ዓይነት ርክክብ ማድረግ መቻላቸውን ገልጸዋል። በዚህም አብዛኛው ተቋማት በጀት በመያዝና ሰራተኞቻቸውን በማስተባበር በተሰጣቸው ቦታ ችግኝ ተክለው መንከባከባቸውን ገልጸዋል፡፡

ችግኝ የተከሉ አካላት በኃላፊነት እንዲከታተሉ እና እንክብካቤ እንዲያደርጉ የውል ርክክብ ማድረግ መቻሉን ጠቁመዋል፡፡ እያንዳንዱ ክፍለ ከተማ ችግኝ የተከሉ ተቋማትን በደብዳቤ የችግኝ የኩትኳቶ እና የእንክብካቤ ስራ እንዲሰሩ በማድረግ መንከባከብ መቻላቸውን ጠቁመዋል። በዚህም በሁሉም ክፍለ ከተሞች የችግኝ እንክብካቤ ስራ የተሰራ መሆኑን ተናግረዋል፡፡

ወ/ሮ ስንታየሁ ችግኝ መትከል እና ተክሎ ዞር ማለት በራሱ በቂ አለመሆኑን ገልጸው ልክ እንደ ልጅ የተተከለውን ችግኝ የቅርብ ክትትል በማድረግ ውሃ ማጠጣት ፣ መኮትኮት እና ዙሪያውን በሳር በመሸፈን እንክብካቤ ማድረግ ይገባል ብለዋል፡፡

ሁሉም ተቋማትና ግለሰቦች በክረምቱ የተከሏቸውን ችግኞች በበጋ ውሃ ለማጠጣት በገቡት ቃል መሠረት ችግኞችን ውሃ ማጠጣት፣ በመኮትኮት እና በማረም እንክብካቤ ማድረጋቸውን አጠናክረው እንዲቀጥሉ ወ/ሮ ስንታየሁ አሳስበዋል።

በከተማዋ ለዘንድሮ የአረንጓዴ አሻራ መርሃ ግብር የሚተከሉ ችግኞችን የመለየት እና የማፍላት ስራን ጨምሮ አስፈላጊዉን የቅድመ ዝግጅት ስራ መደረጉም ታውቋል፡፡

## “ቴክኖሎጂን ... ከገጽ 1 የዞረ

ተገልጋዩ ማህበረሰብ የሚያገኛቸውን የመንግስት አገልግሎቶች ፈጣንና ቀልጣፋ ማድረግ ነው፡፡ ይህም ከስማርት ሲቲ ምሰሶዎች አንዱ ከሆነው “ስማርት አስተዳደር” ጋር የሚያያዝ ሲሆን ተገቢውን ቴክኖሎጂ በመጠቀም ተገልጋዮች ቤታቸው ሆነው አገልግሎት እንዲያገኙ የማስቻል፣ ሰልፍን የመቀነስ፣ ከሰው ንክኪ ውጪ አገልግሎት በመስጠት ግልጽነትን የመፍጠርና ብልሹ አሰራርን የማስቀረት ዓላማ ያለው ነው፡፡

እንደ ሀገር የመንግስት አገልግሎትን ቀልጣፋ፣ ግልፅና ውጤታማ ለማድረግ ሰፋፊ ስራዎች እየተሰሩ ይገኛሉ፡፡ የመንግስት ተቋማትን ሪፎርም በማድረግ እና የመሶብ የአንድ ማዕከል አገልግሎትን በመጀመር አገልግሎትን ለማዘመን የሚደረገው ጥረትም ውጤት እያመጣ ሲሆን፣ ይህም ከዛሬ ጀምሮ ለሶስት ተከታታይ ቀናት የሚቆዩ ሁለት አህጉራዊና ዓለም አቀፍ ኹነቶች በአዲስ አበባ እንዲካሄዱ ምክንያት እንደሆነ የፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን ኮሚሽነር መኩሪያ ሀይሌ (ዶ/ር) ከትናንት በስቲያ በሰጡት መግለጫ ተናግረዋል፡፡

አንደኛው 10ኛው የአፍሪካ ሕብረት አባል ሀገራት የመንግሥት አገልግሎትና አስተዳደር ጉባኤ ሲሆን የመንግሥት ተቋማት ተለዋዋጭ ሁኔታዎችን ተቋቁመው እየተንከባለሉ የመጡ ፈተናዎችን መፍታት እንዲችሉ ልምድ መለዋወጥና መማማርን ዓላማው ያደረገ ነው፡፡ ሁለተኛው ደግሞ የተባበሩት መንግስታት የአፍሪካ ቀጣናዊ ፎረም ጉባኤ ነው፡፡

እንደ ሀገርም ሆነ እንደ አዲስ አበባ የመንግስት አገልግሎቶችን ለተገልጋዩ ማህበረሰብ ተደራሽ፣ ቀልጣፋና ውጤታማ ለማድረግ በተሰራው ስራ አበረታች የሚባሉ ለውጦች መምጣታቸው የሚካድ ባይሆንም አሁንም የአገልግሎት አሰጣጡ በሚፈለገው ደረጃ ላይ ይገኛል ማለት አይቻልም፡፡ ክብር ባለው፣ በተቀላጠፈና ግልፅነት በተሞላበት መንገድ አገልግሎት መስጠት ላይ ችግሮች ይስተዋላሉ፡፡

በአዲስ አበባ ከተማ የፐብሊክ ሰርቪስ እና ሰው ሀብት ልማት ቢሮ በቢሮ ኃላፊ ደረጃ የአገልግሎት አሰጣጥና አውትሶርሲንግ ዘርፍ ኃላፊ አቶ በቀለ ተመስገን ለዝግጅት ክፍላችን በሰጡት አስተያየት፣ በቅርብ ዓመታት የአገልግሎት አሰጣጡን ለማሻሻል በርካታ ስራዎች ተሰርተዋል፤ እየተሰሩም ይገኛሉ፡፡ በ2016 በጀት ዓመት በርካታ ተገልጋዮችን የሚያስተናግዱ፣ ምልልስ የሚበዛባቸው፣ ቅሬታ የሚቀርብባቸው 16 ተቋማት ተመርጠው ሪፎርም ተደርገዋል። የአሰራር ስርዓቶችን በማሻሻልና አዳዲስ አሰራሮችን በመዘርጋት፣ የቢሮዎችን አደረጃጀት በማስተካከል፣ ምቹ የስራ አካባቢ በመፍጠር እና ቴክኖሎጂዎችን በመጠቀም አገልግሎታቸውን ለማሻሻል እየተሰራ እንደሚገኝ ኃላፊው አብራርተዋል።

“ዓለም አሁን ከደረሰበት ደረጃ አኳያ ያለ ቴክኖሎጂ የአገልግሎት አሰጣጡን ማሻሻል የማይታሰብ ነው፡፡” የሚሉት አቶ በቀለ፣ ብልሹ አሰራር፣ ሌብነት፣ ጉቦና የመሳሰሉ ችግሮች የሚቀረፉት አገልግሎቶችን በቴክኖሎጂ አስደግፎ መስጠት ሲቻል ነው። ከንክኪ ነፃ የሆነ፣ ተገልጋዩ በየትኛውም ቦታ ሆኖ በሲስተም አገልግሎት ማግኘት የሚቻልበት ሁኔታ ሲፈጠር ነው፡፡



ፎቶ ከፋይል

በአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለስልጣን አቃቂ ቃሊቲ ቅርንጫፍ ፅህፈት ቤት በቴክኖሎጂ በመታገዝ አገልግሎት ሲሰጥ

## በአዲስ አበባ የተለያዩ ተቋማት አገልግሎቶችን በአንድ ማዕከል መስጠት የሚቻልበትን “አዲስ መሶብ ዲጂታል የአንድ ማዕከል አገልግሎት”ን ለማስጀመር ተቋም የማደራጀት ስራ እየተሰራ ነው

ከዚህ አኳያ በአዲስ አበባ በርካታ አገልግሎቶች በቴክኖሎጂ ተደግፈው እየተሰጡ ነው፡፡ ለአብነትም የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለስልጣን፣ የሲቪል ምዝገባና የነዋሪዎች አገልግሎት ኤጀንሲ፣ ገቢዎች ቢሮ፣ የመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ፣ የንግድ ቢሮና ሌሎችንም መጥቀስ ይቻላል፡፡ በከተማዋ ከ300 በላይ የሚሆኑ አገልግሎቶች በቴክኖሎጂ ተደግፈው እየተሰጡ ይገኛሉ ሲሉ ተናግረዋል፡፡

ኃላፊው እንደገለጹት፣ አገልግሎቶችን በቴክኖሎጂ አስደግፎ ለመስጠት ሲታቀድ አንደኛው ፋይዳ ወጪ ቆጣቢ አገልግሎት ለመስጠት ነው፡፡ ቴክኖሎጂ በመምጣቱ ለወረቀት ይወጣ የነበረውን ወጪ ማስቀረት ተችሏል፡፡

ተገልጋዮች አገልግሎት ለማግኘት ወደ ተቋማት በአካል ሲመጡ የሚወስድባቸው ጊዜና የሚያወጡት ገንዘብ አለ፡፡ የፋይል ፍለጋው፣ ወረፋና ሌሎችም ችግሮች ነበሩ። ቴክኖሎጂን በመጠቀም በሚሰጠው አገልግሎት በርካታ ውጤቶች እየተገኙ ነው። ተገልጋዮች ጊዜና ገንዘባቸውን መቆጠብ፣ በተቀላጠፈና ስታንዳርዱን በጠበቀ መልኩ አገልግሎት እንዲያገኙ አስችሏል፡፡ አንዳንድ ቀናት፣ ሳምንታትና ከዚያም በላይ ይወስዱ የነበሩ አገልግሎቶች በደቂቃዎች መስጠት የሚቻልበት ሁኔታ ተፈጥሯል፡፡

ሁሉንም አገልግሎቶች በቴክኖሎጂ አስደግፎ መስጠት የሚቻልበትን ሁኔታ ለመፍጠር እየተሰራ እንደሆነ ያነሱት አቶ በቀለ፣ በፌዴራል ደረጃ የመንግስትን አገልግሎት ቀልጣፋና ግልጽ ማድረግ የሚያስችል የመሶብ የአንድ ማዕከል አገልግሎት ተጀምሯል፡፡ በአዲስ አበባም የተለያዩ ተቋማት አገልግሎቶችን በአንድ ማዕከል መስጠት የሚቻልበትን “አዲስ መሶብ ዲጂታል የአንድ ማዕከል አገልግሎት”ን ለማስጀመር ተቋም የማደራጀት ስራ እየተሰራ ነው፡፡ ተቋሙ አንድ ዋና መስሪያ ቤት ኖሮት በተለያዩ አካባቢዎች ቅርንጫፎች ሊኖሩ ይችላሉ፡፡

ወደ ማዕከሉ የሚገቡት በዲጂታል ቴክኖሎጂ በመታገዝ አገልግሎት እየሰጡ ያሉ ተቋማት ናቸው፡፡ 13 ተቋማት እና የክፍያ ስርዓቱን የሚያሳልጡ ባንኮችና የቴሌኮም አገልግሎቶችን ጨምሮ ወደ አንድ ማዕከል እንዲገቡ በማድረግ ሰዎች ሳይጉላሉ ሁሉንም አገልግሎት ማግኘት የሚያስችል መሆኑን አቶ በቀለ ያብራራሉ፡፡

በማዕከሉም የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለስልጣን፣ የሲቪል ምዝገባና የነዋሪዎች አገልግሎት ኤጀንሲን፣ ገቢዎች ቢሮን፣ መሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮን፣ ንግድ ቢሮን፣ ስራና ክህሎት ቢሮን ጨምሮ የ13 ተቋማት አገልግሎቶች በቴክኖሎጂ ተሳስረው አገልግሎት ይሰጣሉ።

የአዲስ መሶብ አገልግሎትን ለመጀመር ከቴክኖሎጂ ዝግጅት አኳያም ከኢትዮጵያ አርቲፊሻል ኢንተለጀንስ ኢንስቲትዩት፣ ከአዲስ አበባ ኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ልማት ቢሮ፣ ከኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር እና ከኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር ጋር በቅንጅት እየተሰራ ነው፡፡ አዲስ አበባ የአፍሪካ የመንግስት አገልግሎትና አስተዳደር ጉባኤን እንድታስተናግድ የተመረጠችበት አንዱ ምክንያት በከተማ የመንግስት አገልግሎትን ሪፎርም በማድረግና በቴክኖሎጂ በመታገዝ የምትሰጠው አገልግሎት ለሌሎችም ተሞክሮ ይሆናል በሚል መሆኑን አቶ በቀለ ተናግረዋል፡፡

አቶ ዮናስ ደምሰው በአዲስ አበባ የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ልማት ቢሮ የስማርት ሲቲ ዘርፍ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ስታንዳርድ ዝግጅትና ሬጉላቶሪ ቡድን መሪ ናቸው፡፡ የአዲስ መሶብ ዲጂታል የአንድ ማዕከል አገልግሎትን ለማስጀመር በአንድ ማዕከል የሚሰጡ አገልግሎቶችን የመለየት፣ አገልግሎቱን የሚሰጡ አገልጋዮችን፣ የስራ ዝርዝርና የአሰራር ስርዓቶችን፣ቴክኖሎጂዎችን የመለየትና ግብአት የማሟላት እንዲሁም የግንባታ ስራዎች እየተሰሩ እንደሆነ ይናገራሉ፡፡

በኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ልማት ቢሮ በኩል ቡድን ተቋቁሞ እየተሰራ ሲሆን ወደ አዲስ መሶብ አንድ ማዕከል አገልግሎት የሚገቡ ተቋማት አገልግሎታቸው በቴክኖሎጂ የተደገፈ መሆኑን፣ ቴክኖሎጂዎችና መሰረተ ልማት ላይ መዘግየት እንዳይኖር እንዲሁም የደህንነት፣ ትስስርና ሌሎች ጉዳዮች ላይ ፍተሻ እየተደረገና ለአገልግሎት ብቁ መሆናቸውን የማረጋገጥ ስራ እየተሰራ ነው፡፡ ስራውንም ከተለያዩ ተቋማት ጋር በመቀናጀት፣ የተለያየ ቢሮና የዘርፍ ኃላፊዎች ክትትል እያደረጉበት እንዲሁም ኢንጂነሮችና የኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ ባለሙያዎች ተካትተውበት እየተሰራ ነው። የወረፋ ማስጠበቂያ ስርዓት፣ ገፀ-ድርና ሌሎች አገልግሎቶችንም ዝግጁ የማድረግ ስራ አብሮ እየተሰራ እንደሆነ አቶ ዮናስ ጠቁመዋል፡፡

ከዚህ ባሻገር በቴክኖሎጂ በመታገዝ በሚሰጡ አገልግሎቶች ላይ በተገልጋዩ የኔትዎርክ መቆራረጥ ችግር እንደሚታይ ላነሳንላቸው ጥያቄ አቶ በቀለ ሲመልሱ፣ ከቴክኖሎጂ ጋር በተያያዘ ሁለት ችግሮች ይታያሉ፡፡ አንደኛ ከኔትዎርክ አቅም ማነስ ጋር በተያያዘ የአገልግሎት መቆራረጥ ነው፡፡ ሁለተኛው ቴክኖሎጂን የመጠቀም ክህሎት ክፍተት በተገልጋዩ ብቻም ሳይሆን በአገልጋዩም ጭምር መስተዋሉ ነው፡፡ ይህንን ከህዝብ የሚነሳውን ችግር ለመፍታት የኔትዎርኮችን አቅም ለማሳደግ ከኢትዮ-ቴሌኮምና ከአዲስ አበባ የቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን ልማት ቢሮ ጋር በጋራ እየተሰራ እንደሚገኝ ጠቁመዋል፡፡

ከቴክኖሎጂ አጠቃቀም ጋር በተያያዘ ያሉ ችግሮችን ለማቃለል ለሰራተኞችና ተገልጋዩ ስልጠናና የግንዛቤ ማስጨበጫ ትምህርት እየተሰጠ ነው፡፡ አንዳንድ እንደ የመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ ያሉ ተቋማት ዩቲዩብ፣ ቴሌግራምና ቲክቶክ በመክፈት ማህበረሰቡ የቴክኖሎጂ አጠቃቀም ግንዛቤውን ለማሳደግ እየሰሩ ነው፡፡

በአገልግሎት አሰጣጣችን የህዝብ እርካታ ለማረጋገጥ ብዙ መስራት ይጠበቅብናል ያሉት አቶ በቀለ በበኩላቸው፣ ለዚህም ተገልጋዩን በክብርና በፈገግታ ከመቀበል መጀመር አለበት፡፡ ተገልጋዩ “የማገለግለው ቤተሰቤን ነው፤ ህዝብን በማገልገሌ እድለኛ ነኝ” የሚል አመለካከት ሊኖረው ይገባል። ከዚህ ባሻገር ተቋማትን በአሰራርና አደረጃጀት የማዘመን፣ ምቹ የስራ አካባቢ መፍጠርና ሌሎች ስራዎች ተጠናክረው እንደሚቀጥሉ ጠቁመዋል፡፡

# የበጎነት ፍሬ

## “በንፁህ የመኖሪያ አካባቢ እየኖርን ነው”

**በበጎ ፈቃድ ቤት የተገነባላቸው ወይዘሮ ሻሼ ሸኖ**

**በስንታየሁ ምትኩ**

በአዲስ አበባ የበጎ ፈቃደኝነት አገልግሎት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየሰፋ፣ እየጎለበተና እያበበ መጥቷል፡፡ በርካቶች በበጎ ፈቃደኝነት ጊዜ፣ ጉልበትና ገንዘባቸውን በመስጠት የወገናቸውን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች እያቃለሉ ይገኛሉ፡፡

ከአንድ ሳምንት በፊትም ተጠባቂው የ2017 ዓ.ም የክረምት የበጎ ፈቃድ አገልግሎት መርሃ ግብር የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ ወ/ሮ አዳነች አቤቤ በተገኙበት በይፋ ተጀምሯል፡፡ ከንቲባዋ በወቅቱ እንደተናገሩት ባለፉት የለውጥ ዓመታት በአዲስ አበባ በጎ ፈቃደኝነት ተቋማዊ እንዲሆን ተደርጎ በመሰራቱ በርካታ የዘመሙ ጎጆዎች፣ ጠያቂ የሌላቸው እናቶች፣ አባቶች፣ የሀገር ባለውለታዎች ቀና እንዲሉ ያደረጉ፣ የሚሊዮኖችን እንባ ያበሱ ስራዎች ተከናውነዋል፡፡ በጎ ፈቃደኝነት የአንድ ወቅት ስራ ብቻ ሳይሆን የሁልጊዜ ተግባር፣ በትውልዱ ዘንድ ባህል እንዲሆን መሰረት ተጥሏል፡፡

የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ከቀየራቸው የከተማዋ አካባቢዎች በአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ ከፓስተር አደባባይ ዝቅ ብሎ የሚገኘው “ገብስ ሜዳ” እየተባለ የሚጠራው አንዱ ነው፡፡ የተፋፈጉ፣ ከእንጨት፣ አፈርና ቆርቆሮ የተሰሩ፣ አንዳንድ ቦታ ፕላስቲክ የተወጠረባቸው፣ የጣሪያቸውን ቆርቆሮ ነፋስ እንዳይወስደው ከላይ ድንጋይ የተጫነባቸው … መኖሪያ ቤቶች ያሉበት ሆኖ ቆይቷል፡፡ በዋናነት ቆሎ በመሸጥ የሚተዳደሩት ነዋሪዎቹ፣ ገብስ እየፈተጉና እየቆሉ ሲያዘጋጁ ከቤት እየተንቦለቦለ የሚወጣው ጭስ በራሳቸው ደህንነትና ጤና ላይ አደጋ የሚያስከትል እንደነበር ነዋሪዎቹ በአንደበታቸው ይመሰክራሉ፡፡

ወይዘሮ ሻሼ ሸኖ ከሰላሳ ዓመታት በላይ በአካባቢው ኖረዋል፤ ወልደው፣ ልጅ አሳድገዋል፡፡ አራት ልጆችን ጨምሮ ስድስት የቤተሰብ አባላት አላቸው፡፡ ልክ እንደ አብዛኛው የሰፈሩ ነዋሪዎች ገብስ እየፈተጉ፣ ቆሎ ቆልተው እየሸጡ ነበር ኑሯቸውን ሲመሩ የቆዩት፡፡

ቤታቸው “ኑሮ ካሉት መቃብር ይሞቃል” እንደሚባለው አቅም ስለሌላቸው ችለው ኖሩበት እንጂ ብዙ ችግሮች ያሉበት እንደነበር ወይዘሮ ሻሼ አልሸሸጉም፡፡ “ቤታችን ቆሻሻ ነው፤ ከስራው ባህርይ አኳያ ልብሳችንም የቆሸሸ ነበር፤ አቧራ አለ፡፡ በአንድ መፀዳጃ ቤት እስከ ስድስት ቤተሰብ ነበር በጋራ የምንጠቀመው፡፡ ማዕድ ቤቱም ከቤት ውጭ ሆኖ ሁለት ምድጃ ተሰርቶ በርካታ ሰው እየተጋፋ በጋራ የሚጠቀምበት ነበር። በክረምት ወቅት ዝናብ ሲዘንብ የሚፈጠረው ጎርፍም በቤቱ አካባቢ ስለሚሄድ ‘አንድ ቀን ቤት ይገባል” በሚል ይሳቀቁ እንደነበር ይናገራሉ፡፡

ሌላኛዋ የሰፈሩ ነዋሪ ወይዘሮ ፀሐይነሽ ጫላ ይባላሉ፡፡ እሳቸውም በአስተያየታቸው ለበርካታ ዓመታት ይኖሩበት የነበረው መኖሪያ ቤት ለዘመናዊ አኗኗር የማይመች እንደነበር ያስታውሳሉ፡፡ “በፊት የነበረው የመፀዳጃ ቤት ሁኔታ የሚወራ ነገር አይደለም።” የሚሉት ወይዘሮ ፀሐይነሽ፣ በአንድ ግቢ ውስጥ በርካታ ቤተሰብ በአንድ መፀዳጃ ቤት ወረፋ እየጠበቅን ነበር የምንጠቀመው፡፡ ማዕድ ቤትም ቢሆን በጋራ ነበር የምንጠቀመው፤ ከስራውም ባህርይ፣ ከቤቱ እርጅና ጋር ተያይዞ መኖሪያ ቤታችን የተጎሳቆለ ነበር። የእሳት አደጋም በተለያዩ ጊዜያት ያጋጥም እንደነበርና እሳቱን ለማጥፋትም የአደጋ መውጫና መግቢያ እንዳልነበር አንስተውልናል፡፡

በገብስ ሰፈር የነበሩ መኖሪያ ቤቶች ያረጁ፣ ንጽህና የጎደላቸው፣ ለዘመናዊ አኗኗር የማይመቹ እንደነበሩ እነ ወይዘሮ ሻሼ ብቻ ሳይሆኑ በርካታ የአካባቢው ማህበረሰብ ይመሰክራል። ነዋሪዎቹ ኑሯቸው ከእጅ ወደ አፍ የሚባል በመሆኑ የዘመመውን ጎጆቸውን ለማቃናት አቅም አልነበራቸውም። ለበርካታ ዓመታት ተዘንግተው የቆዩ፣ ያረጁና የተፋፈጉ መኖሪያ ቤቶች ሲኖሩ የነበሩ ነዋሪዎች በከተማ አስተዳደሩና ልበ ቀና በጎ ፈቃደኞች ትብብር ፈርሶ፣ መንገድ፣ የህፃናት መጫዎቻና ማቆያ፣ ዘመናዊ የመጸዳጃና የማብሰያ ቦታዎች፣ እንዲሁም የጋራ መገልገያ ስፍራዎች ያካተቱ ዘመናዊ ህንፃዎች ተገንብተው ተላልፈዋል፡፡ ሰፈሩም በጎነት ቁጥር 3 የመኖሪያ መንደር ተብሏል፡፡

ደሳሳው ቤታቸው ፈርሶ፣ ውብና ዘመናዊ፣ የተለያዩ አገልግሎቶችን ባሟላ መልኩ ተገንብቶ ተጠቃሚ በመሆናቸው ነዋሪዎች ደስተኞች ናቸው፡፡ ከነበሩበት ህይወት እንዲወጡ ቤቶችን በመገንባት ከፍተኛ ድጋፍ ላደረገው የከተማ አስተዳደሩ ከፍ ያለ ምስጋና ያቀርባሉ። ወይዘሮ ሻሼ በዘመናዊው ባለአምስት ወለል የበጎነት ቁጥር 3 መንደር ላይ ባለአንድ መኝታ ቤት ተሰጥቷቸዋል። የራሳቸውን ማዕድ ቤት፣ መኝታ ቤት እና መፀዳጃ ቤት አግኝተዋል፡፡ “አሁን ጤናችን ተጠብቆ፣ በንፁህ መኖሪያ አካባቢ እየኖርን ነው። አዲስ አበባን አሁን ነው ያየናት፤ በፊት ከተማ እየኖርን ነው እንላለን እንጂ ከገጠር አይሻልም ነበር። ከዚህ በኋላ ‘ተመስገን’ እያልን ነው የምንኖረው፡፡ ለዚህ እንድንበቃ ላደረጉት ከንቲባ አዳነች አቤቤ ምስጋና አቀርባለሁ” ብለዋል፡፡

አዲሱ ቤት ሲገነባ ሰባራ ሳንቲም ሳያወጡ በከተማ አስተዳደሩና በጎ ፈቃደኞች ትብብር እንደተሰራላቸው የሚናገሩት ወይዘሮ ፀሀይነሽ፣ “ከአፈር ቤት ወጥቼ ጽዱና ሁሉንም አገልግሎት ያሟላ ቤት ውስጥ እየኖርኩ ነው፤ ተመስገን ከማለት ውጪ የምለው የለኝም” ሲሉ ነው የተሰማቸውን የደስታ ስሜት በቃላት ለመግለፅ እንደሚቸገሩ የተናገሩት፡፡

በአዲስ አበባ ባለሀብቶችን፣ ነዋሪዎችን፣ ተቋማትና የተለያዩ አካላትን በማሳተፍ የሚሰራው የበጎነት ተግባር በቤት ግንባታና እድሳት ላይ ብቻ የተወሰነ አይደለም፡፡ መንገድ ላይ ዜጎች የትራፊክ አደጋ ሰለባ እንዳይሆኑ በማስተናበር፣ በሆስፒታሎች ህሙማንን በመርዳት፣ ማዕድ በማጋራት፣ በአረንጓዴ አሻራ ችግኝ በመትከልና በሌሎች መስኮች በርካታ ዜጎች በበጎ ፈቃደኝነት በመሳተፍ የከተማዋን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግር በማቃለል ከፍተኛ ሚና እየተጫወቱ ይገኛሉ፡፡

በመንገድ ትራፊክ ማስተናበር ተሳትፎ እያደረጉ ካሉ ወጣቶች መካከል በጉለሌ ክፍለ ከተማ ሽጎሌ እየተባለ በሚጠራው አካባቢ ነዋሪ የሆነው ወጣት አበበ ጣሰው አንዱ ነው፡፡ ወጣቱ በትራፊክ ማስተናበር ላይ በበጎ ፈቃደኝነት እንዲሳተፍ ምክንያት የሆነው በአንድ ወቅት በሚኖርበት ሰፈር ዳቦ ከሱቅ ለመግዛት መንገድ ሲያቋርጥ የነበረ ወጣት በመኪና ተገጭቶ ጉዳት ሲደርስበት መመልከቱ ነበር፡፡ በወቅቱ ልጁ ህክምና እንዲያገኝ ከማገዝ ባሻገር “በአካባቢው መንገድ ላይ የሚያስተናብር ቢኖር አደጋ አይደርስም ነበር” በሚል ቁጭት ከሰፈር ጓደኞቹ ጋር በበጎ ፈቃደኝነት መሳተፍ እንደጀመረ ይናገራል፡፡

ላለፉት ሰባት ዓመታትም በመንገድ ትራፊክ ማስተናበር እያገለገለ ይገኛል። የግል ስራውን በጠዋቱ ካከናወነ በኋላ ከቀኑ ከዘጠኝ ሰዓት ጀምሮ፤ ከሰኞ እስከ ቅዳሜ በቋሚነት ይሰራል፡፡

“ስራው የሰውን ነፍስ ማዳን ነው። በበጎ ፈቃድ በመሳተፌ ትልቅ እርካታ ነው የማገኘው፡፡ ከስራው ስቀር ደስታ ይርቀኛል፤ በጎ ፈቃደኝነት ሱስ ነው።” ሲልም በበጎ ፈቃደኝነት መሳተፉ ስለሚፈጥርለት ስሜት ይናገራል። አንዳንዶች የገንዘብ ድጋፍና ጥቅም አግኝተን የምንሰራ ይመስላቸዋል፡፡ ነገር ግን አረጋውያን፣ አይነ ስውራን፣ አካል ጉዳተኞች፣ ህፃናት ያለ ስጋት ከትራፊክ አደጋ ተጠብቀው እንዲንቀሳቀሱ በነፃ ነው የምናገለግለው፡፡ ህብረተሰቡ ልጆቻቸው ወደ ትምህርት ቤት ሲሄዱና ሲመለሱ አደጋ እንዳይደርስባቸው አደራ ጥሎብናል፡፡ በምንሰጠው አገልግሎትም ደስተኛ ነው፤ ያበረታታናልም ይላል ወጣት አበበ፡፡

ወጣት አበበ በጉለሌ ክፍለ ከተማ መድኃኒዓለም ትምህርት ቤት አካባቢ በሚገኘው መንገድ ላይ ነው የትራፊክ ማስተናበር ስራውን የሚያከናውነው፡፡ አካባቢው ትምህርት ቤቶች፣ የመንግስት ተቋማትና የተለያዩ የንግድ ስራዎች ያሉበት፣ ከፍተኛ የትራፊክ እንቅስቃሴ የሚስተዋልበት ነው፡፡

በጎ ፈቃድ የሰዎችን ችግር ከመቅረፍ ባሻገር ራሳችንንም ሆነ ቤተሰባችንን የመንገድ አጠቃቀም ላይ ያለውን ግንዛቤ በማሳደግ ከትራፊክ አደጋ እንዲጠበቁ ለማድረግ ያስችላል፡፡ በሀገራችን ለሰዎች ህይወት መጥፋት ምክንያት ከሆኑት መካከል የትራፊክ አደጋ በቀዳሚነት ይጠቀሳል፡፡ ሁሉም ሰው በየአካባቢው፣ በሰፈሩ መኪና እና ተሽከርካሪ ባለበት አካባቢ ሁሉ የራሱን እገዛ ቢያደርግ የብዙ ሰው ህይወት ማትረፍ እንደሚቻልም ወጣቱ ያስገነዝባል፡፡

የመንገድ ትራፊክ አስተናባሪ በጎ ፈቃደኞች ህብረተሰቡ በተለይ ህፃናት፣ አረጋውያንና አካል ጉዳተኞች ደህንነታቸው ተጠብቆ መንገዶችን እንዲሻገሩ በማስቻል እያደረጉት ያለው ድጋፍ ቀላል ዋጋ ያለው እንዳልሆነ የአካባቢው ነዋሪ አቶ አዲሱ ተፈራ ይመሰክራሉ፡፡ “እኔም ልጅ አለኝ፡፡ ልጆች ወደ ትምህርት ቤት ሲሄዱና ሲመለሱ የትራፊክ አደጋ እንዳይደርስባቸው ተጠብቀው በጥንቃቄ እንዲሻገሩ ከሚያደርጉት መልካምነት ሁሉም ሊማር ይገባል፡፡” ሲሉ አስተያየታቸውን ሰጥተዋል።

### በጎ ፈቃድ ባህል እንዲሆን ምን እየተሰራ ነው?

አቶ ቢኒያም ጊቻ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የህብረተሰብ ተሳትፎና በጎ ፈቃድ ማስተባበሪያ ኮሚሽን የበጎ ፈቃድ ግንዛቤ ማስረፅ ቡድን መሪ ናቸው፡፡ ባለፉት አስር ወራት በአዲስ አበባ በበጎ ፈቃድ ሰፋፊ ስራዎች ተከናውነዋል፡፡ የከተማ አስተዳደሩ፣ ልበ ቀና ባለሀብቶች፣ በጎ ፈቃደኞች፣ የግልና የመንግስት ተቋማት የበጎ ፈቃድ አገልግሎትን የስራቸው አካል አድርገው በሰሩት ስራ ውጤታማ መሆን እንደተቻለ ያስረዳሉ፡፡

አዲስ አበባ ከሌሎች የኢትዮጵያ አካባቢዎች በተሻለ የበጎ ፈቃድ ስራ እየተከናወነባት ያለች ከተማ ናት የሚሉት አቶ ቢኒያም፣ በጎ ፈቃድ ባህል እንዲሆን የሚሰራው ስራ ግንዛቤ ከማስረፅ ይጀምራል፡፡ ከዚህ አንፃር መገናኛ ብዙሃንን በመጠቀም፣ መድረኮችን፣ የፓናል ውይይቶችን በማዘጋጀት፣ የተሰሩ ስራዎችን በማስተዋወቅ፣ ዓለም አቀፍ የበጎ ፈቃድ ቀንን በማክበርና የተለያዩ ኹነቶችን በመጠቀም ከ285 ሺህ በላይ የህብረተሰብ ክፍሎችን መድረስ ተችሏል፡፡ በከተማዋ በሚገኙ

ወደ ገጽ 17 ዞሯል



ፎቶ በመባጽዮን ሀ/ገብርኤል

በበጎ ፈቃድ ቤት የተገነባላቸው ወይዘሮ ሻሼ ሸኖ

# ማዕከላቱ ከዓላማቸው አንጻር ሲመዘኑ

**በሄለን ጥላሁን**

"ወጣት የነብር ጣት" ይባላል በተለምዶ፡፡ የዚህ ምክንያቱ ነብር ራሱን ለመከላከልም ሆነ አድኖ ለመብላት ከሚጠቀምባቸው የሰውነት ክፍሎች ዋነኛው ጣቱ ነው፡፡ ወጣትም ለአንድ ሀገር ሁለንተናዊ እንቅስቃሴ አይተኬ ሚና የሚጫወት ሃይል እንደመሆኑ መጠን ከዚህ ጋር እንዲዛመድ ተደርጎል፡፡

ይህ የህብረተሰብ ክፍል ሚናው አውንታዊ እንዲሆን ካስፈለገ ሰብዕናውን ሊገነቡ፣ ጊዜውን አልባሌ ቦታ እንዳያሳልፍ የሚያደርጉ ስራዎች መሰራት አለበት፡፡ አዲስ አበባ በተለያዩ አካባቢዎች የወጣት ሰብዕና መገንቢያ ማዕከላት የመገንባቷ ምክንያትም ከዚህ መነሻነት መሆኑን መናገር "ለቀባሪ ማርዳት" ነው የሚሆነው። ማዕከላቱ ምን ያህል ለታለመላቸው ዓላማ እየዋሉ ነው? የሚለው ግን ሊነሳ የሚገባው መሰረታዊ ጉዳይ ነው፡፡ ወቅቱ ከበጋው በተሻለ ወጣቱ የመዝናኛ ጊዜ የሚያገኝበት መሆኑ ደግሞ በዚህ ጽሑፍ እነዚህን ማዕከላት እንድንቃኝ ወጣቶችም በጉዳዩ ዙሪያ ሀሳባቸውን እንዲያጋሩን ወደድን፡፡

ወጣት አቤል መስፍን ይባላል፡፡ በተለምዶ ሳንሱሲ ተብሎ በሚጠራው አካባቢ ነዋሪ ነው፡፡ በአንድ የግል ድርጅት ተቀጥሮ በመስራት ላይ ይገኛል። እንደ ወጣቱ ገለጻ፣ ባለው የእረፍት ጊዜ ወደ አዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ ወረዳ 14 የወጣቶች ሰብዕና መገንቢያ ማዕከል በማቅናት የጅምናዚየም እንዲሁም የፑል ጨዋታ አገልግሎት ይጠቀማል፡፡ ከዚህ ቀደም የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራ ባለመኖሩ ምክንያት ጊዜውን በአልባሌ ቦታዎች ያሳልፍ ነበር፡፡ በተለይም የስራ እረፍት በሚኖረው ሰዓት ጊዜ ለማሳለፍ በሚል ለሱስ ተጋላጭ በሚያደርጉ ተግባራት ተጠምዶ እንዳሳለፈ፣ "የት መሄድ እንዳለብኝ፣ ከማን ጋር የእረፍት ጊዜ ማሳለፍ እንደሚገባኝ ባለማወቁ ምክንያት ጫት በመቃም እንዲሁም ሲጋራ በማጨስ ጊዜዬን አሳልፍ ነበር። ዘግይቼም ቢሆን እየሄድኩበት ያለው መንገድ እንደማያዋጣኝ በመረዳት ወዲያው ውሳኔ በመወሰን ከሱስ ነፃ ለመሆን ችያለሁ፡፡" ሲል አብራርቷል፡፡

ከሱስ እና ከአልባሌ ተግባራት መራቅ ብቻውን መፍትሔ እንዳልሆነ የሚናገረው ወጣት አቤል፤ ጤናማ ብሎም ማህበራዊ መስተጋብሮቻችንን በሚያጠናክሩ ተግባራት ላይ ትኩረት ማድረግ አስፈላጊ መሆኑን ያምናል፡፡ ይህንንም ወደ ተግባር በመለወጥ በወጣት ማዕከል የጅምናዚየም ስፖርት በቋሚነት ይሰራል፡፡ በዚህም በጤናው፣ በአካል እና በመንፈስ ጥንካሬው ላይ ትልቅ ለውጥ እንዲያመጣ እንዳገዘው ከልምዱ ይመሰክራል፡፡ "ፑል ለመጫወት ስመጣ ከማገኛቸው ወጣቶች ጋር ጥሩ ማህበራዊ ግንኙነት ለመፍጠር ችያለሁም" ብሏል፡፡

ከሱስ እንዲወጣ፣ በአካል እና በመንፈስ እንዲጠነክር፣ ማህበራዊ መስተጋብሩን እንዲያሻሽል ትልቅ እገዛ ያደረገለት ማዕከሉ፤ ለእርሱ እና ለመሰል ወጣቶች



ፎቶ በመባጽዮን ሀ/ገብርኤል

በወጣት ማዕከላት ከሚሰጡ አገልግሎቶች በከፊል

የሚሰጠውን አገልግሎት በተሟላ መልኩ እንዳይሰጥ የተለያዩ ችግሮች አንቀው እንደያዙት ወጣት አቤል አልሸሸገም። እንደ እርሱ ገለፃ ከሆነ፤ የመብራት መቆራረጥ እንዲሁም የሻወር አገልግሎት በሚፈለገው ልክ አለመኖር ወደ ሰብዕና መገንቢያ ማዕከል የመምጣት ልምዱን ከጊዜ ወደ ጊዜ እንዲቀንስ ካደረጉት ምክንያቶች መካከል ተጠቃሽ ናቸው። በተለይ ቅዳሜ እና እሁድ መብራት ለረጅም ሰዓታት ይጠፋል። እንደ ኤሮቢክስ ያሉ ስፖርቶችን ለመስራት መብራት አስፈላጊ ነው፡፡ ክፍሎቹም ሲጨልሙ ለመስራት ያለን ፍላጎት ይጠፋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በማዕከሉ የኳስ ሜዳ ቢኖር ለወጣቶች ጥሩ ጊዜ ማሳለፊያ ይፈጥርላቸዋል ሲል ቢታይ ያላቸውን ነገሮች አብራርቷል፡፡

ወጣት እመቤት የሺጥላም የወረዳው ነዋሪ ናት፡፡ የስምንተኛ ክፍል ተማሪ ስትሆን ወደ ወረዳው የወጣቶች ሰብዕና መገንቢያ ማዕከል በማቅናት መጽሐፍትን እንደምታነብ ገልጻልናለች፡፡ ሆኖም ቤተ መጻሕፍቱ ሁልጊዜ ክፍት አለመሆኑ፣ የማንበቢያ ክፍሉ ለማንበብ የማይመችና የማይጋብዝ መሆኑ፣ በመጽሐፍት መልክ (ሀርድ ኮፒ) ተዘጋጅተው የማይገኙ አንዳንድ መጽሐፍትን ከተለያዩ ገጸ ድሮች ለማንበብ የሚያስችል የኢንተርኔት አገልግሎት በቤተ መጻሕፍቱ አለመኖሩና በሌሎች ምክንያቶች ምርጫዋ እንደማታደርገው ገልጻልናለች፡፡ በቀጣይ ቤተ መጻሕፍቱ እነዚህን ችግሮች በመቅረፍ፣ የሚሰጡ አገልግሎቶችን በማሻሻል መጪውን የክረምት ጊዜ እውቀታችንን የምናሳድግበትና ጥሩ የትምህርት ዝግጅት የምናደርግበት እንዲሆን የሚመለከታቸው የመንግስት አካላት ትኩረት ይስጡት ስትልም አጽንዖት ሰጥታ ተናግራለች፡፡

ለብዙ ወጣቶች ሰብዕና መገንቢያነት እንዲውል ተደርጎ በተገነባው ማዕከል ላይ የሚታዩ ጉድለቶችን ለማረም እና በተጠቃሚዎች ዘንድ የሚነሱ ቅሬታዎችን ለመፍታት ጉዳዩ የሚመለከተው አካል ምን እየሠራ እንደሆነ ጠይቀናል፡፡ በዚህ ጉዳይ ላይ ምላሻቸውን ያጋሩን በአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ ወረዳ 14 የወጣቶች ሰብዕና መገንቢያ ማዕከል የወጣቶች አቅም ማጎልበት ቡድን መሪ ወይዘሮ በላይነሽ ተሰማ ናቸው፡፡ እንደ እሳቸው ገለጻ፤ በወጣት ማዕከሉ የተለያዩ ስፖርታዊ የመዝናኛ ጨዋታዎች፣ የአዳራሽ አገልግሎት፣ የካፍቴሪያ አገልግሎት፣ የጂምናዚየም እና መሰል አገልግሎቶች እየተሰጡ ይገኛል፡፡ በበጀት ዓመቱ ዘጠኝ ወራትም 6 ሺህ 50 የሚሆኑ ወጣቶች የአገልግሎቱ ተጠቃሚ ሆነዋል፡፡

ማዕከሉ የሚሰጣቸውን አገልግሎቶች በሚፈለገው ልክ ለወጣቶች ተደራሽ ለማድረግ ያሉ ውስንነቶችን ወ/ሮ በላይነሽ ሲያብራሩ፣ "አንዳንድ ጊዜ ወቅታዊ ጉዳዮች ሲገጥሙ የወረዳ አመራሮች በራሳቸው ፍቃድ የስብሰባ አዳራሹን የመጠቀም ነገር አለ፡፡ በተቻለ መጠን የቤተ መጻሕፉቱን የማንበቢያ ክፍልን ሳቢ በሆነ አግባብ በማደራጀት ወጣቱን ተጠቃሚ ለማድረግ እንሰራለን፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ዲጂታል ቤተ መጻሕፍት እንዲሆን የሚመለከታቸው አካላት የበኩላቸውን አስተዋጽኦ ቢያደርጉ ጥሩ ነው" ብለዋል፡፡

አክለውም፤ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ አገልግሎት በመሰረታዊ የኮምፒዩተር ስልጠና በተደራጀ አግባብ አገልግሎት እየሰጠ አይደለም፡፡ ለዚህም እንደ ምክንያት ያነሱት የኤሌክትሪክ ሃይል መቆራረጥ እና የሲስተም ችግር ነው። ለመፍትሔውም ከሚመለከተው አካል ጋር በመነጋገር ላይ እንደሚገኙም ተናግረዋል፡፡

በመዲናዋ ያሉ የወጣቶች ሰብዕና መገንቢያ ማዕከላት እየሰጡ ስላለው አገልግሎት ለመመልከት ሌላኛው ቅኝት ያደረግንበት በጉለሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 4 ቁጥር 2 የወጣቶች የሰብዕና መገንቢያ ማዕከል ነው፡፡ የ10ኛ ክፍል ተማሪ የሆነው ወጣት ቃለአብ ገረመውን፤ በዲጂታል ቤተ መጻሕፍት ውስጥ ሲያነብ አግኝተን በሰጠን አስተያየት፤ "ከዚህ ቀደም እንዲህ አይነት ቤተ መጻሕፍት ይኖራል ብዬ አላስብም ነበር፡፡ አሁን ግን በመኖሪያ አካባቢዬ ይህን መሰሉ አገልግሎት መሰጠቱ ትልቅ እፎይታን ፈጥሮልኛል፡፡ በቤተ መጻሕፍት ውስጥ ነፃ የኢንተርኔት አገልግሎት ስላለ

ወደ ገጽ 17 ዞሯል

## ምን ልርዳዎ?

### የኤሌክትሮኒክስ ደረሰኝ አጠቃቀም እና ፈቃድ አሰጣጥ

**በታክስ ደረሰኝ አጠቃቀም እና አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 149/2011 መሠረት**

1. በሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ መጠቀም የማይችል ታክስ ከፋይ የታክስ ባለስልጣኑን በማስፈቀድ የኤሌክትሮኒክስ ደረሰኝ መጠቀም ይችላል፡
2. የኤሌክትሮኒክስ ደረሰኝ መጠቀም የሚፈልግ ታክስ ከፋይ በሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ መጠቀም የማይችልበትን አሳማኝ ምክንያት ገልጾ ጥያቄውን ታክስ ለሚከፍልበት የታክስ ባለስልጣን በጽሑፍ ማቅረብ አለበት፡፡
3. በተራ ቁጥር (2) በተገለጸው መሠረት የቀረበው ጥያቄ ተቀባይነት ሲያገኝ የታክስ ባለስልጣኑ ታክስ ከፋዩን የኮምፒዩተር ፕሮግራም ሶፍትዌሩን የሰራውን ሰው ስም፣ የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥር እና ህጋዊ የንግድ ስራ ፈቃድ እንዲያቀርብ በማድረግ ጥያቄው በቀረበ በ10 ቀናት ውስጥ ውሳኔውን በጽሑፍ መግለጽ ይኖርበታል፡፡
4. ታክስ ከፋዩ በኤሌክትሮኒክስ ደረሰኝ ለመጠቀም ፈቃድ የሚሰጠው፡
   ሀ) የሚያቀርበው ሶፍትዌር በኮምፒዩተር ፕሮግራም አማካኝነት የሚታተመው ደረሰኝ ቢያንስ ከላይ ከተጠቀሰው መመሪያ ጋር በተያያዘው ደረሰኝ ናሙና ላይ የተመለከቱትን መረጃዎች የሚይዝ ሆኖ ሲገኝ፣ እና
   ለ) ለታክስ መረጃ ጥቅም ላይ የሚውል መረጃ እንደማይቀየር ለማረጋገጥ እና ተከታታይ የሆነ የደረሰኝ ቁጥር ለማተም በሚያስችል አኳኋን የተዘጋጀ የኮምፒውተር ፕሮግራም መሆኑ ሲረጋገጥ ብቻ ነው፡፡

**ምንጭ፡-** ገቢዎች ሚኒስቴር

**ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍትህ ቢሮ ጋር በመተባበር ዘወትር ቅዳሜ የሚቀርብ**

# የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በምሽት የንግድ እና የትራንስፖርት አገልግሎት እንዲሰጥ ለማድረግ የወጣ ደንብ 185/2017

**ኤሚሊያ ፍሬድሪክ (ዐቃቤ ሕግ)**

## መግቢያ

በዓለማችን የስራ ሰዓት በቁጥር የተገደበ አይደለም፡፡ አብዛኛው የምዕራባውያን እና የአውሮፓ ሀገራት የስራ ሰዓታቸውን በሰራተኛው አቅም ልክ ገድበውታል፡፡ ይህንንም ስንል ሰራተኛው እስካልደከመው ድረስ በቀን ከ16 እስከ 21 ሰዓት መስራት እንደሚቻል እንገነዘባለን፡፡ የምዕራባውያን የስራ ባህልን በምንመለከትበት ጊዜ በአንድ ጊዜ ከሁለት እና ከሦስት ስራ በላይ መስራት የሚቻልባቸው መንገዶች እንዳሉ እና በዚህም በኢኮኖሚ ጥሩ ደረጃ ለመድረሳቸው እንደ ምክንያት ለመጥቀስ የሚቻል ነው፡፡ በዚህ መልኩ የስራ ባህላቸውን ወደ ሀገራችን ስናመጣው ከስራ አጥነት አኳያ እና ስራውም ቢገኝ በአንድ ጊዜ ሁለት እና ሦስት ስራዎችን ለመስራት የማይቻልባቸው ብዙ ያልተመቻቹ ነገሮች አሉ፡፡ ከስራ ባህል ጋር ተያይዞ ብዙ ነገሮችን ማንሳት እንችላለን።



በባህል እና በኃይማኖት የታነፀ ሀገር እንደመሆኑ መጠን አንዳንድ የስራ ቀኖችን ከኃይማኖት በዓላት ጋር በማያያዝ ስራ የማይሰራባቸው ቀናት በዓመት ውስጥ በርካቶች ናቸው፡፡ በኃይማኖት ክብረ በዓላት ላይ ስራ መስራት እንደ ሀጥያት የሚቆጥሩ የማህበረሰብ ክፍሎች ብዙ የሚባሉ ናቸው፡፡ በዚህም መሰረት ያለንን የስራ ሰዓት በቀን ከ8 እስከ 10 ሰዓት በሳምንት እስከ 39 እና 41 ሰዓታት ብቻ ወስነን የምንንቀሳቀስ ከሆነ ለሀገር የኢኮኖሚ እድገት እራሱ የሚያሳድረው ተፅእኖ ቀላል የማይባል አይደለም። በዚህም መሰረት እንደ ደንብ ቁጥር 185/2017 ያሉ ደንቦች መውጣቱ ብዙ ጠቀሜታ ያለው እና የስራ ባህላችንንም በምዕራባውያን ልክ እንዲሆን እንደ መነሻ ሊሆን የሚያስችል ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በምሽት ብዙ የንግድ ቦታዎች ስለሚዘጉ አገልግሎት ለማግኘት እና ለንግድ እራሱ ተወዳዳሪነትን የሚቀንስ ነው፡፡ ከዚህም ጋር ተያይዞ ኢትዮጵያ ብሎም ዋና ከተማዋ አዲስ አበባን አሁን ካለችበት የእድገት ጎዳና አንፃር ከተማዋን ለመጎብኘት የሚመጡ ብዙ ቱሪስቶችም እንዳሉ ሆነው በምሽት ብዙ አገልግሎቶችን ለማግኘት የሚቸገሩበት ሁኔታ ስለሚፈጠር ከዚህም አንፃር የሚነሳውን ችግር ለመቅረፍ እንደ ቁልፍ መነሻ አድርገን ልንይዘው እንችላለን፡፡

በዚህ መሰረት ደንብ ቁጥር 185/2017 አስፈላጊነት ስንመለከት በከተማዋ በስፋት እየተከናወነ የሚገኘው መሠረተ-ልማት በኢኮኖሚው ላይ የሚያመጣውን መነቃቃት አጠናክሮ እንዲቀጥል ለማስቻል ነው፡፡ ሌላው የደንቡ አስፈላጊነት ደንቡ የሥራ ባህልን ይበልጥ በማዳበር ከሌሎች ካደጉ ሀገራት ተርታ እንድትሰለፍ በማድረግ የኢኮኖሚ እድገትን ለማፋጠን፣ የከተማዋን ተወዳዳሪነት እውን ለማድረግ፣ ቀን ከሚሰጠው አገልግሎት በተጨማሪ በምሽት የንግድ እና አገልግሎት መስጫ ተቋማት አገልግሎት የሚሰጡበት ምቹ ሁኔታ ለመፍጠር ነው፡፡

በከተማዋ መንገድ ዳር ያሉ የንግድ ቤቶች እና አገልግሎት መስጫ ተቋማት የሚያበሯቸው ስታንዳርዳቸውን የጠበቁ መብራቶች የአካባቢውን ውበት ይበልጥ የሚያደምቁ እና ሠላምና ፀጥታ ለማረጋገጥ አጋዥ በመሆናቸው ህብረተሰቡ ለመዝናናትና እረፍት ለማድረግ የሚያዘወትራቸው ተመራጭ ቦታዎች እንዲሆኑ ለማድረግ እና የንግድና የሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት ተቋማት በምሽት ተግባራቸውን ማከናወን የሚችሉበትን የአሰራር ሥርዓት በህግ መደንገግ በማስፈለጉ ነው፡፡

የደንቡን ተፈፃሚነት በምንመለከትበት ጊዜ በከተማው መንገድ ዳር በሚገኙ የንግድ ተቋማት ወይም ሌሎች አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ላይ እና የሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡ በዚህም መሰረት በደንብ ቁጥር 185/2017 መሰረት ከሥራ ባህሪያቸው አኳያ 24 ሰዓት አገልግሎት የሚሰጡ የንግድ ወይም አገልግሎት ሰጪ ተቋማትን አይመለከትም፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ግን ማንኛውም የንግድ ተቋም ማታ ከምሽቱ 12 ሰዓት እስከ ምሽቱ 3፡30 ድረስ የንግድ ተቋሙን ለተገልጋይ ክፍት በማድረግ አገልግሎት መስጠት አለበት። በምሽት ክፍለ ጊዜ ንግድ ተቋሙን ክፍት ሲያደርግ በቀኑ ክፍለ ጊዜ ሲቀርብ የነበረውን አገልግሎት ወይም ምርት በተሟላ ሁኔታ በምሽት ክፍለ ጊዜም ለተገልጋይ ማቅረብ አለበት፡፡

በዚህም መሰረት ለምሳሌ፡- በአገልግሎት ሰጪ ተቋማት ውስጥ አገልግሎት የሚሰጡ ሰራተኞችን በምሽት ከስራ በሚወጡበት ጊዜ ከትራንስፖርት አኳያ የሚገጥሙ ችግሮችን ከአገልግሎት ጋር አብረው እንዲሄዱ እና አገልግሎቱ እንዳይስተጓጎል፤ የትራንስፖርት አገልግሎትም በምሽት እስከ 4 ሰዓት ድረስ መስጠት እንዳለበት ተመላክቷል፡፡ ነገር ግን የሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት የሚሰጥ ማንኛውም ሰው በቀን ክፍለ ጊዜ በሚከፈለው ታሪፍ አገልግሎት መስጠት አለበት፡፡ ማንኛውም የአገልግሎት ሰጪ ተቋም የንግድ ተቋም እና በመንገድ ዳር ላይ የሚገኝ የመኖሪያ ቤት አግባብ ያለው የከተማው አስፈጻሚ አካል ባወጣው የመብራት ስታንዳርድ መሰረት የሕንጻ የፊተኛው ገጽ መብራት ወይም የፋሳድ ላይት መብራት ከምሽቱ 12 ሰዓት ጀምሮ እስከ ንጋቱ 12 ሰዓት ድረስ ማብራት አለበት፡፡ ከዚህ ድንጋጌ ጋር ተያይዞ በደንቡ የወጡ ክልከላዎች አሉ። ክልከላዎቹን ተላልፈው በሚገኙ የአገልግሎት ሰጪ ተቋም የትራንስፖርት አገልግሎት ላይ ከፅሑፍ ማስጠንቀቂያ ከመስጠት ጀምሮ እስከ አስተዳደራዊ እርምጃዎችም የሚወሰድ በተደጋጋሚ ጥፋቱን የሚፈፅም ከሆነ ደግሞ የገንዘብ መጠኑን እየተጨመረ እንደሚቀጣ እና በዚህም የማይታረም ከሆነ ደግሞ የንግድ ፈቃድ ማገድ እና መሰረዝ የሚደርስ እርምጃዎችን እንደሚወሰድ በደንቡ ላይ ተገልፆ እናገኘዋለን፡፡

ከንግድ ተቋም ጋር ተያይዞ የተቀመጡትን ክልከላዎች እና አስተዳደራዊ እርምጃዎችን በምንመለከትበት ጊዜ ከምሽቱ 3፡30 ሰዓት በፊት የንግድ ተቋሙን መዝጋት 10 ሺህ ብር የገንዘብ መቀጮ፤ ለተገልጋይ ሊያቀርብ የሚችለው አገልግሎት ወይም ምርት እያለው የለም በማለት ተገልጋይ እንዳይስተናገድ ማድረግ 10 ሺህ ብር የገንዘብ መቀጮ፤ መንገድ ዳር ያሉ ንግድ ተቋማት እና አገልግሎት መስጫ ተቋማት ከምሽት እስከ ንጋት ድረስ የተቋሙን የውጭ እና የውስጥ መብራት አለማብራት 7 ሺህ ብር የገንዘብ መቀጮ፤ የሕንጻ የፊተኛው ገጽ መብራት ወይም የፋሳድ ላይት መብራት ያለመስቀል እና/ወይም ያለማብራት 5 ሺህ ብር የገንዘብ መቀጮ፤ የንግድ ተቋሙ መግቢያ በር ዝግ ሆኖ አገልግሎት የሚሰጥ ከሆነ ክፍት መሆኑን የሚያመለክት በኤሌክትሪክ የሚሰራ ምልክት ያለማድረግ የ5 ሺህ ብር የገንዘብ መቀጮ፤ ከምሽቱ 4 ሰዓት በፊት የትራንስፖርት አገልግሎት ማቋረጥ ወይም ከስምሪት መውጣት ወይም የስምሪትን መስመር ማቆራረጥ የ5 ሺ ብር የገንዘብ መቀጮ፤ የከተማ አስተዳደሩ ካወጣው የትራንስፖርት አገልግሎት ታሪፊ በላይ ተሳፋሪውን ማስከፈል የ5 ሺ ብር የገንዘብ መቀጮ እንደሚቀጣ ደንቡ ይገልፃል፡፡

አስተዳደራዊ የገንዘብ ቅጣት የተጣለበት ማንኛውም ሰው የተሰጠውን አስተዳደራዊ ቅጣት ማስታወቂያ ወረቀት በመያዝ ወዲያውኑ ጥፋቱ በተፈፀመበት አካባቢ በሚገኘው የወረዳ ንግድ ጽህፈት ቤት ወይም ትራንስፖርት ቢሮ ቀርቦ ወይም በኤሌክትሮኒክስ መክፈያ ዘዴ በሶስት ተከታታይ የሥራ ቀናት ውስጥ ገንዘቡን ገቢ በማድረግ ቅጣቱን መፈጸም አለበት ይህንን ያላደረገ ሰው የተጣለበትን የቅጣት ገንዘብ መጠን እጥፍ እንዲከፍል እንደሚደረግ ደንብ ቁጥር 185/2017 ይገልፃል፡፡ ይህንን ለማድረግ ፈቃደኛ ያልሆነ ማንኛውም ሰው ላይ ክስ እንዲቀርብ የንግድ ቢሮው ወይም የትራንስፖርት ቢሮው ለከተማው አስተዳደር ፍትህ ቢሮ ማስረጃውን አደራጅቶ ይልካል፡፡ በቢሮው ወይም የትራንስፖርት ቢሮ በሚሰጠው አስተዳደራዊ ውሳኔ ቅሬታ ያለው ማንኛውም ሰው ቅሬታውን ውሳኔውን ለሰጠው አስፈጻሚ አካል ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ማቅረብ ይችላል፡፡ በዚህም ውሳኔ ቅር የተሰኘ ማንኛውም ሰው ስልጣን ላለው ፍርድ ቤት አቤቱታ ማቅረብ እንደሚችል በደንቡ የተካተቱ ነጥቦች ናቸው፡፡ በዚህ መሰረት ይህንን ደንብ ከማውጣት አንፃር ብዙ ጥቅሞች ያሉት መሆኑን በደንቡ ላይ በተካተቱት ነጥቦች መመልከት እንችላለን፡፡

በመጨረሻም ዓለም በደረሰችበት የእድገት ጎዳና አብሮ ለመሰለፍ እና የሀገራችንን ኢኮኖሚ ለማሳደግ ቁልፍ ሚናን የሚጫወት ነው፡፡

# የጥበባዊ ዝግጅቶች ጥቁምታ

በጊዜው አማረ

ባለፉት ቀናት በመዲናችን የተለያዩ ኪነ-ጥበባዊ ዝግጅቶች እና አዳዲስ ኪነ-ጥበባዊ ስራዎችን ለጥበብ አፍቃሪያን ሲደርሱ ቆይተዋል፡፡ ዛሬን ጨምሮ በሚቀጥሉት ቀናትም መሰል ዝግጅቶች ተሰናድተዋል፡፡ ከእነዚህ መካከል የስዕል አውደ ርዕይ፣ የመጽሐፍት መረጃዎች፣ የቴአትር መርሃ ግብር ይገኙበታል። ለመረጃ ይሆንዎት ዘንድ የዝግጅት ክፍላችን እንደሚከተለው አዘጋጅቷል፡፡

## መጽሐፍት

“መባያ” መጽሐፍ ለንባብ ሊበቃ ነው።ጋዜጠኛ ሙሉጌታ ጌቱ ከተለያዩ አንጋፋ ፀሐፍት የቀነጨባቸውን ስራዎች ከራሱ ሥራዎች ጋር በማጣመር ያሰናዳው አዲስ መጽሐፍ በቅርቡ ለንባብ እንደሚበቃ ተገልጿል፡፡ መጽሐፉ በቅደመ ህትመት ሽያጭ ገበያ ላይ የዋለ ሲሆን በቅርቡ በአንባቢያን እጅ እንደሚደርስ ተነግሯል።

በሌላ መረጃ “መንታ ነፍስ” የግጥም መድብል ለንባብ በቅቷል፡፡ የመድብሉ ደራሲ መላከ ማሩ ሲሆን፣ ህይወት፣ ፍቅር፣ ማህበራዊ ጉዳይና ሌሎችንም ሀሳቦቹንና አስተውሎቶቹን በአጠቃላይ የሰው ልጅ ኑረት ላይ የሚያጠነጥኑ ስራዎችን አካትቶባቸዋል ተብሏል፡፡

እንዲሁም የወዳጄነህ መሐረነ (ዶ/ር) መጽሐፍ ለንባብ ሊበቃ መሆኑ ተነግሯል። በወዳጄነህ “101 የጥበብ ጠብታዎች” የተሰኘ ርዕስ የተሰጠው አዲስ መጽሐፍ ከሰሞኑ ለንባብ ሊበቃ እንደሆነ ተሰምቷል። ወዳጄነህ (ዶ/ር) ከዚህ ቀደም ከሶስት በላይ መጻሕፍትን ለንባብ አብቅቷል፡፡

በሌላ ዜና “መኮንን ሽገኔ የሀገር ባለውለታ” የተሰኘው መጽሐፍ ዛሬ ተመርቆ ለንባብ እንደሚበቃ ተገልጿል። መጽሐፉ የተዘጋጀው በጋዜጠኛ እዝራ እጅጉ ሲሆን አራት ኪሎ ኢክላስ ህንጻ በሚገኘው ዋልያ መጽሐፍት መደብር አዳራሽ ተመርቆ ለንባብ ይበቃል። በኦሮሚያ ክልል በባሌ የተወለዱት መኮንን ሽገኔ በመምህርነት ሙያ ሀገራቸውን ያገለገሉና እውቅናን ያተረፉ ሰው ናቸው፡፡




ፎቶ- ከገፀ ድር

ከመዲናዋ ኪነ ጥበባዊ ዝግጅቶች በጥቂቱ

## የኪነ-ጥበብ ውይይት

“አውደ ፋጎስ” የኪነ-ጥበብ የውይይት መድረክ ነገ ይካሄዳል፡፡ ውይይቱ በአሁኑ ጊዜ 62ኛው ዙር ላይ ደርሷል። እንደ ኤቨንት አዲስ ዘገባ በዚህኛው ገጣሚ ውብአረጋ አድምጥ “አገባባዊ ድጋሞ በጋሽ ሰይፉ መታፈሪያ ግጥሞች እና ነገረ ባይራ” በሚል ርዕስ መነሻ ሀሳብ ያቀርባል። ይህ ውይይት ከቀኑ 8:00 ሰዓት ጀምሮ በብሔራዊ ቤተመዛግብት እና ቤተ መጻሕፍት አግልግሎት (ወመዘክር) አዳራሽ ውስጥ ይካሄዳል።

## ስእል

በእይታ ላይ የሚገኘው “የተሸመኑ ትውስታዎች” የሥዕል አውደ ርዕይ ሊጠናቀቅ አራት ቀናት ቀርተውታል፡፡ በወጣቱ ሠዓሊ ብርሃኑ ማናዬ የተዘጋጁ ሥዕሎች የቀረቡበት የሥዕል አውደ ርዕዩ ከባለፈው ግንቦት 2 ቀን 2017 ዓ.ም ጀምሮ በኢትዮጵያ ፖስታ ዋና መስሪያ ቤት ውስጥ በሚገኘው “The Space Ethiopia” የሥዕል ማሳያ ውስጥ ለእይታ እየበቃ ይገኛል። በዳግም አበበ አጋፋሪነት የተዘጋጀው ይህ አውደ ርዕይ የተለያዩ የስዕል አቀራረቦችን እንዲሁም በተለያዩ የአሳሳል ዘይቤ የተሰሩ የስዕል አይነቶችን ያካተተ ሲሆን ሰኔ 18 ቀን 2017 ዓ.ም ይጠናቀቃል፡፡

## ቴአትር

በመዲናችን አዲስ አበባ ቅዳሜ እና እሁድ ከሚታዩ ቴአትሮች ውስጥ የሚከተሉት ይገኙበታል፡፡ የቅርብ ሩቅ የተሰኘው ቴአትር በልዩ ሁኔታ ቅዳሜ 8:30 ሰዓት እንዲሁም 11፡30 ሰዓት ባሎችና ሚስቶች የተሰኘው ቴአትር በብሔራዊ ቴአትር ይታያሉ፡፡ እሁድ በ8፡00 ሰዓት 12ቱ እንግዶች ቴአትር የሚታይ ሲሆን እምዩ ብረቷ የተሰኘው ቴአትር ደግሞ በብሔራዊ ቴአትር 11፡30 ሰዓት ላይ ይታያል፡፡ በቀጣይ ቀናት በብሔራዊ ቴአትር ከሚታዩት መካከል ማክሰኞ በ11፡30 ሰዓት ሶስቱ አይጦች፣ ረዕቡ በ11፡30 ሰዓት የቅርብ ሩቅ፣ ሐሙስ ቀን 11:30 ሰዓት ሽምጋይ፣ አርብ በ11፡30 ሰዓት የሕይወት ታሪክ የተሰኙ ቴአትሮች ይገኙበታል፡፡

# የቁጥር ጨዋታ

## የባለፈው ሳምንት ጥያቄ መልስ

ውድ የአዲስ ልሳን ጋዜጣ አንባቢዎቻችን ባለፈው ሳምንት የቁጥር ጨዋታ አቅርበንላችሁ ነበር፡፡ የጥያቄው ትክክለኛ አሰራርና መልስ የሚከተለውን ይመስላል፡፡ የመጀመሪያው ክብ 9 x 7= 63 ይሆናል፡፡ 63 ሲገለበጥ 36 ይሆናል፡፡ በተመሳሳይ 3 x 21 = 63 ሲሆን ውጤቱ ሲገለበጥ 36 ይሆናል፡፡ በዚህ አመክንዮ መሰረት የመጨረሻው ክብ 8 x 12 = 96 የዚህ ቁጥር ግልባጭ 69 ይሆናል፡፡ በተመሳሳይ 3 x 32 = 96 ነው፡፡ የ96 ግልባጭ 69 ይሆናል፡፡ ስለዚህ በጥያቄ ምልክቱ ቦታ ላይ መግባት ያለበት ትክክለኛ ቁጥር 69 ነው፡፡




## የዚህ ሳምንት የቁጥር ጨዋታ

ውድ አንባቢዎቻችን ከታች በምስሉ ላይ የቁጥር ጨዋታ አቅርበንላችኋል፡፡ በጥያቄ ምልክቱ ቦታ ላይ መግባት ያለበት ትክክለኛው ቁጥር ስንት ነው? በጥያቄው ራስዎን እየፈተኑ ይዝናኑ፡፡ የጥያቄውን መልስ በቀጣይ ሳምንት እትማችን ይዘን እንቀርባለን፡



# ጥበብና ተፈጥሮ የተወዳጁባቸው ስፍራዎች

**በጊዜው አማረ**

ጥበብና አካባቢ በብዙ መልኩ የተቆራኙ ናቸው:: ትስስራቸውም በብዙ አውድ ሊታይ ይችላል:: ከዚህ ውስጥ ከታሪክ እና ከአሁናዊ ነባራዊ ሁኔታ አንጻር ያለውን ትስስር በማሳያነት ማንሳት ይቻላል:: ምክንያቱም ጥበብ አንድ ማህበረሰብ ራሱን የሚገልጽበት ነው:: ኑሮውን የሚከትብበት እና የዛሬን ዘመን የሚገልጽበትም ነው። መኖሪያ አካባቢውን፣ ሰማዩን፣ ዝናቡን፣ ተራራውን፣ ወንዙን፣ ማህበራዊ እሴቱን፣ ሰርጉን ለቅሶውን፣ ደስታውን... የሚያንጸባርቅበት ነው:: የትናንት ትዝታውንም የሚያይበት ነው:: በዚህ ሁሉ አውድ ውስጥ ግን የጥበብና ተፈጥሮ ቁርጠኝነት ከትናንት እስከ ዛሬ ድረስ አብሮ ዘልቋል::



ፎቶ ከድረ ገጽ
በሀገራችን ከተፈጥሮ ጋር ከተዋደዱ የጥበብ ስራዎች መካከል በጥቂቱ

ጥበብ እና አካባቢው ረጅም እና የተሳሰረ ታሪክ አላቸው:: ኪነ ጥበብ አብዛኛውን ጊዜ ለአካባቢ ለውጦች ነጸብራቅ ሆኖ ያገለግላል። ጥበብ በተለይ በሰዎች እና በተፈጥሮ ዓለም መካከል ያለውን ግንኙነት በመዳሰስ፣ ፈጠራን በመጠቀም ግንዛቤን ለማስጨበጥ እና ለውጥን ለመፍጠር ያስችላል። ይህ የተፈጥሮ ቁሳቁሶችን መጠቀም፣ ተፈጥሮን አስመስሎ መስራት፣ አካባቢን ሳይጎዱ ጥበባዊ እሴት መጨመር፣ ከአካባቢው ጋር ትስስር መፍጠር ወይም የአካባቢን ችግሮች በተለያዩ የጥበብ ዘዴዎች መፍታትን ሊያካትት ይችላል ይላል ናሽናል ሙዚየም ኦፍ ኤዢያን አርትስ ገጸ-ድር በዘንድሮ የፈረንጆቹ 2025 ይፋ ባደረገው መረጃ።

የሰዎች ህይወት ሁልጊዜ ከአካባቢ ጋር የተያያዘ ነው:: "The Integration of Art in Relation to Nature, Culture and Expression" በሚል እ.ኤ.አ በ2024 የተሰራ አንድ ጥናት እንደሚያትተው፣ የተፈጥሮና የሰዎች እንዲሁም የአካባቢ እና የጥበበኞች ትስስር በብዙ መልኩ የተጋመደ ነው::

ተፈጥሮ ለአርቲስቶች የመነሳሳት ምንጭ ናት:: ሃሳባቸውን የሚያገኙት ከማህበረሰቡ፣ ከተፈጥሮና ከአካባቢው ነው:: ተፈጥሮ እና ጥበብ በጥልቀት የተሳሰረ ግንኙነት አላቸው የሚባለው ለዚሁ ነው። ይህ ግንኙነት በተለያዩ መንገዶች የሚገለጽ ሲሆን፤ አርቲስቶቹ በፈጠራቸው ውስጥ የተፈጥሮ ቁሳቁሶችን እና ንጥረ ነገሮችን በመጠቀም የተፈጥሮን ዓለም በስራቻው ውስጥ እንደ ዋና ጭብጥ እስከማሳየት ድረስ ይጓዛሉ። በተጨማሪም አካባቢ፣ ጥበባዊ አገላለጽን እና ፈጠራን ሊያበረታታ ይችላል:: ይህም በሰዎች እና በተፈጥሮ መካከል በሥነ ጥበብ ጥልቅ ግንኙነት እንዲኖር ያደርጋል።

ቢኒያም አበበ ሰዓሊ ነው:: በግሉና በጋራ በርካታ የስዕል አውደ ርዕዮችን አሳይቷል:: በአሁኑ ጊዜ በአዲስ አበባ ኮሪደር ፕሮጀክት ከሚሳተፉ ሰዓሊዎች መካከል አንዱ ነው:: ጉዳዩን አስመልክቶ በሰጠው አስተያየት፣ "ጥበብና ተፈጥሮ የተቆራኙ ናቸው የሚባለው ከውበት አንጻር ነው" ይላል:: በጥበብ ሲታገዝ ወይም ተፈጥሮ በጥበብ ሲገለጽ ደግሞ ሌላ ውበት ነው በማለት ያብራራል::

ጥበብ የሚሰሩ ባለሙያዎች ከተፈጥሮ የሚያገኙት ብዙ ነገር አለ:: ከተፈጥሮ ወይም ከአካባቢ አይተው፣ አካባቢውን ተመሳስሎ ተሰርቶ ሲቀርብ ደግሞ የሰው ልጅ ብዙ ይማርበታል::

ይህ ሲሆን ይላል ሰዓሊ ቢኒያም፣ "የትናንትና ኑሮና፣ መልካም አስተሳሰብን፣ ታሪክንና ማንነትን ለቀጣዩ ትውልድ ለማስተላለፍ ይረዳል:: ምክንያቱም ጥበብ የተፈጥሮ፣ የኪነ ጥበብና ሰው ትስስር ከሚገለጽባቸው መንገዶች መካከል ተጠቃሽ ነው::

ተፈጥሮና ሰው በብዙ የተቆራኙ ናቸው:: ይህም ለጥበብ እድገት በራሱ ሌላ መልክ እና ለዛ ነው:: ቢኒያም በአስተያየቱ፣ ተፈጥሮና ጥበብ ትልቅ ዝምድና እና ትስስር አላቸው:: ለምሳሌ፡ - በምስራቁ ዓለም በተፈጥሯዊ ቦታዎች ላይ ስዕሎችና ቅርጻ ቅርጾች ይሰራሉ:: ይህም ተፈጥሮን ራሱን ሳይረብሽ ውበት የሚጨምር ስራ ነው በማለት ይገልጻል::

ለምሳሌ በጫካ አካባቢ የወፍ ስዕልና ቅርጻ ቅርጽ፣ የእንስሳትን መልክና ውበት የሚገልጹ ጥበባዊ ስራዎችን መስራት ይቻላል:: በባህር አካባቢ በውሃ ውስጥ የሚኖሩ አካላትን ቅርጽ መስራት ይቻላል። ከፍጥረታት በተጨማሪም ታሪክን የሚገልጹ፣ ማንነትን የሚያንጸባርቁና የማህበረሰቡን ኑረት የሚያሳዩ የጥበብ ስራዎችን መስራት ይቻላል ይላል::

በእኛም ሀገር በተለይ በቅርብ ጊዜ ጥበብና ተፈጥሮን ማስተሳሰር እየተለመደ መጥቷል:: ለአብነትም የእንጦጦ ፓርክን መጥቀስ ይቻላል:: በአንድነት ፓርክ ውስጥም የአዕዋፋትና የእንስሳት ስዕሎችና ቅርጻ ቅርጾች በብዛት ይገኛሉ። ይህም ተፈጥሮና ጥበብን ከማገናኘት አንጻር ሊታይ የሚችል ነው::

"በሀገር ደረጃ ጥበብ ከጥንትም ነበር" የሚለው ሰዓሊ ቢኒያም፣ ግን በምን አይነት ሁኔታ ነበር የሚለው የሚታወቅ ነው በማለት ያብራራል:: ለአብነትም እንጦጦ የሥነ ጥበብ ማዕከል ራሱን የቻለ ትልቅ ማዕከል ሆኖ ከተፈጥሮ ጋር ተወዳጅቶ መሰራቱ ትልቅ ነገር ነው። ተፈጥሯዊ በሆነው የእንጦጦ አካባቢ እንደዚህ አይነት የጥበብ ማዕከል ከተፈጥሮ ጋር አስተሳስሮ መስራት ለሀገርም ሆነ ለጥበበኛው ያለው ሚና እጅግ ከፍተኛ ነው ሲልም ያክላል::

ሰዓሊው እንደሚለው እንጦጦ የሥነ ጥበብ ማዕከል የተሰራበት ቦታ፣ የአካባቢው ሁኔታ የታወቀ ነው። እንጦጦ ብቻውን ተፈጥሮ የሰራው ጥበብ ነው:: በዚህ ቦታ ደግሞ የሰዎች ሃሳብ ተጨምሮበት ሲሰራ ጥበብን በሌላ መንገድ የሚገልጥ ነው:: አካባቢና ጥበብ በሚገባ የተሳሰሩበት ነው ማለት ይቻላል።

ዓለማችን እየሄደችበት ያለው መንገድ በምድራችን ችግር እየፈጠረ ነው::

> **በአዲስ አበባ የኮሪደር ልማት ፕሮጀክትን ጨምሮ በእንጦጦ ፓርክ፣ አንድነት ፓርክ እና በተለያዩ አካባቢዎች በተሰሩ የመዝናኛ መዳረሻዎች ጥበብና ተፈጥሮን አወዳጅቶ የመስራት ልምድ በስፋት እየተስተዋለ ነው**

ደን ለማገዶ እና ለእርሻ መሬት ፍለጋ መጨፍጨፍ በስፋት ይስተዋላል:: ዛፍ በመቁረጥ ህንጻ መስራት በዓለም ላይ ይስተዋላል:: የከተሞች መስፋፋት ከተፈጥሮ ጋር ባለመተሳሰሩ የአየር ንብረት ለውጥ ትልቅ ስጋት ሲሆን ይታያል:: ግን ተፈጥሮ ባለበት ዛፍ ሳይቆረጥ፣ ተራራው ሳይናድ፣ ውሃው ሳይደርቅ ጥበብና ተፈጥሮን በማወዳጀት እሴት መጨመር ይቻላል:: የሰው ልጅም ከዚህ ተጠቃሚ መሆን ይችላል። የወደቀን እንጨት ወደ ጥበብ መቀየር፣ አካባቢነቱን ሳይለቅ መስራት ለታሪክም፣ ለህዝብም፣ ለጥበብም ትልቅ ሚና አለው።

ሰዓሊ ቢኒያም በአስተያየቱ፣ የሰው ልጅ እድገት የሚጀምረው ከሃሳብ ነው። ሃሳብ ደግሞ መጀመሪያ የሚነሳው አካባቢን ከመረዳትና ከመገንዘብ ነው:: ጥበበኛው ከአካባቢው እና ከተፈጥሮ ተምሮ ተፈጥሮን ያሳምራል:: ጥበብ ደግሞ አካባቢን ሳይጎዱ ጥሩ ነገር መስራት ነው። ይህን ጥሩ ነገር ሰዎች ሲያዩት መልካም ነገር ያስባሉ:: በጎ ነገርና ለትውልድ የሚሻገር ስራ ይሰራሉ:: አስተሳሰባቸው ጥሩ ይሆናል:: ተፈጥሮና አካባቢያቸውን ይጠብቃሉ:: ታሪካቸውን ለትውልድ ያስተላልፋሉ:: ተፈጥሮን እና አካባቢን ይጠብቃሉ:: በዚህ ሁሉ ውስጥ ደግሞ ጥበብ አይነተኛ ሚና አላት በማለት ያስረዳል::

ሊ ዳውን የተባሉ የዘርፉ ምሁር "Environmental Art: Sparking Change Through Awareness" በሚል ርዕስ እ.ኤ.አ በ2019 ለንባብ ባበቁት ጽሑፍ፣ በ1960ዎቹ ውስጥ እየጨመረ የመጣው የአካባቢ መራቆት ስጋት መፈጠሩን ተከትሎ አካባቢን የሚገልጽ ጥበብ (Environmental Art) በስፋት እየታወቀ መጣ:: በተጨማሪም በጥበብ አካባቢን መጠበቅ፣ መንከባበከብና ማልማት፣ የልማት ስራዎችን ከተፈጥሮ ጋር ማወዳጀት ያለውን ጠቀሜታ ማሳየት ምን ያህል አስፈላጊ እንደሆነ ግንዛቤ ለመፍጠር ጥበብ ትልቅ ድርሻ አለው። በብዙ ሀገራትም ተግባራዊ ተደርጓል::

በአዲስ አበባ የኮሪደር ልማት ፕሮጀክትን ጨምሮ በእንጦጦ ፓርክ፣ አንድነት ፓርክ እና በተለያዩ አካባቢዎች በተሰሩ የመዝናኛ መዳረሻዎች ጥበብና ተፈጥሮን አወዳጅቶ የመስራት ልምድ በስፋት እየተስተዋለ ነው::

ይህ በእርግጥም ለሀገርም ለጥበበኛውም ትልቅ እድል እንደሆነ ቢኒያም ያነሳል:: ነገር ግን ሰዓሊያን እና የጥበብ ባለሙያዎች እንደነዚህ ዓይነት እድሎች ሲኖሩ በአግባቡ መጠቀም አለባቸው:: አንዳንድ ባለሙያዎች ኃላፊነት በጎደለው መልኩ ጥራት የሌላቸው ጥበባዊ ስራዎችን ይሰራሉ:: ዘመን ተሻጋሪ ስራን መስራት አለባቸው። መንግስትም ጥበበኞችን በቀጥታ ማግኘት፣ የትኛው ባለሙያ ነው ጥሩ ስራ የሰራው የሚለውን በመገምገም በሀገር እድገት ውስጥ ጥበብ ትልቅ ሚና እንዲያበረክት ማድረግ አለበት ሲልም ያክላል::

ሰዓሊው ጥበብ ተፈጥሯዊ ቦታዎች ላይ ሲሰራ ቦታውን ያማከለ መሆን አለበት:: ፀሐይና ዝናብ ሲፈራረቅበት ለዘመናት ሳይበላሽና ሳይቀየር መቆየት አለበት ሲልም ባለሙያው አክሏል::

# ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ በልጆች ሲገለጽ

**በለይላ መሀመድ**

ልጆች በወርሃ መጋቢት 2003 ዓ.ም. ግንባታው የተጀመረው ታላቁ የኢትዮጵያ ሕዳሴ ግድብ ግንባታ ከትልልቅ የሀገሪቱ ብሔራዊ ፕሮጀክቶች መካከል ቀዳሚው እንደሆነ ታውቃላችሁ አይደል?

ታላቁ የኢትዮጵያ ሕዳሴ ግድብ ግንባታ በዓባይ ወንዝ ላይ በመገንባት ላይ ያለ የኃይል ማመንጫ ፕሮጀክት ነው፡፡ ግንባታው የሚካሄደው በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል በጉባ ወረዳ ነው፡፡

ይህ ግዙፍ ግድብ በኢትዮጵያ እየተከሰተ ያለውን የኃይል አቅርቦት እጥረት ለመፍታት ጉልህ ሚና አለው። ታዲያ ልጆች ይህ ግድብ ያለምንም የውጪ ሀገራት ድጋፍ በራስ አቅም ነው እየተሠራ ያለው፡፡ በዚህም መላው የኢትዮጵያ ህዝብ የግድቡ ግንባታ ከተጀመረበት ጊዜ አንስቶ እስከ አሁን ድረስ ያልተቋረጠ ድጋፍ እያደረገ ይገኛል።



የነገው ሀገር ተረካቢ ትውልድ ጭምር የተሳተፈበት ታላቁ የኢትዮጵያ ሕዳሴ ግድብ

ፎቶ- ከገፀ ድር

መንግስትም ህብረተሰቡን በማስ ተባበር፣ ባለሙያዎችን በማሰማራት እንዲሁም ክትትል እና ድጋፍ በማድረግ የግድቡን ግንባታ ሂደት አሁን ያለበት ደረጃ ላይ እንዲደርስ አድርጓል። በመጪው መስከረም ወር እንደሚጠናቀቅም ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ተናግረዋል። ይህን መነሻ በማድረግ ያነጋገርናቸው ልጆች ስለ ግድቡ ግንባታ ያላቸውን ሀሳብ እንደሚከተለው አጋርተውናል፡፡

በአብርሆት ቤተ መጻህፍት እያነበበ ያገኘነው ተማሪ ሚልክያስ ደረጀ፤ “ታላቁ የኢትዮጵያ ሕዳሴ ግድብ በኢትዮጵያ ካሉ ግድቦች ትልቁና የመጀመሪያው እንደሆነ ነው የምረዳው፡፡ ግድቡ ብዙ ጥቅሞችን ይሰጣል፡፡ ከሀገራችንም አልፎ ለጎረቤት ሀገራትም ጥቅም የሚሰጥ ነው፡፡ ኢትዮጵያ ለጎረቤት ሀገራት የኤሌክትሪክ ሀይል በመሸጥ ኢኮኖሚያዊ ጥቅም እንድታገኝ የሚያደርግም ነው። የሕዳሴ ግድቡ ተጠናቅቆ አገልግሎት ላይ እንዲውል በስልክ መልእክት (በኤስ ኤም ኤስ) የገንዘብ ተሳትፎ አድርጌያለሁ፡፡ በቀጣይም ግድቡ ድረስ በመሄድ መጎብኘት እፈልጋለሁ፡፡ ግድቡ እስኪጠናቀቅም ቦንድ በመግዛት እና በኤስ ኤም ኤስ መልእክት በመሳተፍ የድርሻየን ለመወጣት ጥረት አደርጋለሁ” በማለት ሃሳቡን አጋርቷል፡፡

የ7ኛ ክፍል ተማሪ የሆነችው ተማሪ ማክቤል አድማሱ፤ በዓባይ ወንዝ ላይ እየተገነባ ያለው ታላቁ የኢትዮጵያ ሕዳሴ ግድብ የእሷነቷ፣ የማንነቷ፣ የኢትዮጵያዊነቷ መገለጫ መሆኑን እንደሚከተለው ታስረዳለች፤ “በዓባይ ወንዝ ላይ እየተገነባ ያለው ታላቁ የኢትዮጵያ ሕዳሴ ግድብ በሀገሬ ኢትዮጵያ የሚገኝ ነው፡፡ ሲያልቅም የሚጠቅመው እኛን ነው፡፡ ግድቡ ብርሀን ነው ማለት ይቻላል፡፡ ከፍተኛ የኤሌክትሪክ ሀይል በማመንጨት ከኢትዮጵያ አልፎ ለሌሎች ሀገራት ሽያጭ የሚውል በመሆኑ ለሀገራችን እድገት አስተዋጽኦ ያደርጋል፡፡”

የ6ኛ ክፍል ተማሪ የሆነው አብርሀም መሰለ በተመሳሳይ፤ “ታላቁ የኢትዮጵያ ሕዳሴ ግደቡ ለኢትዮጵያ የጀርባ አጥንቷ ነው ብዬ አምናለሁ፡፡ በሌላ አገላለጽ የሀገራችን ዋልታ ነው፡፡ ተጠናቅቆ አገልግሎት ሲሰጥ ኢትዮጵያ ውስጥ እያስቸገረን ያለውን የመብራት መቆራረጥ ችግር ያስቀርልናል፡፡ ከዚህም ባለፈ ለጎረቤት ሀገራት በመሸጥ የኢኮኖሚ ገቢ እንድናገኝ ያደርገናል” ብሏል፡፡

የ7ኛ ክፍል ተማሪ የሆነችው አናቤል አድማሱ ደግሞ ስለታላቁ የኢትዮጵያ ሕዳሴ ግድብ ይህንን ብላለች፤ “ለኤሌክትሪክ ማመንጫነት እንደሚውል በትምህርት እና በተለያዩ ሚዲያዎች እሰማለሁ፡፡ ታላቁ የኢትዮጵያ ሕዳሴ ግድብ ሙሉ በሙሉ ተጠናቅቆ አገልግሎት ላይ ሲውል ከፍተኛ ኤሌክትሪክ ሀይል ምንጭ ሆኖ ያገለግላል። የሀገር ብልጽግና ያመጣል። እንዳደጉት ሀገራት በቂ የኤሌክትሪክ ሀይል አቅርቦት ሲኖረን የተለያዩ ነገሮችን ለመስራት ያስችለናል። በትምህርት ቤቴ በኩል ባገኘውት እድል ለግንባታው የበኩሌን ተሳትፎ አድርጌያለሁ፡፡”

ልጆች ታላቁ የኢትዮጵያ ሕዳሴ ግድብ ከኃይል ምንጭነቱ ባለፈም በቱሪዝም፣ በዓሳ ሀብት ልማት፣ በስራ እድል ፈጠራ እና መሰል መስኮች ያለው ጥቅም ዘርፈ ብዙ ነው፡፡ ግድቡ አሁን የደረሰበት ደረጃ ላይ መድረስ የቻለው ኢትዮጵያውያን በአንድነት በሁሉም መስክ እያደረጉ ባሉት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ነው፡፡ የግድቡ ግንባታ እስከሚጠናቀቅ ድረስም ድጋፉን መቀጠል ያስፈልጋል፡፡ እናንተም የነገ ሀገር ተረካቢዎች እያደረጋችሁት ያለውን ተሳትፎ አጠናክራችሁ በመቀጠል የድርሻችሁን እንደምትወጡ ተስፋ እናደርጋለን፡፡

## 5 ልዩነቶችን ፈልጉ





## እንቆቅልሽ

### ያለፈው ሳምንት ጥያቄ

**ወድቆ የማይሰበር ሞቶ የማይቀበር ቤተሰብ የሰጠኝ ወንበር**

**መልስ፦** ሐ. ስም

### የዚህ ሳምንት ጥያቄ

**ወደ ላይ የሚወጣ ግን የማይወርድ ምንድ ነው?**

ሀ. ጉም
ለ. እድሜ
ሐ. ተራራ

**ልጆች መልስ ይሆናል የምትሉትን በዌብ ሳይታችን አድርሱን፤ እኛም በተደጋጋሚ የመለሰውን እንሸልማለን፤ ስለዚህ ተሳተፉ፤ ተሸለሙ፡፡**

**ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመብራት አገልግሎት አስተዳደር ጋር በመተባበር ዘወትር ቅዳሜ በየሳምንቱ የሚቀርብ**

# የምሽት መልኳ የፈካው፤ የካ

**• ሌሊቱም ቀኑም ተመሳሳይ ሆኗል ሲሉ የመንገድ መብራቱ የተጠገነላቸው የክፍለ ከተማው ነዋሪዎች ገልጸዋል**

**በፋንታነሽ ተፈራ**

አዲስ አበባ መልኳ እየፈካ፣ ውበቷም እየተገለጠ ነው፡፡ የልማት እና የነዋሪዎቿን ፍላጎት ለመመለስ ካላት መሻት እንዲሁም አህጉራዊና ዓለም አቀፋዊ ኃላፊነቷን በሚመጥን መልኩ ለመገኘት የሚያስችሉ ዘርፈ ብዙ ስራዎች በመከናወን ላይ ናቸው። ለዚህ ደግሞ የምሽት እንቅስቃሴዎችም ጭምር የተሳለጡ እንዲሆኑ የሚያደርጉ የመንገድ መብራቶች በዘመናዊ መንገድ እንዲሰሩ በብልሽት ምክንያት አገልግሎት ያቋረጡትም መፍትሔ እንዲያገኙ እየተደረገ መሆኑ የተግባር አስረጂ ነው፡፡

ስራውን በባለቤትነት ይዞ እየከወነ ያለው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር መብራት አገልግሎት አስተዳደር ባለስልጣን ማህበረሰቡን የመንገድ መብራት ተጠቃሚ ለማድረግ አገልግሎት የማይሰጡ የመንገድ መብራቶችን በመጠገን ወደ ስራ እንዲገቡ እያደረገ ይገኛል፡፡

ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ ጥገና ካደረገባቸው ክፍለ ከተሞች መካከል በየካ ክፍለ ከተማ በተለምዶ ፈረንሳይ ለጋሲዮን እየተባለ የሚጠራው አካባቢ የሚገኘው ይጠቀሳል፡፡ በክፍለ ከተማው ወረዳ ሁለት ጉራራ ወጣት ማዕከል አካባቢ ነዋሪ የሆኑት አቶ አባይነህ ዝቄ ጉዳዩን አስመልክቶ በሰጡት አስተያየት፣ አካባቢው የመንገድ መብራት ፖሎች ቢኖሩትም አገልግሎት አይሰጡም ነበር። በጨለማ ውስጥ ነው የኖርነው፡፡ ይህም የሆነው በስርቆት እና በብልሽት ምክንያት አገልግሎት መስጠታቸውን በማቆማቸው ነው ይላሉ፡፡

የመንገድ መብራቶቹ አገልግሎት በማይሰጡበት ወቅት ጆሮ ጌጥ፣ የአንገት ሃብል፣ የጣት ቀለበት እንዲሁም የእጅ ሰዓት አድርጎና ቦርሳ ይዞ መውጣት አስቸጋሪ ነበር፡፡ “ሚስትና ልጆቻችን ብቻቸውን በምሽት ከታክሲ ወርደው መምጣት አይችሉም፡፡ እኔም ሆንኩ ጎረቤቶቼ እየወጣን ነበር የምንቀበላቸው” ሲሉ መውጣትና መግባት አስቸጋሪ ሆኖባቸው መቆየቱን ያስታውሳሉ፡፡

የመንገድ መብራቱ ተጠግኖ አገልግሎት መስጠት በመጀመሩ ከፍተኛ ደስታ ተሰምቶናል፡፡ ከድቅድቅ ጨለማ ወጥተን ወደ ብርሃን ተሸጋግረናል፡፡ ሌሊቱም ቀኑም ተመሳሳይ ሆኖልናልም ብለዋል፡፡

የአቶ አባይነህን ሃሳብ የሚጋሩት ሌላኛው የአካባቢው ነዋሪ አቶ ተስፋዬ አያሌው፣ “በአካባቢያችን የመንገድ መብራት የለም ነበር ማለት ይቻላል። ይህም በመሆኑ የተለያዩ የዝርፊያ፣ የስርቆት እንዲሁም የድብደባ ወንጀሎች ሲያጋጥሙ ነበር፡፡ ‘ስልክ እና ገንዘብ ተሰረቅን’ ብለው የሚያለቅሱ ሰዎችም ነበሩ” ሲሉ አንስተዋል፡፡



ፎቶ በመባጽዮን ሀ/ገብርኤል

ከአቦ እስከ ጉራራ ኪዳነ ምህረት ቤተ ክርስቲያን ተጠግኖ አገልግሎት እየሰጠ ያለው የመንገድ መብራት

በአሁኑ ወቅት የመንገድ መብራቱ ተጠግኖ አገልግሎት በመጀመሩ እነዚህ ችግሮች መፍትሔ አግኝተዋል፡፡ እኔን ጨምሮ ማንኛውም ሰው እንደፈለገ መንቀሳቀስ እንድንችል እድል ፈጥሮልናል ሲሉም አክለዋል፡፡

ከዚህ በፊት የመንገድ መብራቱ ተሰርቶ ብርሃን ማግኘታችንን ብቻ ነበር የምናውቀው የሚሉት ነዋሪዎቹ፣ መሰረተ ልማቱ ጉዳት እንዳይደርስበት መጠበቅ እንዳለብን ግንዛቤው አልነበረንም፤ ከዚህ በኋላ እንደ ራሳችን ንብረት መጠበቅ እንዳለብን ተረድተናል በማለት ኃላፊነታቸውን እንደሚወጡ ገልጸዋል፡፡

የየካ ክፍለ ከተማ ዋና ስራ አስኪያጅ አቶ መርክነህ ያዕቆብ በሰጡት ማብራሪያ፤ በክፍለ ከተማው ወረዳ አንድ፣ ሁለት፣ ሶስት እና አራት ያሉ የመንገድ መብራቶች በኬብሎች መሰረቅ፣ በአምፖሎች መቃጠል ምክንያት አገልግሎት አይሰጡም ነበር፡፡ በዚህ ምክንያትም አካባቢዎቹ በጨለማ ውስጥ እንደነበሩ ነግረውናል፡፡

“የመንገድ መብራቶቹ አገልግሎት ባለመስጠታቸው ምክንያት በአካባቢው ማህበረሰብ ላይ የሞባይል ስርቆት፣ ዝርፊያ እና ፆታዊ ትንኮሳዎች ይደርስ ነበር” ሲሉ ነዋሪዎቹ ያነሱትን ሀሳብ የሚያጠናክሩት ዋና ስራ አስኪያጁ፣ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመብራት አገልግሎት አስተዳደር ባለሥልጣን ጥገና ባለሙያዎች እና በማህበረሰቡ ተሳትፎ የመንገድ መብራቶቹ እንዲጠገኑና ብርሃን እንዲያገኙ መደረጉን አብራርተዋል፡፡

እንደ ዋና ስራ አስኪያጁ ገለጻ፣ የመንገድ መብራቶቹ ተጠግነው አገልግሎት መስጠት በመጀመራቸው ማህበረሰቡ እስከ ምሽቱ 4፡00 ሰዓት እንዲንቀሳቀስ፣ የሰላም ሰራዊት አባላት ስራቸውን በተቀላጠፈ መልኩ እንዲያከናውኑ፣ ነዋሪዎች ባሉባቸው አካባቢዎች ሱቆችና መዝናኛ ቦታዎች እንዲከፈቱ እድል ፈጥሯል፡፡

ማህበረሰቡ የዓመታት ጥያቄዎቹ መፍትሔ ስላገኙ ደስተኛ መሆኑን የገለፁት አቶ መርክነህ፤ የመንገድ መብራቶቹ ለክፍለ ከተማው ብቻ ሳይሆን ከተማዋ ለወጠነችው የመሰረተ ልማት ግንባታ ወሳኝ ናቸው ብለዋል፡፡

አቶ መርክነህ፤ “የካ ክፍለ ከተማ በሙሉ ከጨለማ መውጣት አለበት” በሚል በተለይ ለወንጀል ስጋት ተጋላጭ የሆኑ አካባቢዎች ብርሃን እንዲያገኙ ከባለስልጣን መስሪያ ቤቱ ጋር በቅንጅት ለመስራት እቅድ አለን፡፡ የመንገድ መብራቶቹ ተጠግነው ደስተኛ የሆነው ማህበረሰብም የመንገድ መብራቶቹ የጋራ ንብረት መሆናቸውን ተገንዝቦ ጥበቃ በማድረግና ጉዳት የሚያደርሱ አካላትን በመጠቆም ኃላፊነቱን እንዲወጣ አሳስበዋል፡፡

> **የመንገድ መብራቶቹ ተጠግነው አገልግሎት መስጠት በመጀመራቸው ማህበረሰቡ እስከ ምሽቱ 4፡00 ሰዓት እንዲንቀሳቀስ፣ የሰላም ሰራዊት አባላት በተቀላጠፈ መልኩ ስራቸውን እንዲያከናውኑ፣ ነዋሪዎች ባሉባቸው አካባቢዎች ሱቆችና መዝናኛ ቦታዎች እንዲከፈቱ እድል ፈጥሯል**

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመብራት አገልግሎት አስተዳደር ባለሥልጣን ኦፕሬሽንና ጥገና ዘርፍ የመንገድ መብራቶችን አገልግሎት የማይሰጡ በማለት ከአዲስ አበባ መንገዶች ባለስልጣን ቆጠራ አካሂዶ ይፋዊ ርክክብ ካደረገባቸው ክፍለ ከተሞች አንዱ የካ ክፍለ ከተማ እንደሆነ የዘርፉ ምክትል ዋና ዳይሬክተር ወይዘሮ እንከንየለሽ አለሙ ይናገራሉ፡፡

ምክትል ዋና ዳይሬክተሯ እንዳብራሩት፤ በክፍለ ከተማው ከስድስት ኪሎ እስከ ቃኘው ሻለቃ ድረስ በትራንስፎርመር ችግር፣ ከቃኘው ሻለቃ እስከ ጉራራ ኪዳነ ምህረት፣ ከኪዳነ ምህረት እስከ አቦ (አቡነ ገብረመንፈስ ቅዱስ) ቤተ ክርስቲያን፣ የሖንስ ፀበል፣ ጀርመንና ጣሊያን ኤምባሲ አካባቢዎች በኬብሎችና ብሬከሮች ስርቆት ምክንያት ለረጅም ጊዜ ጨለማ ሆነው ቆይተዋል፡፡

ጨለማን ተገን በማድረግ የሚከሰቱ ወንጀሎችን መቀነስ የሚቻለው መብራት በማብራት በመሆኑ፣ እነዚህ ቦታዎች በተለይም ደግሞ ከጉራራ ኪዳነ ምህረት እስከ አቦ ቤተ-ክርስቲያን ድረስ 640 ሜትር ኬብሎችን በመዘርጋት የመንገድ መብራቶቹ አገልግሎት እንዲሰጡ ተደርጓል፡፡

ብዙ ገንዘብና ጉልበት ፈስሶባቸው የመንገድ መብራቶቹ ከተጠገኑ በኋላ ለማህበረሰቡ ተገቢውን አገልግሎት እንዲሰጡና በመሰረተ ልማት ላይ ምንም ዓይነት ጉዳት እንዳይደርስ ለክፍለ ከተማው እና ወረዳ ስራ አስኪያጅ እንዲሁም ለሰላም እና ፀጥታ አስተዳደር ጽህፈት ቤት ኃላፊዎች ጥገና ለተደረገላቸው መንገድ መብራቶች መሰረተ ልማቱ ላይ ምንም አይነት ጉዳት እንዳይደርስ ክትትል እና ቁጥጥር እንዲደረግ የማስረከብ ሥራም ተሰርቷል ብለዋል፡፡

በአሁኑ ወቅት ጥገና የተደረገላቸው አካባቢዎች ሙሉ በሙሉ አገልግሎት እየሰጡ መሆናቸውን የገለፁት ምክትል ዋና ዳይሬክተሯ፤ ይህም ህብረተሰቡ ከስርቆትና ከተለያዩ የወንጀል ድርጊቶች ስጋት ነጻ ሆኖ መንቀሳቀስ እንዲችል፣ የሰላም ሰራዊትን ጨምሮ የተለያዩ የፀጥታ አካላት እንደልባቸው ስራቸውን እንዲሰሩ፣ ከተማዋም ፅዱ እና ብሩህ እንድትሆን አድርጓል፡፡

አካባቢው አብያተ ክርስቲያናት የሚበዙባቸው እንደመሆኑ መጠን ብዙ ጊዜ ማታና ጠዋት የእምነት ቦታዎች ለመሄድ ይቸገር ለነበረው ማህበረሰብ ብርሃን ሆኗል፡፡ እንደልብ መንቀሳቀስ ችሏል፤ የትራፊክ ፍሰቱም እንዲሳለጥ አድርጓል ሲሉ የመንገድ መብራቶች ጥገና ያስገኛቸውን ጥቅሞች ገልጸውልናል፡፡

የኦፕሬሽንና ጥገና ዘርፉ “የማይበሩ” ብሎ ከተረከባቸው 12 ሺህ 423 ፖሎች ውስጥ ከ8 ሺህ 600 በላይ የሆኑትን አገልግሎት እንዲሰጡ ማድረግ እንደቻለ የገለፁት ምክትል ዋና ዳይሬክተሯ፤ በቀጣይ በተለይም ደግሞ በኮልፌ ቀራኒዮ ክፍለ ከተማ ትኩረት ተሰጥቶ እንደሚሰራ አብራርተዋል፡፡

እየበራ ያለው የመንገድ መብራት ነገ በተለያየ ችግር ምክንያት ላይበራ ይችላል፡፡ ይህ ከመሆኑ በፊት ማህበረሰቡ መሰረተ ልማቶቹን ልክ እንደራሱ ንብረት በአግባቡ በመጠበቅ፣ ጉዳት ደርሶባቸው ሲመለከት ደግሞ በአካባቢው ለሚገኙ የፀጥታ ሃይሎች በማሳወቅ ኃላፊነቱን እንዲወጣም ጥሪ አቅርበዋል፡፡

## ከተፈሪ መኮንን ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ ጋር በመተባበር ዘወትር ቅዳሜ በየአስራ አምስት ቀኑ የሚቀርብ

# ያልባከነ ንብረት

- **ያገለገሉ ንብረቶችን በመሸጥ ከ1 ነጥብ 5 ሚሊዮን ብር በላይ ገቢ ተገኝቷል**

**በሰገነት አስማማው**

ንብረቶች ከረዥም ጊዜ በኋላ በእርጅና እና ሌሎች ምክንያቶች ተገቢውን አገልግሎት መስጠት ሳይችሉ ሲቀር ህግና መመሪያ በሚፈቅደው መሰረት መወገድ እንዳለባቸው ይታወቃል፡፡ ከዚህ አንፃር ተቋማት የአገልግሎት ዘመናቸው ያለፈባቸውን የተለያዩ የተከማቹ ንብረቶችን የማስወገድ ስራ ይሰራሉ። አገልግሎት ላይ የማይውል ንብረት ማስወገድ አካባቢን ለሥራ ምቹ ማድረግ፣ ገቢን ማሳደግ እንዲሁም ንብረቶቹ ያለምንም አገልግሎት የያዙትን ቦታ በማስለቀቅ ለሌላ አገልግሎት ለማዋል ከፍተኛ ጠቀሜታ አለው፡፡

ከዚህ አኳያ ተፈሪ መኮንን ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ ከመማር ማስተማር ስራው ጎን ለጎን አገልግሎት የማይሰጡ ቁሳቁሶችን በስጦታ እንዲሁም በሽያጭ መልክ ህግና መመሪያን በመከተል የማስወገድ ስራ እያከናወነ መሆኑን በኮሌጁ የንብረትና ጠቅላላ አገልግሎት ዳይሬክተር ወይዘሮ ሰናይት አወቀ ለጋዜጣው ዝግጅት ክፍል ገልፀዋል፡፡

ዳይሬክተሯ እንዳብራሩት፤ ኮሌጁ በአዲስ አበባ ከተማ የመንግስት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት መመሪያ ቁጥር 02/2008 መሰረት የአስወጋጅ ኮሚቴ በማዋቀር ያገለገሉ ንብረቶችን በመመሪያው መሰረት በስጦታ እንዲሁም በሽያጭ እንዲወገዱ የማድረግ ስራ አከናውኗል፡፡ የአገልግሎት ዘመናቸው ያለፉ ንብረቶች ተጠግነው ጥቅም ላይ እንዲውሉ 64 ጠረጴዛ፣ 77 ወንበር፣ 6 ዴስክ ለተቋማት ተሰጥቷል፡፡ በስጦታ የተሰጣቸው ተቋማት ኮተቤ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤትና በአዲስ አበባ ፖሊስ ኮሚሽን የጉለሌ ክፍለ ከተማ ፖሊስ መምሪያ ሲሆኑ ንብረቶቹም 340 ሺህ 747 ብር የሚያወጡ ናቸው፡፡

ከዚህ በተጨማሪ ኮሌጁ ያገለገሉ ንብረቶች በሽያጭ እንዲወገዱ ለመንግስት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት ጽፏል፡፡ አገልግሎቱም በመመሪያው መሰረት ግልፅ ጨረታ በማወጣት ንብረቶቹ በሽያጭ እንዲወገዱ አድርጓል። ኮሌጁ ንብረቶችን ለተጫራቾች የማሳየት ስራ የሰራ ሲሆን፤ በዚህም 7 አሮጌ ተሽከርካሪዎች፣ ያገለገሉ የመኪና መለዋወጫዎች፣ ጎማ፣ ቁርጥራጭ ብረትና ቶነር ተሸጠው 1 ሚሊዮን 550 ሺህ ብር ወደ መንግስት ካዝና ገቢ መደረጉን ዳይሬክተሯ ገልፀዋል፡፡

ኮሌጁ የአገልግሎት ጊዜያቸው ያለፈባቸውን ንብረቶች ከማስወገድ በተጨማሪ አገልግሎት እየሰጡ በብልሽት ምክንያት የማይሰሩ ኮምፒዩተሮችና ፕሪንተሮች ጥገና ተደርጎላቸው በተገቢው እንዲያገለግሉ የማድረግ ስራም እየሠራ መሆኑን ወይዘሮ ሰናይት ያነሳሉ። ጥገናው የሚካሄደው በአዲስ አበባ ኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ልማት ቢሮ በተላኩ ባለሙያዎች አማካኝነት ሲሆን፤ ንብረቶቹን የመሰብሰብ ስራ ተሰርቶ ለጥገና በዝግጅት ላይ ነው ብለዋል፡፡

ኮሌጁ የአገልግሎት ግዜያቸው ያበቁ ንብረቶችን ከማስወገድና ንብረቶችን ከማደራጀት አንፃር ዘመናዊ አሰራርን ለመከተል እቅድ ይዟል፡፡ በአሁኑ ወቅትም የንብረት አያያዝን በቴክኖሎጂ በማስደገፍ መረጃን የማደራጀት ስራ እየተሰራ መሆኑን ወይዘሮ ሰናይት ጠቁመዋል፡፡

አንድ ንብረት ለአገልግሎት የማይውል ከሆነ በስጦታም ይሁን በሽያጭ በማስወገድ የያዘውን ቦታ ለሌላ አገልግሎት ማዋል ይገባል የሚሉት ወይዘሮ ሰናይት በየደረጃው የሚገኙ የኮሌጁ ሰራተኞችም አገልግሎት የሚሰጡ ማንኛውንም ንብረት ለረዥም ጊዜ እንዲያገለግል በአግባቡና በጥንቃቄ መጠቀም እንደሚገባ መልዕክት አስተላልፈዋል፡፡

ያገለገሉ ንብረቶች በአግባቡ የማይወገዱ ከሆነ ለብልሽት ከመዳረጋቸው ባሻገር በአካባቢ ፅዳት፣ ውበት፣ ጤና እና ኢኮኖሚ ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ይኖራቸዋል፡፡ ከዚህ አኳያ ያለአገልግሎት የተቀመጡ ሀብቶችን በስጦታ ወይም በሽያጭ በማስወገድ አካባቢን ንጹህ ማድረግና ገቢ በማመንጨት የከተማዋን ኢኮኖሚ መደገፍ ይገባል እንላለን፡፡



ፎቶ- ከተፈሪ መኮንን ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ
ኮሌጁ ካስወገዳቸው ያገለገሉ ንብረቶች መካከል በከፊል

## የኤሌክትሮኒክስ ቆሻሻዎችን መልሶ በመጠቀም ላይ ቀዳሚ ሀገራት

**በስንታየሁ ምትኩ**

የኤሌክትሮኒክስ ቆሻሻን መልሶ በመጠቀም ቀዳሚ ከሆኑ ሀገራት መካከል ሲንጋፖር አንዷ ናት፡፡ በሀገሪቱ የኤሌክትሪክና ኤሌክትሮኒክስ ምርት አወጋገድ ከፍተኛ ፈተና ደቅኖ የሚገኝ ሲሆን፤ በየዓመቱ 60 ሺህ ሜትሪክ ቶን ቆሻሻ ይመነጫል፡፡ ይህንን ችግር ለመቅረፍ የሲንጋፖር መንግስት አምራቾች ጥቅም ላይ የዋሉ የኤሌክትሮኒክስ ዕቃዎችን የመሰብሰብና የመለየት እንዲሁም መልሰው ጥቅም ላይ እንዲውሉ ለሚያደርጉ አካላት የመላክ ግዴታን የሚጥል ህግ አውጥቷል፡፡ ከዚህ ባሻገር ያገለገሉ የኤሌክትሮኒክስ ዕቃዎችን ከመጣል ይልቅ ጥገና ተደርጎላቸው መልሰው ጥቅም ላይ እንዲውሉ ማህበረሰቡን በማሳተፍ እየሰሩ ይገኛሉ፡፡ “ሪፔር ኮፒቲያም” በተሰኘ በበጎ ፈቃደኞች የሚመራ ድርጅት በኩልም ዜጎች ያገለገሉ ዕቃዎችን ከመጣል ይልቅ ጥገና ተደርጎላቸው መልሰው ጥቅም ላይ እንዲውሉ ድጋፍ ይደረግላቸዋል፡፡ ጥገና የሚደረግለት ዕቃ ባለቤት የሆነ ሰው በሌላ የሚተካ ካልሆነ በስተቀር አገልግሎቱን በነፃ ያገኛል፡፡ በራሱ ጥገና ማድረግ የሚችልበት ክህሎት መያዝ ከፈለገም ስልጠና ይሰጠዋል፡፡

በእንግሊዝም ሳንቲሞችን እና ሜዳሊያዎችን ከ30 በላይ በሆኑ ሀገራት በመስራት የሚታወቀው “ሮያል ሚንት” የተሰኘው ኩባንያ፣ ከሚወገዱ የኤሌክትሮኒክስ መሳሪያዎች ወርቅና ሌሎች የከበሩ ብረቶችን ማውጣት የሚቻልበት ስርዓት ፈጥሯል።

በታይዋን የኤሌክትሮኒክስ ምርቶች አያያዝ፣ አወጋገድና መልሶ መጠቀም የሚመራበት ህግ ያለ ሲሆን፣ በዘርፉ የተሰማሩ አምራቶችና አስመጪዎች ዕቃዎችን ሲያመርቱ መልሶ መጠቀምን ታሳቢ በማድረግ መሆን እንዳለበት ተቀምጧል። በተጨማሪም ያገለገሉ የኤሌክትሮኒክስ ቆሻሻዎች የአሰባሰብ ስርዓት መዘርጋት፣ መልሰው ጥቅም ላይ እንዲውሉ በፋይናንስ መደገፍን ጨምሮ የምርቶች ሙሉ ዑደት ጤናማ መሆኑን የመከታተል ኃላፊነት ተጥሎባቸዋል፡፡

**ከጀነራል ዊንጌት ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ ጋር በመተባበር ዘወትር ቅዳሜ በየሳምንቱ የሚቀርብ**

# የቴክኖሎጂ ማዕድ

**በሄለን ጥላሁን**

ችግር ብልሃትን ይወልዳል፡፡ ብልሃት ውጤታማነትን ያሳድጋል፡፡ ከፍ ያለ ውጤት ተወዳዳሪነትን ይጨምራል። ጤናማ ውድድር ደግሞ ዕድገትን ያፋጥናል፡፡ 21ኛው ክፍለ ዘመን የሠው ልጅ የተወሳሰቡ ችግሮችን በከፍተኛ ደረጃ የሚጋፈጥበት ወቅት ሆኗል። የችግሮቹ መብዛት ደግሞ የመፍትሔ አማራጮችን እንዲያበዛ አስገድዶታል። በየዕለቱ በሚባል ደረጃ በሠው ረቂቅ አዕምሮ ውስጥ ተፀንሰው ዕውን እየሆኑ የሚገኙ የቴክኖሎጂ ፈጠራ ውጤቶች ደግሞ ሁነኛ የችግር መፍቻ ቁልፍ የመሆን ምስጢሩን ከዚህ ጋር እንዲያያዝ አድርጎታል፡፡

እንደ ጀነራል ዊንጌት ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅን የመሳሰሉ የዕውቀት እና የክህሎት ማዕከላት አዳዲስ የቴክኖሎጂ ውጤቶች እንዲፈጠሩ፣ እንዲባዙ እና ለተጠቃሚው እንዲደርሱ የማድረግ ጉልህ ሚናን ይጫወታሉ፡፡ የማህበረሰቡን ችግር የሚፈቱ የፈጠራ ስራዎችን መስራት በእጅጉ በሚበረታታበት በዚህ ወቅት በተለይም እንደ ጀነራል ዊንጌት ያሉ የቴክኒክና ሙያ ማሰልጠኛ ተቋማት ወጣቶችን በተለያየ የሙያ መስክ በማሰልጠን ረገድ እያበረከቱት ያለው አስተዋፅኦ ከፍተኛ ነው፡፡ ከሩቅ ሆነን የምንመለከታቸውና የምንመኛቸው የቴክኖሎጂ ምርቶች ጊዜ አስቆጥረውም ቢሆን በየደጃችን ጎራ እንዲሉ የተቋማቱ ሚና አስፈላጊ ነው፡፡

የጀነራል ዊንጌት ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን በመፍጠር ወይም ከሌሎች በመኮረጅ ለተጠቃሚው ማህበረሰብ የማድረስ ኃላፊነቱን እየተወጣ ይገኛል፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ እየተሠራ ስላለው ሥራ በኮሌጁ የቴክኖሎጂ ልማት እና የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎት ምክትል ዲን አቶ ደሜ መርሻ ለዝግጅት ክፍላችን እንዳስረዱት፤ በርካቶችን የሙያ ባለቤት ባደረገው በአንጋፋው የእውቀት ቤት ውስጥ በርካታ የፈጠራ ስራዎች ተሰርተዋል፡፡ በተለይም አንድን ግብዓት በቀላሉ ጥቅም ላይ ሊውል በሚችልበት አግባብ በመለወጥ፣ በመቅዳትና በማላመድ ቴክኖሎጂው ጥቅም ላይ እንዲውል የማድረግ ስራ በስፋት እየተሰራ ነው፡፡

እንደ አቶ ደሜ ገለፃ፤ ችግሮችን የሚቀርፉ ቴክኖሎጂዎችን የመፍጠር ሥራ የጀነራል ዊንጌት ኮሌጅን ጨምሮ በመሰል ተቋማት የተለመደ ሆኗል፡፡ ተቋማት ሥራዎቻቸውን የበለጠ ውጤታማ ለማድረግ ደግሞ በመካከላቸው የውድድር መንፈስ መፍጠር፣ ተሞክሮና ልምድ እንዲለዋወጡ ማድረግ ይገባል፡፡ እንደ ከተማ አስተዳደር ብሎም በሀገር አቀፍ ደረጃ የሚዘጋጁ መድረኮች ለዚህ ትልቅ አበርክቶ እያደረጉ ይገኛል፡፡ ባሳለፍነው ሚያዝያ ወር 2017 ዓ.ም. ላይ "ብሩህ አዕምሮዎች በክህሎት የበቁ ዜጎች" በሚል መሪ ሀሳብ 4ኛው ሀገር አቀፍ የብቃት ውድድር በፌደራል ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ኢንስቲትዩት የተካሄደው መርሐ ግብር ተጠቃሽ ነው፡፡

በዚህ መርሐ ግብር ላይ የጀነራል ዊንጌት ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ በክህሎት፣ በቴክኖሎጂ እና በተግባራዊ ጥናትና ምርምር ዘርፎች መወዳደሩን የጠቆሙት አቶ ደሜ፤ ኮሌጁ በዚህ ውድድር ሜዳሊያዎችን ማግኘቱን ገልጸዋል፡፡ "በተለያዩ ጊዜያት የሚካሄዱ ውድድሮች ለተሻለ ስራ ብርታት ይሆኑናል" የሚሉት አቶ ደሜ፤ ሰልጣኞች ብሎም አሰልጣኞች በሚያገኟቸው ማበረታቻዎች በርካቶች መነቃቃታቸውን ጠቅሰዋል፡፡

አክለው እንዳስረዱት፤ በቴክኒክና ሙያ ማሰልጠኛ ተቋማት የሚሰጠው ስልጠና 30 በመቶ የንድፈ ሃሳብ ትምህርት እንዲሁም 70 በመቶ የተግባር ላይ ልምምድ በመሆኑ 'እንዴት ስራዎችን መከወን ይቻላል?' የሚለውን በቀላሉ ሰልጣኞች እንዲረዱት ያግዛቸዋል። ኮሌጁ የቴክኖሎጂ ውጤቶችን አባዝቶ ይሸጣል፡፡ ውጤታማ ስራዎችን ለመስራት ይቻል ዘንድ የተግባር ላይ ልምምድ ማድረጊያ ግብዓቶችን፣ ቁሳቁሶችንና የመስሪያ ማሽኖችን ጭምር በአግባቡ ማሟላት መቻሉ ኮሌጁ ስራውን በትጋት እንዲወጣ አግዞታል፡፡

## ለዕይታ የቀረቡ የኮሌጁ አዳዲስ ፈጠራዎች

በመጠናቀቅ ላይ ባለው የ2017 የትምህርት ዘመን የቴክኖሎጂ ፈጠራ ሥራዎችን ለማበረታታት የሚያስችል መርሐ ግብር በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ደረጃ ተካሂዷል። የቴክኒክና ሙያ ሳምንት በሚል በየዓመቱ በሚካሄደው መርሐ ግብር ሲሳተፍ የቆየው የጀነራል ዊንጌት ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ፣ በዚህ ዓመትም በንቃት ተሳትፏል። የምርት ማምረቻ ቴክኖሎጂዎች በአሰልጣኝ ብሎም በሰልጣኞች ተሰርተው ለእይታ ቀርበዋል። በተለይም ሀገር በቀል እንዲሁም ከውጭ የተቀዱ የቴክኖሎጂ ስራዎችን በአሰልጣኞች ብሎም በሰልጣኞች ስለመሰራታቸው የሚያብራሩት አቶ ደሜ፣ አካል ጉዳተኛውን መመገብ ብሎም ማጠጣት የሚችል ሮቦት ለእይታ ቀርቧል፡፡ አካል ጉዳተኞች በራሳቸው እጃቸውን ለማንቀሳቀስ የሚቸገሩበት አጋጣሚ ካለ ሮቦቱ በቀላሉ ምግባቸውን የመመገብ እንዲሁም የሚጠጡትን ጭምር የማጠጣት ስራ ይሰራል ሲሉም ተናግረዋል፡፡

በሌላ በኩል የሰው ልጆችን ድካም የሚቀንስ ብሎም በጥራትና በፍጥነት ተወዳዳሪ መሆን የቻለውን የእህል መፍጫ ማሽን በአሰልጣኞች ተሰርቶ ለእይታ



ፎቶ ከጀነራል ዊንጌት ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ

የፕላስቲክ መፈጫ ማሽን




ፎቶ ከጀነራል ዊንጌት ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ

ዘመናዊ የዶሮ ኬጅ

ቀርቧል፡፡ የኤሌክትሪክ ሃይል ውስንነት ባለባቸው አካባቢዎች ካለምንም ስጋት እህል ማስፈጨት የሚችሉበት አግባብ ተመቻችቷል። አብዛኞቹ የእህል መፍጫ ማሽኖች ከፍተኛ የሆነ የኤሌክትሪክ ሃይል ፍጆታ ይጠቀማሉ፡፡ ጥቅም ላይ በሚውለው የኤሌክትሪክ ሃይል አላግባብ የሚፈስሰውን ሃብት ለመቆጠብ አማራጭ መፍትሔ የሚሆነው ዝቅተኛ የሆነ የኤሌክትሪክ ሃይል መጠቀም ነው ብለዋል፡፡

እንደ አቶ ደሜ ገለፃ፤ ኮባን በመፋቅ ወደ ቃጫነት የሚቀይር ማሽንም ለእይታ በቅቷል፡፡ በሀገራችን አብዛኛው አካባቢ ላይ በስፋት ኮባ ይተከላል፡፡ ታድያ ማሽኑ ኮባውን ደጋግሞ በመፋቅ ወደ ቃጫነት ይቀይራል፡፡ ምርቱንም ለተለያዩ አገልግሎቶች እንዲውል በማድረግ ተጠቃሚዎች ይገለገሉበታል፡፡

በተያያዘም እንደ ሃይላንድ እና መሰል የፕላስቲክ ውጤቶች በየቦታው ተጥለው ይታያሉ፡፡ እነዚህ ደግሞ አካባቢን በመበከል ረገድ ትልቁን ድርሻ ይወስዳሉ፡፡ ይህን ከግምት በማስገባት ፕላስቲኮችን የሚፈጭ ማሽን ለመስራት ተችሏል፡፡ ማሽኑ በዋናነት ፕላስቲኮቹን ቁርጥራጭ እስኪሆኑ ድረስ በመፍጨት ስራውን ይሰራል፡፡ ቀጥሎም የተፈጨውን ፕላስቲክ የሚያቀልጥ ማሽን በተጨማሪነት በኮሌጁ አሰልጣኞችና ሰልጣኞች አማካኝነት ተሰርቷል፡፡ የቀለጠውን ፕላስቲክ በመጠቀም ደግሞ የተለያዩ ወንበሮችን ጠረጴዛዎችን በቅርፅ ማውጫ ውስጥ በመክተት የሚፈለገውን ውጤት ይሰጣል፡፡

ሌላኛው የማምረቻ ቴክኖሎጂዎች ውጤት የሆነው ብዛት ያለውን ድንች በአንድ ጊዜ በሚፈለገው ቅርጽ የሚሰነጣጥቅ ማሽን ነው፡፡ በተለይ ችብስ በመስራት ላይ ያሉ ሙያተኞች ጊዜያቸውን እና ጉልበታቸውን እንዲቆጥብላቸው ተደርጎ የተዘጋጀ የፈጠራ ስራ ነውም ብለዋል፡፡

በምርት ደረጃ ለውድድር የቀረቡ ስራዎችን በተመለከተ በጀነራል ዊንጌት ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ በብረታ ብረት ማምረቻ ትምህርት ክፍል የዶሮ ኬጂዎች እየተመረተ ይገኛል፡፡ የኮሌጁ ሜታል ማኑፋክቸሪንግ ዲፓርትመንት በአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ ስር ለሚገኙ ወረዳዎች አገልግሎት የሚውል የዶሮ ኬጂዎችን በማምረት ላይ ይገኛል። ዲፓርትመንቱ እያንዳንዳቸው 50 ዶሮዎችን የሚይዙ 48 ኬጂዎች እና 100 ዶሮዎችን ማስተናገድ የሚችሉ 24 የዶሮ ኬጂዎችን በጥራት አምርቶ ለማስረከብ እየተጋ እንደሚገኝም አቶ ደሜ አክለዋል። እየተሰሩ ያሉ ኬጂዎች ለእንቁላል ጣይ ዶሮዎች መኖሪያ አገልግሎት እንደሚውሉ የተናገሩ ሲሆን፤ በአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ ስር የሚገኙ የወረዳ አስተዳደር ጽህፈት ቤቶች የከተማ ግብርና ውጤት በሆኑት የሌማት ትሩፋት ስራዎች ላይ አጠናክረው እንዲሰሩ ያግዛል፡፡ በተለይ ዶሮዎች የሚመገቧቸውን ብሎም የሚጠጡትን ውሃ ብክነት እንዳይፈጠር የሚያስችል የዶሮ ኬጂ ስለመሆኑ አስረድተዋል፡፡

በምርት ደረጃ ለውድድር ከቀረቡ ስራዎች መካከል ለሆስፒታሎች የሚሆን፣ ተጣጣፊ የሆነ እና ወንበርም አልጋም ሆኖ ማገልገል የሚችለው የቴክኖሎጂ ፈጠራ አንዱ ነው፡፡ በሆስፒታሎች አካባቢ ያለውን የአልጋ እጥረት ለመቀነስ ብሎም የታካሚውን እና የአስታማሚውን ምቾት ለመጠበቅ ያስችል ዘንድ የተሰራ መሆኑን አብራርተዋል፡፡

ሀገራችን ከፍተኛ የውጭ ምንዛሬ በማውጣት የምትገዛቸውን የመስሪያ ማሽኖች እዚሁ በሀገር ውስጥ ምርት በመተካት ረገድ በቴክኒክና ሙያ ተቋማት የሚመረቱ የፈጠራ ውጤቶች ትልቅ ሚና አላቸው፡፡ በተለይም አንድን ግብዓት በቀላሉ ጥቅም ላይ ሊውል በሚችልበት አግባብ በመለወጥ፣ በመቅዳትና በማላመድ ረገድ ያላቸው አበርክቶ አይተኬ ነው፡፡ ስለዚህ እንዲህ አይነት የቴክኖሎጂ መፍለቂያ ስፍራዎች አቅማቸውን ማጠናከር ያስፈልጋል መልዕክታችን ነው፡፡

## የበጎነት... ከገጽ 8 የዞረ

ከ402 በላይ ትምህርት ቤቶች ላይ የበጎ ፈቃድ ክበባት ተቋቁመው ተማሪዎች በጎ ፈቃድን ከልጅነታቸው ጀምሮ እንዲማሩ፣ እርስ በርስ መረዳዳትና መደጋጋፍን እንዲያጎለብቱ እየተደረገ ነው፡፡ ይህ ዓይነቱ ስራ ከስድስት ዓመት በፊት ጀምሮ ሲሰራበት የቆየ ሲሆን፤ በዘንድሮው ዓመት በተለየ ትኩረት ተሰጥቶ እየተሰራበት እንደሚገኝ አቶ ቢኒያም ይናገራሉ፡፡

የከተማዋን ነዋሪዎች በበጎ ፈቃድ አገልግሎት ላይ በበጎ ፈቃደኝነት በማሳተፍ ረገድ ውጤታማ ስራ መከናወኑን አቶ ቢኒያም ያነሳሉ፡፡ በዚህ ረገድ ባለፈው ክረምት በተከናወነው የአረንጓዴ አሻራ መርሃ ግብር ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው በጎ ፈቃደኞች የተሳተፉበት ሲሆን፤ በድግግሞሽ ከ2 ነጥብ 2 ሚሊዮን በላይ የህብረተሰብ ክፍሎች ተሳትፈዋል፡፡ በደም ልገሳ መርሃ ግብር ከ62 ሺህ በላይ፣ በከተማዋ በሚገኙ ሆስፒታሎችና ጤና ጣቢያዎች ለተገልጋዮች አቅጣጫን በማመላከት፣ አስታማሚ የሌላቸውን ታካሚዎች በማስታመምና መሰል "በጎነት በሆስፒታል" አገልግሎት ከ3 ሺህ 500 በላይ በጎ ፈቃደኞች ተሳትፈዋል፡፡

የጎርፍ ስጋትን ለመከላከል የመፋሰሻ ቱቦዎችን በማፅዳት ከ541 ሺህ በላይ በጎ ፈቃደኞች በየአካባቢያቸው በድግግሞሽ ተሳትፈዋል፡፡ ሌላው በርካታ በጎ ፈቃደኞች ተሳትፎ እያደረጉበት ያለው የማዕድ ማጋራት ሲሆን፤ ከባለሀብቱ ድጋፍ በማሰባሰብና ለተጠቃሚዎች በማድረስ በጉልበት አስተዋጽኦ በማድረግ ከ73 ሺህ በላይ በጎ ፈቃደኞች ተሳትፎ አድርገዋል፡፡

የቤት እድሳት ላይ በዋናነት የሚታደሰውን ቤት በማፍረስ፣ እቃዎችን በአግባቡ በማውጣትና የሚፈለገው ቦታ በማድረስ የጉልበት አስተዋፅኦ በማድረግ ረገድ ከ63 ሺህ በላይ በጎ ፈቃደኞች ተሳትፎ አድርገዋል፡፡

የመንገድ ትራፊክ ማስተናበር ሌላኛው የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ሲሆን፤ በዚህ ዘርፍ የሚሳተፉ በጎ ፈቃደኞች በተለይ ክረምት ላይ ቁጥራቸው ከፍ ይላል፡፡ በበጋ ወቅት ይህንን ስራ የሚያከናውኑ በመደበኛነት የመንገድ ትራፊክ ማስተናበር ላይ የሚሳተፉ በጎ ፈቃደኞች 800 ናቸው፡፡ ክረምት ላይ ተማሪዎችም ስለሚሳተፉ በጥቅሉ 8 ሺህ አካባቢ በጎ ፈቃደኞች ይደርሳሉ።

በ"ሙያዬን ለሀገሬ" መርሃ ግብር መምህራንን፣ የጤና ባለሙያዎችን፣ የህግ ባለሙያዎችን ጨምሮ ከ11 ሺህ በላይ በጎ ፈቃደኞች እየተሳተፉ ይገኛሉ፡፡ በሰላም እሴት ግንባታ፣ በኪነ ጥበብና መዝናኛ ፕሮግራም፣ በስፖርታዊ እንቅስቃሴ፣ በከተማ ግብርና፣ በአገልግሎት ሰጪ ተቋማት፣ በወሰን የለሽ በጎ ፈቃድና በሌሎች ፕሮግራሞች በርካታ በጎ ፈቃደኞች እየተሳተፉ እንደሚገኙም አቶ ቢኒያም አብራርተዋል፡፡

በጎ ፈቃደኝነት ባህል እንዲሆን ለበጎ ፈቃደኞች እውቅናና ሽልማት እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡ ባለፉት አስር ወራት ከ6 ሺህ 900 በላይ ለሚሆኑ በጎ ፈቃደኞች ከምስክር ወረቀት ጀምሮ እስከ ዋንጫ የሚደርስ እውቅናና ሽልማት ተሰጥቷቸዋል፡፡

አቶ ቢኒያም እንደገለፁት፣ ባለፉት አስር ወራት ውስጥ በበጎ ፈቃድ አገልግሎት ከ1 ነጥብ 4 ሚሊዮን በላይ የህብረተሰብ ክፍሎችን ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል፡፡ 7 ሺህ 566 የሚሆኑ ቤቶች ታድሰውና ተገንብተው ለነዋሪዎች ተላልፈዋል፡፡ በበጎ ፈቃደኞች ድጋፍ የበጎነት መንደሮች በየቦታው ተገንብተዋል፡፡ በእነዚህ በታደሱ ቤቶችም ከ29 ሺህ በላይ ነዋሪዎችን ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል፡፡

ሌላው በበጎ ፈቃድ አገልግሎት ሰፊ የማህበረሰብ ክፍል ተጠቃሚ የሆነበት የማዕድ ማጋራት መርሃ ግብር ሲሆን፤ ባለፉት አስር ወራት ከ1 ነጥብ 2 ሚሊዮን በላይ የሚሆኑትን ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል፡፡ ይህም በተለያዩ በዓላት በድግግሞሽ ድጋፍ የተደረገላቸውን በማካተት ጭምር እንደሆነ አቶ ቢኒያም አስረድተዋል፡፡

ባለፉት ዓመታት እየተጠናከረ የመጣው በጤናው ዘርፍ የሚሰጠው የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ሌላኛው ሲሆን፤ በዚህም ከ123 ሺህ በላይ የህብረተሰብ ክፍሎች የነፃ ህክምና አገልግሎት ተጠቃሚ መሆን ችለዋል፡፡ ትላልቅ የህክምና ካምፖችን አደባባዮች አካባቢ በመገንባት ከምርመራ እስከ ህክምና የሚደርስ አገልግሎት ነዋሪዎች የሚያገኙበት፣ ትላልቅ የመንግስት፣ የግልና ዓለም አቀፍ የጤና ተቋማት የሚሳተፉበትና ውጤትም የተገኘበት መርሃ ግብር እንደሆነ አቶ ቢኒያም አንስተዋል፡፡

ሌሎች በዚህ ዘርፍ ያላካተትናቸው የበጎ ፈቃድ መርሃ ግብርም በርካታ ሰዎችን ተጠቃሚ ማድረግ እንደተቻለ አቶ ቢኒያም አብራርተዋል፡፡

በበጎ ፈቃድ በተሰጡ አገልግሎቶች ከ12 ቢሊዮን ብር በላይ በመንግስት ይሸፈን የነበረን ወጪን ማዳን አስችሏል። አቶ ቢኒያም እንደገለፁት፣ በበጎ ፈቃድ በከተማዋ እየተሰሩ ያሉ ሁሉም ስራዎች ተለቅመው ቢያዙ ከዚህም በላይ ይሆናሉ፡፡ ባለፉት ስድስት ዓመታት በበጎ ፈቃድ የሚሰጡ አገልግሎቶች በይዘትም ሆነ ብዛት እየጨመሩ መጥተዋል፡፡ በዚህ ረገድ የከተማ አስተዳደሩ ሚና ከፍተኛ ነበር፡፡

የ2017 በጀት ዓመት የክረምት የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ከሰኔ ወር ጀምሮ እስከ መስከረም 30 ቀን 2018 ዓ.ም እንደሚቆይ ከከተማዋ የህብረተሰብ ተሳትፎና በጎ ፈቃድ ማስተባበሪያ ኮሚሽን ያገኘነው መረጃ ያመለክታል፡፡ በበጎ ፈቃድ አገልግሎቱ ከ2 ሚሊዮን በላይ የሚደርሱ በጎ ፈቃደኞች በድግግሞሽ በ15 ፕሮግራሞች እና በ19 መርሃ ግብሮች ላይ ይሳተፋሉ፡፡ 800 ሺህ የህብረተሰብ ክፍሎችም ተጠቃሚ ይሆናሉ ተብሎ ይጠበቃል፡፡

የከተማ አስተዳደሩ ከሰኔ 5 ቀን እስከ ጳጉሜ 5 ቀን 2017 ዓ.ም ባሉ 90 ቀናት በልዩ ተልዕኮ ከሚያከናውናቸው 18 ዋና ዋና ተግባራት መካከል የክረምት የበጎ ፈቃድ ስራዎች ይጠቀሳሉ፡፡

## ማዕከላቱ... ከገጽ 9 የዞረ

የምፈልገውን ነገር በማውረድ እንዳነብ አድርጎኛል፡፡ የተለያዩ መጽሐፍትም ስላሉ የንባብ ክህሎቴን አዳብሮልኛል፡፡ የኮምፒዩተር እውቀቴንም አሻሽሎልኛል። ብዙ ጊዜ የማነብበው ፈተና ሲቃረብ ነበር፤ አሁን ግን በወጣቶች የሰብዕና መገንቢያ ማዕከላት የምፈልገውን አገልግሎት ማግኘት ችያለሁ" ብሏል፡፡

የማዕከሉ ሥራ አስኪያጅ አቶ አሰግድ ተሾመ ለዝግጅት ክፍላችን እንዳስረዱት፤ ማዕከሉ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከሚገኙ የወጣቶች ሰብዕና መገንቢያ ማዕከላት ሞዴል ለመሆን የቻለ ነው። ቁጥራቸው 18 የሚሆኑ አገልግሎቶችን ይሰጣል፡፡ ከእነዚህም መካከል ስፖርታዊ የመዝናኛ ጨዋታዎች፣ ወጣት ተኮር የጤና አገልግሎት፣ የዲጂታል ቤተ መጻሕፍት አገልግሎት፣ የካፍቴሪያ፣ የጤናና የሥነ ተዋልዶ፣ የሻወር፣ የሴቶች የውበት ሳሎን፣ የወንዶች የውበት ሳሎን፣ ጌም ዞን፣ ሳይንስና ፈጠራ፣ የዲ ኤስ ቲቪ፣ የጂምናዚየም፣ የክብደት ማንሳት አገልግሎት፣ እንደ ከረምቡላና ፑል ያሉ የቤት ውስጥ ጨዋታዎች፣ የተለያዩ ክበባት በስፖርት ሰርከስ እና ቴኳንዶ፣ በአርት ዘርፉ ውዝዋዜ ዳንስ እንዲሁም በቴአትርና በመሳሰሉት አገልግሎት እንደሚሰጥ ተናግረዋል፡፡

ማዕከሉ በ2017 በጀት ዓመት 9 ወራት 52 ሺህ 254 ወጣቶችን ተዳራሽ ያደረገ አገልግሎት መስጠቱን የሚናገሩት የማዕከሉ ሥራ አስኪያጅ፣ በክረምቱ መርሐ ግብር 25 ሺህ ወጣቶችን በተለያዩ አገልግሎቶች ተጠቃሚ ለማድረግ ስለመታሰቡ ጠቁመዋል፡፡ በበጎ ፈቃደኛ የኮሌጅና ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች የትምህርት ስልጠና የመስጠት፣ ከጤና ጽህፈት ቤት ጋር በመተባበር በወር አንድ ጊዜ ለሁሉም ማህበረሰብ የጤና ምርመራ የማድረግ፣ የአረንጓዴ አሻራ መርሐ ግብር ተሳታፊ መሆን እንዲሁም የአቅመ ደካሞችን ቤት የማደስ ስራዎችን ለመስራት በዝግጅት ላይ መሆኑንም ተናግረዋል፡፡ ማዕከሉ የሰው ሃይል እጥረት እንዳለበት በመጠቆምም ይህንን ችግር ለመቅረፍ በበጎ ፈቃደኛ ወጣቶችና ሁሉም ሰራተኛ ደከመኝ ሰለቸኝ ሳይል በመስራቱ ውጤታማ ለመሆን መብቃታቸውን አብራርተዋል፡፡

በከተማችን ያሉ የወጣት ሰብዕና መገንቢያ ማዕከላት ሁለት መልክ ያላቸው እንደሆኑ ከላይ ያነሳናቸው ማዕከላት አስረጅዎች ናቸው፡፡ ይህን ከግምት ያስገባ ስራም ከሚመለከተው የመንግስት አካል ይጠበቃል፡፡

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በወጣቶችና ስፖርት ቢሮ የወጣት ሰብዕና መገንቢያ ማዕከል አገልግሎት ልማት ቡድን መሪ አቶ ሳሙኤል ምትኩ፤ በከተማ አቀፍ ደረጃ ያለውን የወጣቶች ሰብዕና መገንቢያ ማዕከላት ያሉበትን ሁኔታ እና የአገልግሎት አሰጣጥ ደረጃቸውን በተመለከተ ለዝግጅት ክፍላችን ማብራሪያ ሰጥተዋል፡፡ ማዕከላቱ ወጣቶች ከተለያዩ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች ተላቅቀው በከተማዋ ልማት ንቁ ተሳታፊና ተጠቃሚ እንዲሆኑ እንዲሁም ራሳቸውን ለማዝናናትና በእውቀት ለመገንባት እንዲችሉ የወጣቶች ሰብዕና መገንቢያ ማዕከላቱ ጉልህ ሚና እንዳላቸው ገልፀዋል፡፡

**አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ወጣቶችና ስፖርት ቢሮ የሚያስተዳድራቸው 114 የወጣት ሰብዕና መገንቢያ ማዕከላት አሉ። የሚሰጡት አገልግሎት በአራት ይከፈላል**

እንደ ቡድን መሪው ማብራሪያ፤ አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ወጣቶችና ስፖርት ቢሮ የሚያስተዳድራቸው 114 የወጣት ሰብዕና መገንቢያ ማዕከላት አሉ፡፡ የሚሰጡት አገልግሎት በአራት ይከፈላል፡፡ ሞዴል፣ ሁለገብ፣ መለስተኛ እና አነስተኛ ተብለው ይከፈላሉ። ሞዴል የሚባሉት ከአስራ ስድስት በላይ አገልግሎት የሚሰጡ ናቸው፡፡ በዚህ ደረጃ አገልግሎት እየሰጡ ያሉ 33 ማዕከላት ናቸው፡፡ ሁለገብ የሚባለው ደረጃ ደግሞ ከአስራ ሦስት በላይ አገልግሎት የሚሰጡ ሲሆን የማዕከላቱ ቁጥርም 47 ናቸው፡፡ መለስተኛ በሚባል ደረጃ የሚገኙት ከዘጠኝ በላይ አገልግሎት የሚሰጡ ሲሆን፤ ቁጥራቸውም 24 ነው። አነስተኛ የሚባሉት ደግሞ ከአምስት በታች አገልግሎት የሚሰጡ ሲሆን ቁጥራቸውም 10 ነው፡፡

አክለው እንዳስረዱት፤ ቢሮው አነስተኛዎችን ወደ መለስተኛ፣ መለስተኛዎችን ወደ ሁለገብ እንዲሁም ደግሞ ሁለገቦችን ወደ ሞዴልነት እንዲመጡ ማስቻል ላይ በትኩረት እየሰራ ይገኛል፡፡ በዚህም መሰረት የመገልገያ ቁሳቁሶችን የማሟላት ስራ ተሰርቷል፡፡ ከመብራት ጋር በተያያዘ ለተነሱ ጥያቄዎች አቶ ሳሙኤል በሰጡት ምላሽ ማዕከላቱ አቅማቸው ደከም ብሎ መክፈል ሲቸገሩ እንዲሁም በተለያዩ ልማቶች ምክንያት የመብራት መቆራረጥ ይገጥማል፡፡ እርሱም እንዲፈታ ባለን ትስስር መሰረት ከመብራት አገልግሎት ጋር በመነጋገር ችግሮች እንዲፈቱ የማድረጉን ስራ እየተሰራ ነው፡፡ ጉዳዩም በሂደት ላይ ይገኛል፡፡

የባለሙያ እጥረት ባለባቸው የወጣት ሰብዕና መገንቢያ ማዕከላት ጉድለቶችን ለመሙላት የመፍትሔ ሃሳብ አቅርበዋል። በዚህም መሰረት እንደ ከተማ የባለሙያ ቅጥር ቆሟል፡፡ መፍትሔ የሚሆነው ያሉ ባለሙያዎችን በውክልና እንዲሰሩ ማድረግ በመሆኑ ያንን ማድረግ ተችሏል። ከዚያ በተጨማሪ የክረምት ብሎም የበጋ ቋሚ በጎ ፍቃደኞች አሉ፡፡ የቤተ መጻሕፍት ቤቱ ባለሙያ ባይኖር እንኳ በበጎ ፍቃደኛ እንዲሸፈን የማድረግ ስራ ተሰርቷል፡፡ ሌላው ደግሞ ስብሰባዎች ሲኖሩ የአዳራሽ መጨናነቆች ይፈጠራሉ። ክበባት ላይ አገልግሎት ተጠቃሚ የሆኑ ወጣቶች የመስሪያ ፕሮግራማቸውን በማይጋፋ መልኩ እንዲካሄድ አቅጣጫ ተሰጥቷል። በተቀመጠው ፕሮግራም መሰረትም የሚገለገሉ አካላት እራሳቸው ስብሰባውን እንዲያስተባብሩ እየተደረገ ስለመሆኑ አብራርተዋል፡፡

በ9 ወር ውስጥ በድግግሞሽ 4 ነጥብ 9 ሚሊየን በላይ ወጣቶች በሰብዕና መገንቢያ ማዕከላት ውስጥ ተጠቃሚ ለመሆን ችለዋል፡፡ በመጪው ክረምት በእቅድ ደረጃ ቢሮው ሊሰራቸው ያሰባቸው ተግባራት ሰብዓዊ አገልግሎት፣ አረንጓዴ ልማትና አካባቢ ጥበቃ አገልግሎት፣ ትምህርትና ስልጠና አገልግሎት፣ የጤና አገልግሎት እንዲሁም የበጎ ፈቃድ ወጣቶች ፌስቲቫል በማድረግ በማዕከል የሚሰጡ አገልግሎቶችን ማስተዋወቅ ይገኙበታል፡፡ በዚህም 334 ሺህ 293 በላይ ወጣቶችን ያሳተፈ ብሎም 257ሺህ 426 የህብረተሰብ ክፍሎችን ተጠቃሚ የሚያደርግ አገልግሎት እንደሚሰጥ አስታውቀዋል፡፡

የወጣቶች የሰብዕና መገንቢያ ማዕከላት ወጣቶች በአካልና በአዕምሮ እንዲዳብሩ ብሎም የተሟላ ሰብዕና እንዲኖራቸውና አልባሌ ቦታዎች ላይ ጊዜያቸውን እንዳያሳልፉ የሚያግዝ በመሆኑ የከተማዋን ወጣት በሚመጥን መልኩ ለማሻሻል ዘመኑን በዋጀው የሶፍት ኮፒ አገልግሎት ወጣቶቹ በስልካቸውም ሆነ በኮምፒዩተር አውርደው እንዲጠቀሙ ነፃ የዋይፋይና የኢንተርኔት አገልግሎት እንዲያገኙና ወደ ሳይንስ ካፌ እንዲያድጉ ጥረቶች እየተደረጉ ነው ብለዋል፡፡

## በድጋሚ የወጣ የቅጥር ማስታወቂያ

### የአዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ ከዚህ በታች በተገለፁት ክፍት የስራ መደቦች ላይ አመልካቾችን አወዳድሮ ለመቅጠር ይፈልጋል፡፡

| ተ.ቁ | የሥራ መደብ መጠሪያ | ደረጃ | ተፈላጊ የትምህርት ደረጃ | አግባብ ያለው የሥራ ልምድ | የሙያ ዓይነት | መደብ መታወቂያ ቁጥር | ብዛት | የቅጥር ሁኔታ | ደመወዝ | የሥራ ቦታ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| **የዲጂታል ሚዲያና ህትመት ዘርፍ በድጋሚ የወጣ** | | | | | | | | | | |
| 1 | የድረ ገፅ ከፍተኛ አዘጋጅ | XIII | ቢ.ኤ./ኤም.ኤ ዲግሪ | 8/6 ዓመት | በጋዜጠኝነትና ኮሚዩኒኬሽን፣ በሀገር ውስጥ ቋንቋዎችና ስነ-ጽሁፍ፣ በውጭ ቋንቋዎችና ስነ-ጽሁፍ፣ በቲያትርካል አርት በፖለቲካል ሳይንስና ዓለም አቀፍ ግንኙነት፣ የሚዲያ ጥናት፣ ሥራ አመራር እና ቢዝነስ አስተዳደር ወይም በተዛማጅ የማህበራዊ ሳይንስ የትምህርት ዘርፍ | ሴ/18. | 1 | በቋሚነት | በተቋሙ ስኬል መሰረት | አዲስ አበባ |

**ማሳሰቢያ፡-**

1. አመልካቾች ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ባሉት 10/አምስት/ ተከታታይ የስራ ቀናት ውስጥ የትምህርት ማስረጃችሁን ዋናውንና የማይመለስ ፎቶ ኮፒ በመያዝ በተቋሙ የሰው ኃብት ስራ አመራር እና ልማት ዳይሬክቶሬት ቢሮ ቁጥር 05 ድረስ በመምጣት እንድትመዘገቡ እናሳስባለን፡፡
2. ከግል ድርጅቶች የሚቀርብ የስራ ልምድ ማስረጃ የስራ ግብር የተከፈለበት ስለመሆኑ ከግብር ሰብሳቢ መ/ቤት ማስረጃ ማምጣት ይኖርባቸዋል፡፡
3. የስራ ልምድ የሚጠይቀው ከወጣው ክፍት መደብ ጋር ቀጥተኛ መሆን አለበት፡፡
4. የምዝገባው ቀን ከሰኔ 16 ቀን 2017 ዓ.ም እስከ ከሰኔ 27 ቀን 2017 ዓ.ም ድረስ
5. የፈተና ቀን በውስጥ ማስታወቂያ ይገለፃል፡፡
6. ለበለጠ መረጃ አድራሻ አምስት /5/ ኪሎ ቅድስተ ማርያም ፊት ለፊት ማህበረ ቅዱሳን ህንፃ ጐን ስልክ 0111551848

**አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ**

---

ወ/ሮ/ወ/ት/አቶ/ እየሩሳሌም ታረቀኝ ፈለቀ ስም በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በን/ስ/ክ/ከተማ ወረዳ 12 የይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፊኬት (ካርታ) AA00008l200868 የሆነው ካርታ የሴሪ ቁጥሩ 002007 የሆነው ይዞታ የይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፊኬት (ካርታ) ስለጠፋባቸው በማናቸውም ምክንያት አግኝቼዋለሁ /ይዤዋለሁ/ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት እስከ 90 ቀን ድረስ ጽ/ቤታችን ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ሰርተፊኬት እንደሚሰጣቸው እናሳስባለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የንፋስ ስልክ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

በጉለሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 02 በቤት ቁጥር 554/553 በካርታ ቁጥር 2089 በአቶ እንግዳ ደስታ ስም የሆነው በእጃቸው መገኘት የነበረበት ኦርጅናል ካርታ የጠፋ በመሆኑ ይህንኑ አስመልክቶ የሚቀርብ ማንኛውም መቃወሚያ ካለ ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ታትሞ ከወጣ ቀን ጀምሮ በ20 ቀን ውስጥ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ ጉለሌ ክፍለ ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ማስረጃውን ይዞ ካልቀረበ ካርታው እንደጠፋ ተቆጥሮ በምትኩ አዲስ ካርታ በማዘጋጀት አገልግሎት የምንሰጥ መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የጉለሌ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

አድዋ ዱቄት ፋብሪካ ሀላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ አስተዳደር ወረዳ 03 ክልል ውስጥ የሚገኝ ይዞታ ተመዝግቦ የተሰጣቸው ካርታ ቁጥር 39453 ሴሪ ቁጥር 6237 የቦታው ስፋት 14,111 ካሬ ሜትር የሆነ ካርታ የጠፋባቸው በመሆኑ በጋዜጣ እንዲታወጅ እየገለጽን በማንኛውም ምክንያት የጠፋውን ካርታ ይዤዋለሁ የሚል አካል ካለ ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ከታወጀበት ዕለት ጀምሮ እስከ 20 ተከታታይ የስራ ቀናት ባለው ጊዜ ውስጥ በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ የመሬት ልማትና አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት ካላቀረቡ በምትክ ሌላ ካርታ የምንሰጣቸው መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የአቃቂ ቃሊቲ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

አቶ/ወ/ሮ/ወ/ሪት እነ ጡባ አወል ሀሺም በኮልፌ ቀራንዮ ክ/ከተማ በቀደሞ ቀበሌ -------- በአሁኑ ወረዳ 05 ቤት ቁጥር -------ነዋሪ ሲሆኑ ከይዞታ አስተዳደር የተሰጣቸው ካርታ ቁጥር ኮ/ቀ/የማ/ን/መ/301/12395/01 በሴሪ ቁጥር 069917 ኦርጂናሉ ተፈልጎ ሊገኝ ስላልቻለ በምትኩ ሌላ ካርታ እንዲሰጣቸው ይህንን ካርታ በእዳ፣ በዋስትና ወይም በሌላ በማንኛውም ምክንያት ይዤዋለሁ የሚል ካለ በ20 ቀን ውስጥ ኮ/ቀ/ክ/ከተማ ቀርቦ እንዲያሳውቅ ካላሳወቅ ግን በምትኩ ሌላ የምንሰጥ መሆኑን እንገልጻለን፡፡

**ኮልፌ ቀራንዮ ክፍለ ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

በንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ በቀድሞ 20 ቀበሌ 52 በአዲሱ ወረዳ 06 የቤት ቁጥር----- በካርታ ቁጥር 18299/29035/01 በአቶ/ወ/ሮ/እነ ይዘንጋው መንግስቱ ስም ተመዝግቦ ተሰጥቶ የነበረ ካርታ የጠፋ ስለሆነ በማንኛውም ምክንያት ይዤዋለሁ የሚል አካል ማስታወቂያው በጋዜጣ ከወጣበት እስከ 20 ቀን ድረስ ለንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ድረስ በመቅረብ አቤቱታ እንዲቀርብ፡፡ ይዤዋለሁ የሚል ከሌለ ተለዋጭ ሌላ ካርታ የሚሰጣቸው መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የን/ስ/ላ/ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

የሳንሻይን ኮንስትራክሽን ኃ/የተ/የግ/ማህበር በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ለሚ ኩራ ክ/ከተማ ወረዳ 8 የካርታ ቁጥር ቦሌ8/93/7/19/48460/00 የሆነው ሰርተፊኬት በፅ/ቤታችን ተመዝግቦ የሚገኘው በቤት ባለቤትነት ካርታ በሴሪ ቁጥር 125318 ስለ ጠፋባቸው በማንኛውም ምክንያት አግኝቼዋለሁ የሚል ግለሰብም ይሁን ሌላ አካል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት እስከ 30 ቀን ድረስ ጽ/ቤታችን ካልቀረበ በምትኩ ሌላ ሰርተፊኬት /ካርታ/ ተዘጋጅቶ እንደሚሰጣቸው እናሳውቃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የለሚ ኩራ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

በደስታ ሽፈራው ሰለሞን በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በን/ስ/ላ/ክ/ከተማ ወረዳ 12 የሚገኘው በይዞታ ልዩ መለያ ቁጥር AA00008l108458 በሴሪ ቁጥሩ 0134716 በስማቸው በጽ/ቤታችን ተመዝግቦ የሚገኘው ይዞታ የይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፊኬት ስለጠፋባቸው በማናቸውም ምክንያት አግኝቼዋለሁ /ይዤዋለሁ/ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ እስከ 90 ቀን ድረስ ጽ/ቤታችን ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ሰርተፊኬት እንደሚሰጣቸው እናሳስባለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የንፋስ ስልክ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ፅ/ቤት**

---

ከላይ ለመግለጽ እንተሞከረው በለሚ ኩራ ክ/ከተማ ክልል ውስጥ የሚገኝ ቦ/አያ/108/1943/01 በሴሪ ቁጥር 005056 ቴዎድሮስ ቀለሙ አየለ ስም ተመዝግቦ የሚገኝ ቤት የኮንደሚንየም ቤት እናት ማህደር ከለሚ ኩራ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት በማህደር ክፍላችን ተፈልጎ ባለመገኘቱ ማህደራቸውን ልናደራጅላቸው ስለሆነ ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ከወጣበት ቀን አንስቶ በ30 ቀናት ውስጥ በለሚ ኩራ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት ተቃውሞውን እንዲያቀርቡ እያሳሰብን፣ በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ ተቃውሞ የማያቀርቡ ከሆነ በምትኩ በመመሪያው በሚፈቅደው መሠረት ሌላ ካርታ የሚሰጣቸው መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የለሚ ኩራ ክፍለ ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

ወ/ሮ ፀሀይ ግርማ ገብሩ በኮልፌ ቀራንዮ ክ/ከተማ በቀድሞ ቀበሌ ----- በአሁኑ ወረዳ 05 ቤት ቁጥር ----- ነዋሪ ሲሆኑ ከይዞታ አስተዳደር የተሠጣቸው ካርታ ቁጥር ሊዝ 9747/95 በሴሪ ቁጥር 018859 ኦርጂናሉ ካርታ ተፈልጎ ሊገኝ ስላልቻለ በምትኩ ሌላ ካርታ እንዲሰጣቸው ይህንን ካርታ በዕዳ፣ በዋስትና ወይም በሌላ በማንኛውም ምክንያት ይዤዋለሁ የሚል ካለ በ30 ቀን ውስጥ ኮ/ቀ/ክ/ከተማ መሬት ልማት አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት ቀርቦ እንዲያሳውቅ ካላሳወቀ ግን በምትኩ ሌላ ካርታ የምንሰጥ መሆኑን እንገልጻለን፡፡

**ኮልፌ ቀራንዮ ክፍለ ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

በለሚ ኩራ ክ/ከተማ ወረዳ 03 በአዲስ መንደር የቤት ስራ አ/ማ ስም የተመዘገበ ካርታ ቁጥር ቦሌ10/107/7/8/6704/00 ሴሪ ቁጥር 0116677 የሆነው የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ የጠፋ ስለሆነ ቤቱን በዕዳ ይዤዋለሁ፤ አስይዤዋለሁ የሚል አካል በ30 ቀናት በጋዜጣ ጥሪ ስለሚደረግ በተጠቀሰው ቀናት ውስጥ ለተቋሙ እንዲያሳውቁን እያልን በዚህ ምክንያት ለ30 ቀናት የሚቆይ በጋዜጣ ጥሪ እንዲደረግ እየጠየቅን ይህ ጋዜጣ ጥሪ ከተደረገ በኋላ አዲስ ካርታ የምንሰራ መሆኑንና ሀላፊነት የማንወስድ መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የለሚ ኩራ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

የወልመስ ኮንስትራክሽን ኃ/የተ/የግ/ማህበር ስም የተመዘገበ ይዞታ ካርታ ቁጥር ለ/ኩራ/3/46/3/58524/0148/12/01 ሴሪ ቁጥር 1645059 የሆነው የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ በእኛ ተቋም የተሰጠ መሆኑ ይታወቃል፡፡

ይሁንና ወልመስ ኮንስትራክሽን ኃ/የተ/የግ/ማህበር ስም የተመዘገበ ይዞታ ካርታ ቁጥር ለ/ኩራ/3/46/3/58524/0148/12/01 ሴሪ ቁጥር 1645059 የተሰጠበት ቀን 19/4/15 ዓ.ም የቤቱ ወለል ስፋት 118 ሜ.ካ የቤቱ አገልግሎት ለመኖሪያ ለሚ ኩራ ክ/ከተማ ወረዳ 03 ካርታ የጠፋ ስለሆነ ይዞታ ቤቱን በዕዳ ይዤዋለሁ፤ አስይዤዋለሁ የሚል አካል በ30 ቀናት በጋዜጣ ጥሪ ስለሚደረግ በተጠቀሰው ቀናት ውስጥ ለተቋሙ እንዲያሳውቁን እያልን በዚህ ምክንያት ለ30 ቀናት የሚቆይ በጋዜጣ ጥሪ እንዲደረግ እየጠየቅን ይህ ጋዜጣ ጥሪ ከተደረገበት በኋላ ሀላፊነት የምንወስድ ይሆናል፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የለሚ ኩራ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

ከላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው በለሚ ኩራ ክ/ከተማ ክልል ውስጥ የሚገኝ ቦሌ14/149/5906/ሊ/ዕ/8227/95/01 በሴሪ ቁጥር 127783 አያት ሙሳ አማረ ስም ተመዝግቦ የሚገኝ ቤት እናት ማህደር ከለሚ ኩራ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት በማህደር ክፍላችን ተፈልጎ ባለመገኘቱ ማህደራቸውን ልናደራጅላቸው ስለሆነ ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ከወጣበት ቀን አንስቶ ከ30 ቀናት ውስጥ በለሚ ኩራ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት ተቃውሞውን እንዲያቀርቡ እያሳሰብን፣ በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ ተቃውሞ የማያቀርቡ ከሆነ በምትኩ በመመሪያው በሚፈቅደው መሠረት ሌላ ካርታ የሚሰጣቸው መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የለሚ ኩራ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

በጉለሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 03 በቤት ቁጥር 556 በካርታ ቁጥር 3/18/21420/00 በአቶ ዳመና ገ/አምላክ ስም የሆነው በእጃቸው መገኘት የነበረበት ኦርጂናል ካርታ የጠፋ በመሆኑ ይህንኑ አስመልክቶ የሚቀርብ ማንኛውም መቃወሚያ ካለ ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ታትሞ ከወጣ ቀን ጀምሮ በ20 ቀን ውስጥ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ ጉለሌ ክፍለ ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ማስረጃውን ይዞ ካልቀረበ ካርታው እንደጠፋ ተቆጥሮ በምትኩ አዲስ ካርታ በማዘጋጀት አገልግሎት የምንሰጥ መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የጉለሌ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

ከላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው በለሚ ኩራ ክ/ከተማ ክልል ውስጥ የሚገኝ በካርታ ቁጥር ድ0579 በሴሪ ቁጥር 3517 በአቶ/በወ/ሮ/በወ/ሪት ዲይላይት አፕላይድ ቴክኖሎጂስ ኃ/የተ/የግ/ኩባንያ ስም ተመዝግቦ የሚገኝ ማህደር ከለሚ ኩራ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት በማህደር ክፍላችን ተፈልጎ ባለመገኘቱ ማህደራቸውን ልናደራጅላቸው ስለሆነ ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ከወጣበት ቀን አንስቶ በ30 ቀናት ውስጥ በለሚ ኩራ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት ተቃውሞውን እንዲያቀርቡ እያሳሰብን፣ በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ ተቃውሞ የማያቀርቡ ከሆነ በምትኩ በመመሪያው በሚፈቅደው መሠረት ሌላ ካርታ የሚሰጣቸው መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የለሚ ኩራ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

አቶ ሀዲ ታንቀቶ አይዳሼ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ አስተዳደር ወረዳ 01 ክልል ውስጥ የሚገኝ ይዞታ ተመዝግቦ የተሰጣቸው ካርታ ቁጥር 015870 ሴሪ ቁጥር 079603 የቦታው ስፋት 642.7 ካሬ ሜትር የሆነ ካርታ የጠፋባቸው በመሆኑ በጋዜጣ እንዲታወጅ እየገለጽን በማንኛውም ምክንያት የጠፋውን ካርታ ይዤዋለሁ የሚል አካል ካለ ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ከታወጀበት ዕለት ጀምሮ እስከ 20 ተከታታይ የስራ ቀናት ባለው ጊዜ ውስጥ በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ የመሬት ልማትና አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት ካላቀረቡ በምትክ ሌላ ካርታ የምንሰጣቸው መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የአቃቂ ቃሊቲ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

ከላይ በርዕሱ ለመጥቀስ እንደተሞከረው በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ አዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ ቅርንጫፍ ከአዲስ ከተማ ክ/ከተማ ወረዳ 14 የቤት ቁጥር አዲስ በአቶ ነገዎ ደበላ ምህረቴ ስም የተመዘገበው የይዞታ ካርታ ቁጥር 14/2/1/2299 ሴሪ ቁጥር 0249557 የሆነው የይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፍኬት (ካርታ) እንደጠፋባቸው በቀን 12/10/2017 ዓ.ም ያመለከቱ ሲሆን ይህንኑን የይዞታ ካርታ ይዤዋለሁ (አግኝቼዋለሁ) የሚል አካል ካለ ይህ ማስታወቂያ በአዲስ ልሳን ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ባሉት ተከታታይ በ 30 ቀናት ውስጥ በአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ የመሬት ይዞታ ምዝገባ እና መረጃ ኤጀንሲ ቅ/ጽ/ቤት ማቅረብ የሚችል ሲሆን ይህ የማይሆን ከሆነ ግን ምትክ የማረጋገጫ ሰርተፍኬት (ካርታ) የሚሰጣቸው መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ አዲስ ከተማ ክ/ከተማ ቅ/ጽ/ቤት**

---

አዜብ ስምኦን ቢሂል በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በቦሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 04 የይዞታ መለያ ቁጥር AA000060400925 ሴሪ ቁጥር R 0130877 የሆነ በጽ/ቤታችን ተመዝግቦ የሚገኝ ይዞታ የቤት ባለቤትነት ምዝገባ ምስክር ወረቀት/ካርታ ስለጠፋባቸው በማናቸውም ምክንያት አግኝቼዋለሁ /ይዤዋለሁ/ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት እስከ 90 ቀን ድረስ ጽ/ቤታችን ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ሰርተፊኬት እንደሚሰጣቸው እናሳስባለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ ቦሌ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

አቶ ተስፋዬ ተክለዮሀንስ ወልደጸዲቅ አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በጉ/ክ/ከተማ ወረዳ 08 ነዋሪ የሆነው የይዞታ ልዩ መለያ ቁጥር AA000100803026 የሴሪ ቁጥር 098632 በቀን 04/06/2016 ዓ/ም ወጪ የተደረገ ካርታ በጽ/ቤታችን ተመዝግቦ የሚገኘው የይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፊኬት /ካርታ/ ስለጠፋባቸው በማናቸውም ምክንያት አግኝቸዋለሁ /ይዤዋለሁ/ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ እስከ 90 ቀን ድረስ ጽ/ቤታችን ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ሰርተፊኬት እንደሚሰጣቸው እናስታውቃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ ጉለሌ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

**ጉዳዩ፡- የጠፋ ካርታ በጋዜጣ እንዲወጣ ስለማሳወቅ ይመለከታል።**

ከላይ በርዕሱ ለመጥቀስ እንደተሞከረው በየካ ክ/ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የካ ክፍለ ከተማ ቅርንጫፍ ወረዳ 10 በእነ መሰለች ቱፋ ማለት 1. መሰለች ቱፋ ዋኬኔ 2. ፀጋዬ ገብረማርያም ሮባ 3. ወንደሰን ገብረማርያም ሮባ 4. ሮባ ገብረማርያም ሮባ 5. ፍሬህይወት ገብረማርያም ሮባ 6. ኤልያስ ገብረማርያም ሮባ ስም የተመዘገበ ይዞታ የይዞታ ልዩ መለያ ቁጥር AA000051002974 እና የሴሪ ቁጥር R 047180 የሆነ ካርታ መጥፋቱን ከላይ የተጠቀሱት ግለሰቦች ያመለከቱ ሲሆን ይህንኑ የይዞታ ካርታ በጋዜጣ 90 ቀን ውስጥ ሙብት አለኝ የሚል እና ካርታው መጥፋቱን ከላይ የተጠቀሱት ግለሰቦች የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር መሬትና ምዝገባ መረጃ ኤጀንሲ የካ ቅርንጫፍ ማስታወቅያ እንዲወጣልኝ ሲሉ ያመለከቱ ስለሆነ ካርታው መጥፋቱን በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባ መረጃ ኤጀንሲ የካ ቅርንጫፍ እንዲያሳውቅ እየገለጽን ይህ ባይሆን ለአመልካቹ አዲስ ካርታ ወጪ ተደርጎ የሚሰጥ መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የካ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

በመሀመድ ዘይኑ ሀሰን ስም በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በን/ስ/ክ/ከተማ ወረዳ 02 በይዞታ መለያ ቁጥር AA000080208750 የሆነው የካርታው የሴሪ ቁጥሩ L 058769 የሆነው ይዞታ የይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፊኬት(ካርታ) ስለጠፋባቸው በማናቸውም ምክንያት አግኝቼዋለሁ /ይዤዋለሁ/ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት እስከ 90 ቀን ድረስ ጽ/ቤታችን ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ሰርተፊኬት እንደሚሰጣቸው እናሳስባለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የንፋስ ስልክ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

## ‘ኢትዮጵያን... ከገጽ 3 የዞረ

ፍላጎት ከጎረቤቶቿ ጋር በጋራ መልማት መሆኑን ገልጸው የኢትዮጵያ ሰላም መሆንና መልማት ለቀጣናው ዕድገት በጎ ሚና እንደሚጫወትም ጨምረው ተናግረዋል። ኢትዮጵያ ትልቅ ሀገር እና ከፍተኛ የህዝብ ብዛት ያላት ናት ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ ሰላም እና ልማት ለኢትዮጵያ ቁልፍ ጉዳዮች እንደሆኑ ጎረቤቶቿ ሊረዱ እንደሚገባ አመልክተዋል። ኢትዮጵያ የባህር በር ጥያቄዋ በህጋዊ እና ሰላማዊ መንገድ ምላሽ እንዲያገኝ እየሰራች እንደምትገኝም ተናግረዋል። የባህር በር አለመኖር በኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ላይ ከፍተኛ ጫና እያሳደረ እንደሚገኝም ገልጸው ጉዳዩ አፋጣኝ መፍትሄ እንደሚያሻው አሳስበዋል።

አክለውም ኢትዮጵያ የባህር በር እንደሚያስፈልጋት እና ይህም በንግድ ህጎች አማካኝነት ምላሽ ያገኛል ብለው እንደሚያምኑም ጠቅላይ ሚኒስትሩ ገልጸዋል። የጎረቤት ሀገራት የኢትዮጵያን የባህር በር ጥያቄ በቀናነት እንዲረዱትና ጥያቄው ከመልማት እና ከማደግ ካለ ጽኑ ፍላጎት የመነጨ እንደሆነ መገንዘብ እንደሚገባቸው አንስተዋል።

ለውጡ ከመምጣቱ በፊት በነበረው የኢሕአዴግ መንግሥት ፓርቲዎች አጋር እና ዋና ተብለው የተለዩ መሆናቸውን የጠቀሱት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ብልፅግና ፓርቲ ግን ይህን አካሄድ እንደቀየረ ተናግረዋል። እንደ ምርጫ ቦርድ እና የሰብዓዊ መብቶች ኮሚሽን ያሉ የዴሞክራሲ ተቋማት ነጻ መደረጋቸውን የጠቀሱት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፣ ላስተዋለ አካል ይህ ትልቅ ለውጥ መሆኑን ገልጸዋል፡፡ መንግሥት እነዚህ የዴሞክራሲ ተቋማት በነጻነት እንዲሠሩ ጣልቃ እንደማይገባ ጠቁመው፣ “የሰብዓዊ መብቶች ኮሚሽን በርካታ ሪፖርቶችን እኛ ላይ ሲያወጣ ይህም ልምምድ መሆን አለበት ብለን ምንም አላልንም” ብለዋል፡፡ ለውጡ በፖለቲካ ብቻ ሳይሆን በኢኮኖሚ እና በማኅበራዊ ዘርፍም በግልጽ እንደሚስተዋል ጠቅሰዋል፡፡

አሁን ያለው መንግሥት ትላንት የተሠሩ መልካም ነገሮችን ሁሉ አሳምሮ በማስቀጠል እንደሚያምን በቅርሶች እድሳት ላይ እየተሠራ ያለው ሥራ ማሳያ እንደሆነ ያወሱት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፣ ይህም የእውነተኛ ለውጥ ማሳያ ነው ብለዋል፡፡

የኑሮ ውድነቱን አስመልክቶ ከፖለቲካ ፓርቲዎች ለተነሳላቸው ጥያቄ በሰጡት ምላሽ የዋጋ ግሽበቱን ለማስተካከል ባለፉት ዓመታት በተሰሩ ስራዎች ለውጥ መምጣቱን አንስተው የዋጋ ግሽበቱ በዚህ ዓመት በግማሽ ስለመቀነሱ ተናግረዋል። ይህንንም ለማድረግ ምርታማነትን ማሳደግ፣ ከፍተኛ ድጎማ ማድረግ እና የንግድ ስርዓቱን የማዘመን ስራዎች እየተሰሩ መሆኑን አስረድተዋል፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ(ዶ/ር) ከሰሞኑን ከተፎካካሪ ፖለቲካ ፓርቲዎች በተጨማሪ ከመምህራን፣ ከንግዱ ማህበረሰብ፣ ከኪነ ጥበብ ባለሙያ ተወካዮችና ከሌሎች የህብረተሰብ ክፍሎች ጋር ውይይቶችን ሲያደርጉ መቆየታቸው ይታወሳል፡፡

# የመላው ኢትዮጵያ ጨዋታዎችና ተጠባቂው ውጤት



ፎቶ ከገፀ ድር

ከዘጠኝ ዓመት በኃላ ወደ ውድድር የተመለሰው የመላው ኢትዮጵያ ጨዋታዎች ከ4500 በላይ ስፖርተኞች በ26 የስፖርት አይነቶች ይሳተፋሉ

**በሳህሉ ብርሃኑ**

ስፖርት ለህዝቦች አንድነት መጠናከር ፍቱን መድኃኒት ስለመሆኑ የስፖርት ባለሙያዎች ይገልጻሉ፡፡ እንደዚሁም ስፖርታዊ ውድድሮች የሰላምና የአንድነት አየር እንዲነፍስ የሚጫወቱት ሚና ከፍ ያለ ነው፡፡ ጥንታዊውና በየአራት ዓመቱ አንድ ጊዜ የሚከናወነው የኦሎምፒክ ጨዋታዎች ውድድርም ለዚህ በአስረጅነት ከሚጠቀሱ ውድድሮች መካከል ቀዳሚው ነው። የሰላምና የአንድነትን ችቦ በመለኮስ የሚካሄደው የኦሎምፒክ ጨዋታዎች ውድድር ሰላም፣ አንድነትና መከባባር የሚሰበክበት መድረክ ነው፡፡

በፈረንጆቹ ሚያዝያ ወር በዓለም አቀፍ ደረጃ ስፖርት ለልማትና ለሰላም በሚል የሚዘከረውም ለዚሁ ነው፡፡ ስፖርት ለአዕምሮ ጤናና ለአካል ከሚሰጠው ጠቀሜታ በተጨማሪ ማኅበራዊ ትስስርን በማጎልበት ዘላቂ ሰላምና ልማትን ለማፋጠንም ትልቅ ጠቀሜታ እንዳለው ግንዛቤ ለማስጨበጥ በዓለም አቀፍ ደረጃ ይታወሳል። ስፖርት በሕዝቦች መካከል ያለውን ግንኙነት ለማጠናከርም ከፍተኛ ጠቀሜታ እንዳለውና ይህንን ትሩፋት ማስፋት እንደሚገባም የመስኩ ተንታኞች ይገልጻሉ።

ከዘጠኝ ዓመታት ቆይታ በኋላ ዳግም የተመለሰው የመላው ኢትዮጵያ ጨዋታዎች የውድድር መንፈስም በዚሁ ዙሪያ የሚቃኝ ነው፡፡ ኢትዮጵያ የኦሎምፒክ መርህን በመከተል መላዉ ኢትዮጵያ ጨዋታዎችን እያካሄደች የቆየች ቢሆንም ከ2008 ዓ.ም ጀምሮ ለ9 ዓመታት ተቋርጦ ቆይቷል። የተቋረጠውን የመላው ኢትዮጵያ ጨዋታ ዘንድሮ በማስጀመር ከሰኔ 10 እስከ 19/2017 ዓ.ም ድረስ በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት አስተናጋጅነት በጅማ ከተማ እየተካሄደ ይገኛል፡፡

በጅማ ከተማ የሚካሄደው 6ኛው የመላው ኢትዮጵያ ጨዋታዎች ከስፖርታዊ ውድድርነቱ ባሻገር የህዝቦችን አንድነት የሚያጠናክርና ስፖርታዊ ጨዋነት የተላበሰ ተተኪ ስፖርተኞች ለማፍራት ወሳኝ እንደሆነም በባህልና ስፖርት ሚኒስቴር ተገልጿል። በኢትዮጵያ ዘመናዊ የከተሞች ታሪክ ሲነሳ ተጠቃሽ የሆነችው ጅማ ከተማ ከ4 ሺህ 500 በላይ ስፖርተኞች የተገናኙትም ለዚሁ ነው። በኦሎምፒክ መርህ በሚደረገው እና በባህልና ስፖርት ሚኒስቴር አስተባባሪነት በኦሮሚያ ክልል መሪነት በጅማ ከተማ አስተናጋጅነት እየተካሄደ ባለው ውድድር ላይ ከ12 ክልሎች እና 2 ከተማ አስተዳድር የተወጣጡ ስፖርተኞች እየተሳተፉ ነው፡፡

እንደዚህ አይነት ውድድሮች ከስፖርቱ ዕድገት ባሻገር ዘርፈ ብዙ ፋይዳ እንዳላቸው የሚገልጹት ደግሞ በአርባ ምንጭ ዩንቨርሲቲ የስፖርት ሳይንስ ትምህርት ክፍል መምህሩ አቶ አሰግድ ከተማ ናቸው፡፡ እሳቸው እንደሚሉት የሰላም ምልክት የሆነውን ስፖርታዊ ውድድር በህዝቦች መካከል ጠንካራ ግንኙነት እንዲጎለብትም ድርሻው ቀላል አይደለም። ስፖርት ከአካላዊ ብቃትና ለጤንነት ጥቅም ባሻገር ወዳጅነትን፣ ፍቅርንና፣ አንድነትን ለማጠናከር፣ የአንድ አካባቢ ባህልና ወግን ለሌሎች ለማሳየት፣ አዳጊና ተተኪ ወጣቶች ከተጫዋቾች ልምድ የሚቀስሙበት ብሎም ስፖርተኞችን ለማፍራት አስተዋጽኦ እንደሚያበረክትም ያስረዳሉ አቶ አሰግድ፡፡

የመላው ኢትዮጵያ ጨዋታዎችን አስመልክቶ የባህልና ስፖርት ሚኒስትር ዴኤታ አቶ መኪዩ መሀመድ በሰጡት አስተያየት ስፖርት ለአብሮነት ለሰላምና ለእርስ በእርስ ግንኙነት ከፍተኛ ሚና አለው፡፡ ውድድሩ አዳጊ ስፖርተኞችን ለማፍራት አይነተኛ መድረክ ነው ብለዋል፡፡

በስፖርት ኢንደስትሪ ውስጥ ተዋናይ ሆኖ ለመቀጠል እራስን ማብቃት፣ ማስተማርና ተራማጅ አስተሳሰቦች እንዲሁም አመለካከቶችንና ዘዴዎችን ተግባራዊ ማድረግ ያስፈልጋል የሚሉት አቶ መኪዩ መሀመድ ስፖርት ከመዝናኛነት ውድድር ባለፈ ለማህበራዊ ትስስር፣ ለሀገራት ግንኙነት (ዲፕሎማሲ)፣ ለኢኮኖሚያዊ እድገት እና ለስራ እድል ፈጠራ ያለው አስተዋጽኦ እጅግ ከፍተኛ ነው ይላሉ፡፡

አያይዘውም የስፖርት ኢንዱስትሪውን በእውቀት በመምራት የተሻለ ውጤት ማስመዝገብ ይገባል የሚሉት አቶ መኪዩ በስፖርት ሀገራዊ የልማት ግብ፤ አንድነቱ የተጠበቀ፣ ማህበራዊ ትስስሩ የጎለበተ፣ ጤናማ ዜጋ እና አሸናፊ ሀገር መፍጠር ይገባል። ለዚህም ዓላማ ስኬት በጥናትና ምርምር ላይ የተመሠረተ የአሰራር ስርዓት መዘርጋት፣ ብቃት ያለው የሰው ኃይል ማፍራት እና በቴክኖሎጂ የተደገፈ አገልግሎት በመስጠት በየጊዜው ዓለም አቀፋዊ ሁኔታን ያገናዘበ የውይይት እና ምክክር መድረኮችን ማዘጋጀት ያስፈልጋል ብለዋል።

ስፖርት ለማህበራዊ ጉዳዮችና ለሀገር ግንባታ ያለውን ፋይዳ በሚያጎላ መልኩ ለመጠቀም 6ኛው መላው ኢትዮጵያ ጨዋታ ወሳኝ መሆኑን የስፖርት ሳይንስ መምህሩ አቶ አሰግድ ተናግረዋል፡፡ እንደዚሁም ስፖርት ከመዝናኛነት ባሻገር በማህበራዊ ትስስርና ሀገር ከመገንባት አኳያ ያለው ሚና ከፍተኛ እንደሆነ ያስረዳሉ፡፡

ከዚህ በፊት ኢትዮጵያ በሀገር ውስጥና ከጎረቤት ሀገራት ጋር ጭምር ስፖርትን የሰላም መፍጠሪያ፣ ወዳጅነትና አንድነትን ማጠናከሪያ በማድረግ ትጠቀምበት እንደነበር የታሪክ ድርሳናት ይነግሩናል። የመላ ኢትዮጵያ ጨዋታ በ26 የስፖርት አይነቶች በጅማ ዩኒቨርስቲ ስታዲየምና በተለያዩ የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች "ስፖርት ለህብር ኢትዮጵያ አርበኝነት" በሚል መሪ ሃሳብ እየተከናወነ የሚገኘውም ውድድር ከዚህ አንጻር የሚታይ ነው፡፡

በአርባ ምንጭ ዩንቨርሲቲ የስፖርት ሳይንስ ትምህርት ክፍል መምህሩ አቶ አሰግድ እንደሚያስረዱት እንደዚህ ዓይነት ውድድሮች ሌላም ወሳኝ ጥቅም አላቸው፡፡ እንደዚህ ዓይነት ሀገር አቀፍ ውድድሮች ላይ ዋነኛ ትኩረታቸው አዳጊዎች ላይ በመሆኑ ፋይዳው ለሀገርም ይተርፋል ይላሉ፡፡ አዳጊዎች ዕድል አግኝተው ብቃታቸውን ማሳየት ከቻሉ በቀጣይ ብሔራዊ ቡድናቸውን የማገልገል ተስፋ ይኖራቸዋልም ብለዋል፡፡

የተለያዩ የስፖርት ክለቦችም በተጨዋቾች የዝውውር ገበያና ደሞዝ የሚገጥማቸውን የናረ ወጭ መቆጣጠር ይችላሉ፤ በየጊዜው ተተኪ ተጨዋቾችን ያፈሩባቸዋል፤ ዋና ቡድኖቻቸውን በየጊዜው ለማጠናከር አይቸገሩም። የሚያፈሯቸውን ተጨዋቾች በዝውውር ገበያዎች በማቅረብ ትርፋማ የሚሆኑበትን ዕድልም ይፈጥርላቸዋል ብለዋል፡፡

አክለውም ክለቦችን በአግባቡ ለማስተዳደር እንደዚሁም የተረጋጋ ቡድን ለመገንባት አዳጊዎች ላይ አተኩሮ መስራት ግድ ይላል ብለዋል፡፡ በሌላም በኩል የሁሉም ስፖርት አይነት ክለቦች በውድድሩ ላይ የምልመላ ባለሙያዎችን መድበው በየአካባቢው የተለየ ችሎታ ያላቸው ወጣቶች የመመልመል ስራ መስራት ይኖርባቸዋል ሲሉም አቶ አሰግድ ያሳስባሉ፡፡ ክለቦቹ ይህንን ካደረጉም ከመላው ኢትዮጵያ ጨዋታዎች ተተኪ ስፖርተኞችን ለማፍራት መንገድ እንደሚከፍትና ለስፖርት ዘርፉ ለውጥ ለማምጣት ዕድል እንደሚፈጥርም ያስረዳሉ።

ለዘጠኝ ዓመታት የመላው ኢትዮጵያ ጨዋታዎች ከመቋረጡ በፊት የመጨረሻ አዘጋጅ የነበረው የሲዳማ ክልል የነበረ ሲሆን ከሰሞኑን የጀመረው ውድድርም እስከ ሰኔ 19 ቀን/2017 ዓ.ም ድረስ በጅማ ከተማ የሚካሄድ ይሆናል፡፡


## ከቀዳሚዎቹ ነን!!

ከቀዳሚ የመረጃ ምንጭነት የትውልድ ድምጽ ለመሆን እስከመትጋት!!
ከ20 አመት በላይ በሞገድ AMN FM 96.3 ደግሞ እንደገና
ከዘመኑ በቀደመ ከበፊቱ በብዙ በተሻለ የሬዲዮ ማሰራጫ ቴክኖሎጂ ታጥቀን መጥተናል!!



በላቀ ጥራት፣ በአዲስ ጉልበት በማራኪ ይዘት እና አቀራረብ
በያላችሁበት መጥተናል

አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ
ኤፍ ኤም 96.3 የትውልድ ድምፅ